
የደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለምና የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን
እንቶጸ ተዋህዶሰንበት ት/ቤት

መልዕልተ አድባራት ቀራንዮ መድኃኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት አንቀጸ ተዋሕዶ ሰንበት ትምህርት ቤት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ታሪክ

ለካልዓይ ኮርስ የተዘጋጀ

አዘጋጅ ዲ/ን ጌታመሳይ ኃይለሚካኤል ኃይለማርያም

2009 ዓ/ም

መግቢያ 6
የትምህርቱ አላማና ግብ 6
ምዕራፍ አንድ 8
1. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት 8
1.1. የታሪክ ትምህርትን ለምን እንማራለን? 8
1.1.1. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ምንነት 9
1.1.2. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ መረጃዎች ዐበይት ችግሮችና መፍትሔዎች 9
1. ተፈጥሯዊ ምክንያቶች 10
2. ሰው ሰራሽ ምክንያቶች 10
1.1.3. መፍትሔዎቻቸው 11
1.1.4 ታሪክ በየመስኩ 11
1.1.5 ታሪክ ከአፈታሪክ የሚለየው እንዴት ነው? 12
1.1.6 ታሪክን እንዴት ማወቅ ይቻላል? 12
1.1.7 የታሪክ ምንጭ 13
1.2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ስያሜ 14
1.2.1. ኢትዮጵያ በጥንት ግብጻውያን አጠራር 14
1. ጱንጥ 14
2. ቶ-ኔቶር 15
3. ኩሽ ምድር 16
1.2.2. ኢትዮጵያ በጥንት ግሪካውያን አጠራር 16
1.2.3. የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሌሎች መጠሪያዎች 18
ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስያሜ ትርጉምና ትርጓሜ 19
ኦርቶዶክስ (Orthodox) 19
ተዋሕዶ (Miaphysite) 19
ምእራፍ ሁለት 21
2.የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን በቅድመ ክርስትና 21
2.1 የኢትዮጵያ እምነት በሕገ ልቡና ዘመን 21
2.1.1. ሄኖክ 21
2.1.2. መልከጼዲቅ 21

2.1.3. ዮቶር ራጉኤል 22
2.1.4. ሲጳራ 22
2.2. የኢትዮጵያ እምነት በሕገ ኦሪት ዘመን 22
2.2.1. ንግስተ ሳባ ኢትዮጵያዊት ወይስ ዐረባዊት (የመናዊት) 23
ሀ) የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት፡- 24
ለ) ክብረነገስት፡- 25
ሐ) ትውፊታዊ የጥንት ጥናት መካናት (Archeological Site) በአገራችን መገኘታቸው 26
2.2.2. ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን ያደረገችው ጉዞ ያበረከተው አስተዋጽዖ 26
2.2.3. ቀዳማዊ ምኒልክ ማነው? 27
2.2.4. የታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት 28
2.2.5. የብሉይ ኪዳን ዕምነት እና ሥርዓት በኢትዮጵያ 28
1. በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመዱና የሚታወቁ አይሁዳዊ ትውፊቶች (Judaic Elements) 28
ሀ) የታቦተ ጽዮን መኖርና አከባበሩ 28
ለ) ቀዳሚት ሰንበትን ማክበር 29
ሐ). ልብሰ ተክህኖ (የካህናት ልብስ) 29
መ) ግዝረት 29
ሠ) የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትን መለየት 30
ረ) የማሕሌት ሥነ-ሥርዓትና የመዝሙር መሣሪያዎች 30
ሰ) እንግዳ መቀበል 30
ሸ) በደስታና በሐዘን ያለጊዜ ያለው ሁኔታ፤... ወዘተ 30
ምዕራፍ ሦስት 31
3. ክርስትና በጥንታዊት ኢትዮጵያ 31
3.1. የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ መግባት 31
3.1.1. የብሉይ ኪዳን እምነት፣ ሥርዓትና ትንቢት ቀድሞ በሀገራችን መታወቁ 31
3.1.2. ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የነበራት የጠበቀ ግንኙነት 33
3.1.3. የንግስት ህንደኬ ጃንደረባ ጉዞ ወደ ኢየሩሣሌም 33
3.1.4. ኢየሩሳሌም ተገኝተው በዓለ ኃምሳን ያከበሩ ኢትዮጵያውያን 34
3.1.5. የሐዋርያት አስተዋጽኦ 34
3.1.6. ክርስትና አስቀድሞ በነገሥታት አካባቢ ተቀባይነት ማግኘቱ 34

3.2. በኢትዮጵያ ለክርስትና ሃይማኖት መታወቅና መስፋፋት አስተዋጽኦ ያበረከቱ ቅዱሳን 34
3.2.1. ኢትጵያዊው ጃንደረባ 34
3.2.2. ቅዱስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማከሣቴ ብርሃን) 35
3.2.3. ዘጠኙ ቅዱሳን 36
3.2.4. ዐፄ ካሌብ 38
3.2.5. ቅዱስ ያሬድ 38
3.2.6. ዐፄ ገብረመስቀል 39
3.3. የጨለማው ዘመን ተጽዕኖዎች 39
3.3.1. የእስልምና እምነት መስፋፋት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ያደረሰው ተጽዕኖ 40
3.3.2. የዮዲት ጉዲት የጥፋት ዘመቻ 41
3.4. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ዛጉዌ ሥርወ መንግሥት 41
3.4.1. ካህናተ ነገሥታት 42
3.4.2. የውጭ ግንኙነት 42
ቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ 43
ቅዱስ ሀርቤ 43
ቅዱስ ላሊበላ 43
3.4.3. የዓለት ላይ አብያተ ክርስቲያናት ሥራ 44
የቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት 44
ምዕራፍ አራት 45
4. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በመካከለኛው የታሪክ ዘመን 45
4.1. ወርቃማ መንፈሳዊ ክስተቶች 45
4.1.1. የገዳማዊ ሕይወት መስፋፋት 45
4.1.2. የስብከተ ወንጌልና የትምህርተ ሃይማኖት መጠናከር 46
4.1.3. የግዕዝ ስነጽሑፍ ዕድገት 48
4.1.4. የውጭ ግንኙነት 49
ሀ) የግማደ መስቀሉ ወደ ሀገራችን መምጣት 49
ለ) የፍሎረንሱ የሃይማኖት ጉባኤ 50
ሐ) የደብረ ምጥማቅ ቤተክርስቲያን የተሠራችበት ምክንያት 51
4.1.5. የኢትጵያ ቤተክርስቲያን በጎንደር ዘመነ መንግሥት (፲፮፳፰-፲፯፻፸፪) 51

4.2. ዓበይት የቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች 52
4.2.1. የደቂቀ እስጢፋ የተቃውሞ ትምህርት 52
4.2.2. የቤተ ተክለሃይማኖትና የቤተ ኤውስጣቴዎስ አለመግባባት 52
4.2.3. የአሕመድ ግራኝ ጦርነት 53
4.2.4. የካቶሊክ ሚሲዮናዊያን ትንኮሳ 55
4.2.5. የሐሳዊ መሲሕ መነሳት 56
4.2.6. የዘመነ መሳፍንቱ ክፍፍል 57
ምዕራፍ አምስት 59
5. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዘመናዊ ታሪክ 59
5.1. ነገሥታቱና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን 59
5.1.1. ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (1847-1860) 59
5.1.2. ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (፩ሺ፰፻፰፫) 61
5.1.3. ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (1881-1906 ዓ.ም) 62
5.1.4. ልጅ ኢያሱ፣ ንግሥት ዘውዲቱ፣ ራስ ተፈሪ መኮንን እና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (1906-1922) 64
5.2. ራስን የመቻል ትግል እና ስኬት 65
ምንጮች 69

መግቢያ

‹‹በመንገድ ላይ ቁሙ፣ ተመልከቱም፣ የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ፣መልካሚቱም መንገድ ወዴት እንደሆነች ዕወቁ በእርሷም ላይ ሂዱ፣ ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ፡፡›› ት. ኤር 6÷16

ሃይማኖት በመጀመሪያ ስነፍጥረት ቀን በመላእክት እንደተጀመረች ክህደትም እንዲሁ በተመሳሳይ ቀን በዲያብሎስ አማካኝነት የሃይማኖት ተፃራሪ ሆኖቆሟል፡፡

በሃይማኖት ውስጥ ያለን ሠው፡- አማኝ ከሃይማኖት ውስጥ የወጣን ደግሞ፡- ከሃዲ እንደምንል ዘመናችን ወደ ስህተት ሊመሩ (ሊያደርሱ) የሚችሉ በርካታ መንታ እና አቋራጭ የሚመስሉ መንገዶች የበዙበት ነው፡፡እነዚህም መንገዶች ከዋናው እና ከቀደመችው መንገድ ተነጥለው በተለያየ ጊዜ የተፈጠሩ ሲሆን ቁጥራቸውም ከመብዛታቸው የተነሳ ለመቁጠር ከማስቸገር ደረጃ ደርሷል፡፡ዕረፍተ ነፍስ ወደ ሚገኝበት የምታመራው ዕውነተኛዋ መንገድ ግን አንዲት ናት፡፡ ስለሆነም ጊዜው ቆም ብለን እንድናስብ፣ የቀደመችውን መንገድ እንድንጠይቅና መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እንድናውቅ ግድ ይላል፡፡

በዚህ አንቀፅ መንገድ የተባለችው የዘለዓለም ሕይወት (ዕረፍተነፍስ) ወደ ሚገኝባት መንግስተ ሰማያት የምታመራውን እውነተኛዋን እና ቀዳሚዋን እምነት ነው፡፡በዚህ የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍልም በዚህች በቀደመ እምነት ውስጥ ፀንታ በሦስቱ ሕግጋት ውስጥ የኖረችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ታሪክ እንመለከታለን፡፡

የትምህርቱ አላማና ግብ

የታሪክ ትምህርት ለሰው ልጆች በአጠቃላይም በዓለም ላይ ለሚኖሩ ለማንኛውም ሕብረተሰብ ወይም ሕዝብ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡የታሪክ ትምሕርት የቀድሞውን የሰው ልጆች አነሳስና ዕድገትና ያጋጠሙትን መሰናክሎችና ሲፈራረቁበት የነበረውን ደስታና ችግሮች በአጠቃላይ የሰው ልጆችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፤ ’ማህበራዊ ፣ሐይማኖታዊ ችግሮችና ዕድገቶች ዕውቀት በማስጨበጥ ከዛሬው ተጨማሪ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለሰው ልጅ የነገውን የዕድገትና የብልጽግና ስልቶችን ለመተንበይ የሚስችልበት ትምህርት ነው፡፡ ከዚህም በላይ የሰው ልጅ በአንድ የ(ታሪክ ወቅት ያደረጋቸውን ጥፋቶች እንደገና በዓለም ላይ እንዳይደገም ትምህርት የሚሰጠን የዕውቀት ዘርፍ ነው፡፡ ጠቀሜታውን በአጠቃላይ ስናየው፡-

-በቂ መረጃ ያለውና በራሱ የሚተማመን ዜጋን ለማፍራት፡፡

-ወቅታዊ ሁኔታዎችን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል፡፡

-ነገሮችን ከመሰረቱና ከተለያየ አቅጣጫ ለማየት ያግዛል፡፡

-ያለፉ አባቶችንን መልካም አሰረፍኖት ለመከተል፡፡

-ያለፉትን ችግሮች በማጥናት ዳግም እንዳይከሰት ለማገዝ፡፡

-ያለፈውን ተረድቶ ያለውንም ጠንቅቆ በማወቅ መጪውንም ለመረዳት

ምዕራፍ አንድ

1. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት

1.1. የታሪክ ትምህርትን ለምን እንማራለን?

ታሪክ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ወይም የሰው ልጅ ከአካባቢው ጋር ለዘመናት የነበረውን ግንኙነትና የኑሮ ውጣ ውረድ ለማሸነፍ ያደርገው የነበረውን የትግል ጉዞ አጉልቶ የሚያሳይ የጎበረተሰብ ሳይንስ ክፍል ነው።

- ታሪክ ሦስት ዘመናትን ትላንት፣ ዛሬንና ነገ ንየሚያገኛኝ የድርጊትና የጊዜ ሰንሰለት ነው
- ታሪክ የሰው ልጆች በማናቸውም የሕይወት ጉዳይ ያሳለፉት የኑሮ ልምድ ዘገባ ነው በመሆኑም
- በቂ መረጃ ያለው (Well Informed)
- በራሱ የሚተማመን (Self Confident) እና
- ውሳኔ ለመስጠት የሚችል (Decision Maker) ዜጋ ለማፍራት የጎላ አስተዋፅየ ይኖረዋል።

ስለሆነም የታሪክ ትምህርት ስለ ተለያዩ አጋጣሚዎች መሰረታዊ ግንዛቤ እንዲኖረን ወቅታዊ ሁኔታዎችን በቀላሉ ለመረዳት እንድንችል ነገሮችን ከሥር መሰረቱና ከተለያዩ አቅጣጫ የማየትና የማስተዋልን ልምድ እንድናዳብርና አንድን ነገር በጭፍን ከመቀበል ይልቅ ምክንያታዊ ለመሆን ያግዛል ስለዚህም እንማረዋለን።

ታሪክ በመረጃ የተደገፈና ሳይንሳዊ የጥናት ዘዴን ተከትሎ የሚጻፍ እውነታ (Fact) ስለሆነ ከአፈታሪክ (story) ፍፁም የተለየ ነው ታሪክን ለማጥናት የሚረዱና ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉባቸው በርካታ ምንጮች (Sources) ሲኖሩ ከነዚህም መካከል፡-

- ሰነዶች (archives)
- ቅሪተ አካሎች (Fossils)
- የብራና ጽሑፎች (Inscriptions)
- ትውፊታዊ መረጃዎች (Traditional Sources)
- ድንጋይ ላይ ፅሁፎች (Inscriptions)
- ቤተ መቅደሶች (Temples)
- ሳንቲሞች (Coins)
- ጌጣጌጦች (Ornaments)
- አብያተ መንግስታት (Palaces) ወ.ዘ.ተ ይገኙባቸዋል፡

1.1.1. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ምንነት

የቤተክርስቲያን ታሪክ የክርስትና ሃይማኖት ታሪክ ነው በመሆኑም በዋናነት የሰው ልጅ ከአምላኩ ጋር ለዘመናት የነበረውን ግንኙነት ማዕከል ያደረገ የመንፈሳዊ ትምህርት ዘርፍ ነው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ቤተክርስቲያን ከተመሰረተችበት ዕለት ጀምሮ እስካለንበት ጊዜ ድረስ ያሳለፈችውንና የኖረችበትን የረጅም ዘመን እንቅስቃሴ ዳስሶ መንፈሳዊና ቁሳዊ ክንዋኔዎችን የሚያትት ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው፡፡

የቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት አንዲት ሐዋርያዊት ኦርቶዶክሳዊትና እውነት የሆነችውን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለይተን ከስር መሰረቷ እንድናውቃት የሚያግዝ ዓይነተኛ የዕውቀት መዝገብ ነው፡፡አለበለዚያ ‹‹የአገሩን ታሪክ የማያውቅ ሰው ከብዙ ሴቶች መካከል እናቱን ለይቶ የማያውቅ ልጅን ይመስላል፡፡›› እንደሚባለው ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በርካታ መሰናክሎችን አልፋ ለእኛ ዘመን እንድትደርስ የቅዱሳን አበው ተጋድሎና መሥዋዕትነት መዘከር ብቻ ሳይሆን አሠረፍኖታቸውን ተከትለን በምግባር እንድንመስላቸውና እኛም ቤተክርስቲያን በሚገባ ጠብቀን ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ በኩል የድርሻችንን እንድንወጣ የቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ የቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ታላቅ ፍቅርና መንፈሳዊ ቅናት እንዲኖረን፣ የእኔነት ስሜት እንድናዳብርና ተቆርቋሪዎች እንድንሆን በማድረግ በኩልም ታላቅ ድርሻ አለው፡፡

1.1.2. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ መረጃዎች ዐበይት ችግሮችና መፍትሔዎች

የታሪክ መረጃዎች አንድን ታሪክ ከቦታ ከዘመንና ከሌሎች ተዛማጅ ነገሮች ጋር በማገናዘብ ትክክለኛነቱን የሚረጋገጡ እማኞች /ምስክሮች/ ናቸው፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የኢትዮጵያን ህዝቦች የስልጣኔና የጥበብ አሻራ ሆኑ የበርካታ ቅርሶች ባለቤት ነች፡፡

ቅርስ ደግሞ የአንድ ህዝብ የዘመናት የኑሮ እንቅስቃሴ የሥራ እና የፈጠራ ክንውን መዘከር ስለሆነ ተፈጥሮንና አካባቢን በሚገባ ለመረዳት ለሚደረግ ጥናትና ምርምር መተኪያ የሌለው የመረጃ ምንጭ ነው ከቤተክርስቲያናችን ቅርሶችና የታሪክ መረጃዎች መካከልም፡-

- ውቅርና የዋሻ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት
- ያሬዳዊ ዜማ
- መካነ መቃብራት
- የማሕሌትና የቅዳሴ ስነሥርዓት
- ጥንታዊ ስዕሎች
- ንዋያተ ቅድሳት
- የብራናመጻሕፍት

- የነገስታት አልባሳት
- ቅዱሳት መካናት
- መንፈሳዊ በዓላት
- የአብነት ትምህርት ቤቶች...ወ.ዘ.ተ ናቸው

ከሁሉ አስቀድማ ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ተለይታ የራሷ ፊደል አጋዝ እና ዘመን አቆጣጠር እንዲኖራት ያስቻለች የትውልድ ባለውለታ ናት፡፡ እነዚህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ይዞታ ስር የሚገኙ የመረጃ ምንጭ እና ቅርሶቻችንን ለጥፋትና ለብልሽት ሚዳርጉ ዓይነተኛ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ተፈጥሯዊ ምክንያቶች

አየር ንብረት መለዋወጥ ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋዎች

- ሙቀትና ቅዝቃዜ
- የመሬት መንቀጥቀጥ
- ዝናብ
- ጎርፍ
- ርጥበት አዘል አየር
- የመሬትመንሸራተት
- ነፋስ
- መብረቅ
- የፀሐይ ጨረር
- ነጎድጓድ
- የዕድሜ መብዛት

2. ሰው ሰራሽ ምክንያቶች

- ዘረፋ
- ሌብነት
- የእሳት ቃጠሎ
- ንዝረት
- ኋላቀር የአያያዝ ዘዴ
- የንጽሕና ጉድለት
- ትኩረት መንፈግ
- የቦታ ጥበት
- የባለሙያ እጥረት
- በስጦታ መልክ ለሌሎች ማበርከት
- አግባብነት የሌለው እድሳት ናቸው

1.1.3. መፍትሔዎቻቸው

- ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ስለ ቅርሶችና መረጃዎቻችን ምንነት፣ ጠቀሜታ፣አያያዝና ዘዴ በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ ቅድሚያ መሰጠት ካለባቸው ጉዳዮች የመጀመሪያው ነው፡፡ በዚህም ሕብረተሰቡ ላይ፡-
  - የባለቤትነትና እና
  - የባለአደራነት ስሜት ማሳደር

- የመረጃ ምንጮቻችን በዓይነት፣ በቦታ፣ በይዘት፣ በእድሜ ….. ወዘተ መስፈርቶች መሰረት ተገቢውን ቆጠራና ምዝገባ ማካሄድ
- የመረጃ ማዕከላትን ማጠናከር፣ ባለሙያ ማሰልጠን፣ ዘመናዊ የማህደር፣ የምስል፣የድምፅ ክምችት ሥርዓት እና አገልግሎት መዘርጋት በዚህም፡-
  - መረጃዎቻችን በሚገባ ተለይተው እንዲታወቁ
  - ህጋዊ ጥበቃ እንዲደረግላቸውና
  - ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኙም ያስችላል፡፡

- እያንዳንዱ አጥቢያ ቤ/ክ (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ) እምቅ ክምችት ቅርስ ያለው በመሆኑ እንደ አካባቢያዊ ሙዚየምና ቤተ-መዛግብት ሊቆጠር የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም፡-
  - ብቃትና ጥራት ያላቸውን ዕቃ ቤቶችን ከማስፋፋትና ከመስራት ባሻገር የዕቃ ቤት ጠባቂዎችንም ከአመኔታ፣ ከዕድሜና ከጤና አኳያ በጥንቃቄ መርጦ መመደብ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ካህናት ቅርሶችና የመረጃ ምንጮች በመሆናቸው የኑሮ ደረጃቸው ቢሻሻል፣ በመንግስትም ሆነ በሕዝብ አስፈላጊው እንክብካቤና ድጋፍ ቢደረግላቸው የተሰጣቸውን ሃይማኖታዊ፣ አገራዊና ታሪካዊ አደራ በሚገባ እንደሚወጡ ጥርጥር ለውም፡፡

- በሰ/ት/ቤቶች በአብነት ት/ቤቶች እንዲሁም ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት የመረጃ ምንጮቻችንና ቅርሶቻችን ልንንከባከብ እንችላለን፡፡

1.1.4 ታሪክ በየመስኩ

ታሪክ በአጠቃላይ የሰውን ልጅ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሐይማኖታዊ አኗኗር የሚያሳውቅ የትምርት ዘርፍ ነው፡፡

ታሪክ በፖለቲካው ዘርፍ የሰው ልጆች የመሠረቱት የአስተዳደር አካላት መቼና እንዴት እንደተፈጠሩና በአስተዳደሩና በሕዝቡ መካከል ያላቸው ግንኙነቶች በዓለም ላይ ሰፋፊ

መንግስታት መፈጠራቸውና በእነርሱ መካከል በግዛት መስፋፋት ምክንያት የተነሱትን ጦርነቶች እንዲሁም ጦርነቶቹ ያስከተሉዋቸውን ጉዳቶች ከታሪክ እንማራለን ስለጥንታዊያን መንግስታት አነሳስና አወዳደቅ ምክንያት የምናውቀው ከታሪክ ትምህርት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ስለ ሰው ልጆች ቀደምት ባሕላዊና ሞራላዊ አስተሳሰቦች ጭምር የማምረቻ መሣሪያዎችን ዕድገትና ዓይነት ከየወቅቱ የሰው ልጆች ሥልጣኔ ጋር የምናውቀው ከታሪክ ነው፡፡

ታሪክ በኢኮኖሚው ዘርፍ፡- የሰው ልጅ በእርሻ መስክ ሰፊና የጠነከረ እንቅስቃሴ በማሳየትና በዚሁ ዘፍር የተግባር መገልገያ መሣሪያዎች ዕድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ ታይቷል፡ ፡ቀድሞ ከእንጨት የተሰሩ የእርሻ መሳሪያዎች ሲጠቀም ቆይቶ በኋላ ላይ በእንስሳት ጉልበት መጠቀም መቻሉን የሚያስረዳን ታሪክ ነው፡፡

ታሪክ በማህበራዊ ዘርፍ፡- የሰው ልጅ እርስበርስ በመተጋገዝ፣ በመከባበር፣ በመፈቃቀድ አንድ ላይ ይኖር እንደነበር ሲያሳውቀን በዚህም መስክ የሰው ልጅ በጋራ አደን ለመሄድ ያገኘውን በጋራ በመጠቀም ይኖር እንደነበር ታሪክ ያሳውቀናል፡፡

ታሪክ በሐይማኖታዊ ዘርፍ፡- የሰው ልጅ እምነቱ በአንድ እግዚአብሔር ብቻ እንደነበር በኋላ ግን በኃጢአቱ ምክንያት በትዕቢቱ፣ ዕውቀት ማጣቱ ወዘተ እምነቱን ሊያበዛው እንደቻ ለታሪክ ያሳውቀናል፡፡

1.1.5 ታሪክ ከአፈታሪክ የሚለየው እንዴት ነው?

- ✓ በመረጃ የተደገፈ በመሆኑ
- ✓ ሳይንሳዊ የጥናት ዘዴን ተከትሎ ስለሚጻፍ፡፡

1.1.6 ታሪክን እንዴት ማወቅ ይቻላል?

- ✓ በዕውቀት የበሰሉ ካህናት በዕድሜ የሚበልጡንን ሽማግሌዎች በመጠየቅ ዘዳ 32-7 « አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል ሽማግሌዎችን ጠይቅ ይነግሩህማል» ኢዮ 8-9 «ዘመናችን በምድር ላይ እንደ ጥላ ነውና እኛ የትናት ብቻ ነን ምንም አናውቅም ስለዚህ የቀደመውን ትውልድ ጠይቅ አባቶቻቸውን ለመረመሩት ነገር ትጋ እነርሱ የሚስተምሩህና የሚነግሩህ ቃልንም ከልባቸው የሚያወጡ አይደሉምን» ስለተባለ ከእነርሱም መጠየቅ

- ✓ ቅዱሳን አባቶች ጽፈው ያወረሱንን መንፈሳዊ መጽሐፍትን በማንበብ ትውፊታቸውን በመቀበል የታሪክ አባቶች የጻፉትን መጽሐፍ ማንበብ፡፡-መንፈሳዊ ጉባኤዎችን በመገኘትና ተከታትሎ በመማር፡፡

- ✓ ታሪካዊ ቦታዎችን ገዳማትን በመጎብኘት ወዘተ..

1.1.7 የታሪክ ምንጭ

ታሪክ ራሱን በቻለ ምንጭ ወይም መረጃ ላይ የተመሠረተ ትምህርት ነው በመረጃ ላይ ያልተመረኮዘ ጽሑፍ ታሪክ አይደለም በመሆኑም የታሪክ ጸሐፊዎች ታሪክን አዘጋጅተው ለሕብረተሰቡ ለማቅረብና በትምህርት ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ቀዳሞትና ዋነኛ ሥራቸው ለመጻፍ በሚፈልጉት የታሪክ ርዕስ ላይ የታሪክ መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናከር አለባቸው፡፡

የታሪክ መረጃ ትልቁና ዋንኛ ጥቅሙ፡- የነገሮችን፣የክስተቶችን እውነተኛነትና ሐሰተኛነትን በዝርዝር ለመለየትና ይህንንም በትክክል ለማሳወቅ ነው፡፡በአስተማማኝ መረጃና ምንጭ ላይ የተመሠረተና የተደገፈ ታሪክ ለነቀፌታና ለትችት አያጋልጥም፤ በአስተማሪነቱና በአሳዋቂነቱ በብዙ የታሪክ ምሁራን ድጋፍ ያገኛል በተጨማሪም ለሕብረተሰቡ ጠቃሚ ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ያስጨብጣል በዚህም መሠረት የታሪክ ምንጭ በሦስት ይከፈላል፤

፩ኛደረጃ፡- ቅዱሳት መጻሕፍት፣ አዋልድ መጻሕፍት፣ ገድላት፣ድርሳናት ወዘተ የታሪክ ምንጭ ናቸው፡፡

፪ኛደረጃ፡- የተለያዩ ቅርሶችና በሌሎች ስሞች የተጻፉ የታሪክ መጻሕፍቶች

ለምሳሌ ቅርሶች የታሪክ ምንጭ ናቸው እነዚህ ታሪኩ (ድርጊቱ) በተፈጸመበት ወቅት በጽሑፍ የሰፈረ እውነተኛ የታሪክ ምንጭ ነው፡፡በዚህ ወቅት የታሪኩ መዝጋቢ ይገኛል በዓይኑ ተመልካችና የድርጊቱ ተዋናይ ሊሆን ስለሚችል በአብዛኛው የታሪክ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነታቸው የበለጠ የጎላ ነው ለምን በአብዛኛው የታሪክ ወቅት የተሠሩ የተግባር መገልገያዎች ቅሬቶችም ስላለበት ነው እነዚህ ቅርሶች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡

ሰነዶች - የብራና ጽሑፎች - የድንጋይ ላይ ጽሑፎች - ድልድዮች

ሳንቲሞች - ሐውልቶች - ጌጣጌጦች - የጦር መሣሪያ

ቅሪት አካሎች - ማሕተሞች - የሸክላ ውጤቶች - ሞሽጎች

ቤተ መቅደሶች - የመቃብር ቦታዎች - ትውፊታዊ መረጃዎች - አብያተ መንግስታት ወዘተ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ የታሪክ መረጃዎች (ምንጮች) ናቸው

በሌሎች ሰዎች የተጻፉ የታሪክ ምንጮች፡- እነዚህ የታሪክ ምንጮች የተጻፉት ታሪኩ በተከናወነበት ጊዜ ሳይሆን ቆይተው የተጻፉ መረጃዎች (ምንጮች) በተለያዩ ሰዎች የተጻፉ የተዘገቡ የታሪክ ምንጮች ናቸው፡፡

፫ኛ ደረጃ አፈታሪክ (የቃልትውፊት) ለምሳሌ፡የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ መረጃዎች

ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የኢትዮጵያን ሕዝቦች የሥልጣኔና የጥበብ አሻራ የሆኑ የበርካታ ቅርሶች ባለቤት ነች፤ቅርስ ደግሞ የአንድ ሕዝብ የዘመናት የኑሮ እንቅስቃሴ የሥራና የፈጠራ ክንውን መዘክር ስለሆነ ተፈጥሮንና አካባቢን በሚገባበ መረዳት ለሚደረግ ጥናትና ምርምር መተኪያ የሌለው የመረጃ ምንጭ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በከፍተኛ የሥነጥበብ ዕውቀት የተራቀቁ በጽሕፈትና በድጉስት በሥዕልና በቅርጻ ቅርጽ በሥነ ህንጻና በተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች የላቀና የመጠቀ ችሎታ የነበራቸው ሊቃውንት በየዘርፉ ሰርተውና ጠብቀው ለትውልድ ያስተላለፏቸው የአያሌ አስደናቂ ቅርሶች ማህደር ነች፡፡በመሆኑም ቤተክርስቲያን የታሪክ ቁፋሮን ሐይማኖትን የሚነግሩ ታሪክን መረጃዎችና ቅርሶች የሚገኙባት ዓለም አቀፍ ሙዚየም ነች፡፡

ከእነዚህ የቤተክርስቲያን ቅርሶችና የታሪክ መረጃዎች መካከልም፤ውቅርና የዋሻ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት መካነ መቃብራት ጥንታዊ ሥዕሎች የብራና መጻሕፍት ቅዱሳት መካናት ያሬዳዊ ዜማ የማሕሌትና የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ንዋያተ ቅድሳት የነገሥታት አልባሳት መንፈሳዊ በዓላት የአብነት ትምህርት ቤቶች ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው ከሁሉ አስቀድማ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች በተለይ የራሷ ፊደል አሐዝና የዘመን አቆጣጠር እንዲኖራት ያስቻለች የትውልድ ባለውለታ ናት፡፡

1.2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ስያሜ

የዛሬዋ ኢትዮጵያ በጥንቱ ዘመን አጠራር

ከዛሬ 20 ዓመት በፊት በ1978 ዓ.ም ‹‹ኢትዮጵያ ›› የሚለው ቃል ‹‹ሱዳን›› በሚለው ተቀይሮ በአሜሪካ ሀገር አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞ መሰራጨት ሲጀምር የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ አስቸኳይ መልስ ሰጥቶበት ጉዳዩ በአጭሩ ተቀጭቷል፡፡እኚህ ሰዎች እንዲህ እንዲያደርጉ ያደፋፈራቸው አሁን ኢትዮጵያ ተብላ የምትታወቀው ሀገር ከዚህ በፊት በተለያዩ ስሞች የምትታወቀውን ኢትዮጵያ ማለት እንዳልሆነ ግምት ስላላቸው ነበር፡፡በመሆኑም ይህን ፈር የለቀቀ አመለካከት ማስተካከልና ስለሀገራችን ጥንታዊ ስያሜዎች ግንዛቤ ማስጨበጥ ለቤተክርስቲያኒቱ ታሪክ ጥናት መሰረታዊ ነገር መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በሌላ አገላለፅ ስለኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ታሪክ ስናነሳ ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለው ስያሜዋ መነሻችን ስለሆነ በቅድሚያ እንመለከተዋለን፡፡

1.2.1. ኢትዮጵያ በጥንት ግብጻውያን አጠራር

1. ጱንጥ

ይህን ስያሜ አስመልክቶ ሁለት ዓይነት አስተያየተቶች አለ፡፡ የመጀመሪያው ‹‹ጱንጥ›› የተባለው ስም ከአራቱ የካም ልጆች አንዱ ከሆነው ‹‹ፉጥ›› ጋር ይመሳሰላል

የሚለውነው፡፡በቅዱስ መጽሐፍም አራቱ የካም ወንድ ልጆች ስም ተጠቅሷል፡፡ እነዚህም ጽራይም፣ ኩሽ፣ከነዓንና ፉጥ ናቸው (ዘፍ.10) እዚህ ላይ ኢትዮጵያን ያቀፍት የካም ልጆች (ዘሮች) ናቸው የሚለው ትውፊታዊ ምስክርነት ስላለምን አልባትም በዚሁ ምክንያት አገሪቱ ጹንጥ የሚለውን ስያሜ ከካም ልጆች አንዱ በሆነው ፉጥ በሚለው አግኝታ ሊሆን ይችላል የሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል (ሁለተኛው) የጥንት ግብጻውያን የታሪክ መረጃዎች በአፍሪካ ቀንድ ‹‹ፑንት›› የሚባል ጥንታዊ መንግስት እንደነበር ያመለክታሉ፡፡ በርግጥ የዚህ ጥንታዊ መንግስት ትክክለኛው የግዛት ወሰን (ድንበር) የታወቀ ባይሆንም የዛሬዋ ኢትዮጵያ በዚህ ስር እንደምትጠቃለል መረጃዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ በጥንታዊያኑ ግብጾች የአጻጻፍ ዘዴ (ሂሮግራፊክስ) በፒራሚዶች ላይ የተጻፉ መረጃዎችም ግብጻውን ፈርኦኖች ውድና ብርቅ የሆኑ ዕቃዎችን ከ‹‹ፑንት›› ያገኙ እንደነበር ያመለክታሉ፡፡ በተለይም ዕጣን፣ የዝሆን ጥርስ፣ ወርቅ፣ከርቤና የአይን ኩል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡እነዚህ ነገሮችም በተለይ ከሌሎች በተሻለ በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡ ሌሎች መረጃዎችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

ሁሉንም ምንጮች ስንመረምር ‹‹ፑንት›› ተብሎ ይጠራ የነበረው የመንግስት ስሜ ግብጻውያን ‹‹ጹንጥ›› ብለው ከሚጠሩት ጋር ተመሳሳይ ሊሆን እንደሚችልና መሰረቱ የዛሬዋ ኢትዮጵያን መሬት አካባቢ ሊያካትት እንደሚችል ያመለክታል፡፡ከሚታወቁት ታሪካዊ ማስረጃዎች ሌላ በሁለቱም ሀገሮች (በግብጽና በኢትዮጵያ) በጋራ የሚታወቁ አንድ አንድ ባህላዊ ቁሶች ይህንኑ አሳባችንን የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ለምሳሌነትም የተወሰኑትን እንመለከታለን፡-

- ✓ የኢትዮጵያና የግብጽ ቆነጃጅት የሚጠቀሙበት የአይን ቅባት በሁለቱም ሀገር ሰዎች እስከ ዛሬ ድረስ በተመሳሳይ መጠሪያ ‹‹ኩል›› በመባል ይታወቃል፡፡
- ✓ በሀገራችን የምንጠቀምባቸው አንድ አንድ ጌጣጌጦች (ለምሳሌ አምባር፣ ጨሌ (ለመቁጠሪያ)... የግብጻውያኑ ተጽዕኖ ያለባቸው ናቸው፡፡
- ✓ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውለው ‹‹ዕጣን›› ጥንታውያን ግብጾች ለአምልኮት ይጠቀሙበት እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን አሁንም በሁለቱ ሀገሮች በተመሳሳይ መጠሪያ ‹‹ዕጣን›› ተብሎ ይታወቃል፡፡
- ✓ ጸናጽል፣ ዋሽንትና የመሳሰሉት የመዝሙር መሳሪዎች ጥንተ መሰረታቸው ግብጽ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡
- ✓ አሁን በዝዋይና በጣና ሐይቆች አካባቢ የሚያገለግሉ ጀልባዎች ከጥንት ግብጻውያን ጀልባዎች ጋር በጣም ይመሳሰላሉ፡፡

2. ቶ-ኔቶር

ትርጉሙ ‹‹የአምላክ ሀገር›› ማለት ነው፡፡ግብጻውያን የዛሬዋን ኢትዮጵያ በዚህ ስያሜ መጥራታቸው በሁለት ዓበይት ምክንያቶች ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው ለግብጻውያን የስልጣኔ መሠረትና የኑሮ ዋስትና የሆነው የናይል (ዓባይ) ወንዝ መነሻ ስለሆነች ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጥንታውያን ግብጾች ለአማልክቶቻቸው የሚቀርቡት ዕጣንና ሌሎች ውድ የሆኑ ሽቶዎችን ከኢትዮጵያ ያገኙ ስለነበር ነው፡፡

3. ኩሽ ምድር

ይህ ስያሜ ግብጾች ከአገራቸው በስተደቡብ ያለውን ሰፊ ቦታ የሚያውቁበት ሌላኛው መጠሪያ ነው።።ሊቀ ነብያት ሙሴም ብሉይ ኪዳንን ሲጽፍ ኢትዮጵያን የኩሽ ምድር እያለ መግለጹ በግብጽ ምድር ተወልዶ ያደገና የግብጻውያንን ባህልና ቋንቋ ያውቅ ስለነበር ነው።።የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ደግሞ ኢትዮጵያ የኩሽ ምድር ተብላ ስትጠራ የነበረችበት ምክንያት የካም የመጀመሪያ ልጁ የኩሽ ዘሮች ስለሰፈሩባት እንደሆነ ይገለጻሉ (ዘፍ.10)።።ከጌታ ልደት በፊት በ284 ዓመት ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ (ፅርዕ) የተረጎሙት ሰባው ሊቃውንትም ሙሴ ‹‹ኩሽ›› እያለ የጻፈውን ‹‹ኢትዮጵያ›› በሚል ቃል የተኩትም በዚህ ምክንያት ነው።።አስቀድሞ እንደተገለጸው አንድ አንድ ሰዎች ጥንታውያን ግብጾች ‹‹ኩሽ›› በማለት የሚጠሩትን አካባቢ የዛሬዋን ሱዳን በማለት ይገልጻሉ።።ሆኖም ግን ይህ አባባል ለማን እንደሆነ ሊቀ ነብያት ሙሴ ከጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መረዳት እንችላለን።። በቅዱስ መጽሐፍ ‹‹የሁለተኛው ወንዝስም ግዮን ነው፤እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል›› (ዘፍ 2÷13) በማለት ተጽፏል።። በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ግዮን›› ተብሎ የተጠራው ‹‹የዓባይ›› ወንዝ ደግሞ የሚከበው በዛሬዋ ኢትዮጵያ የሚገኙ አካባቢዎችን እንጂ ሱዳንን እንዳልሆነ ግልጽ ነው።።

1.2.2. ኢትዮጵያ በጥንት ግሪካውያን አጠራር

ጥንት ግሪካውያን ለአውሮፓ ሥልጣኔ የመጀመሪያ ሕዝቦች ናቸው።።ከሁሉም በላይ በጥንታዊ ፍልስፍናቸው የሚታወቁት ግሪካውያን ግዛታቸውን በማስፋት በታላቁ እስክንድር ዘመነ መንግስት ሰሜን አፍሪካን ሳይቀር ተቆጣጥረዋል።።ግሪካውያን በታላቁ እስክንድር ስያሜ የወጣላትን የግብጽ ከተማ (እስክንድሪያን) ማዕከል በማድረግ ሲኖሩ ከግብጻውያን ጋር የባህልና የንግድ ልውውጥ ከነበራቸው ሌሎች ጥንታውን ሕዝቦች ጋር ለመተዋወቅ አጋጣሚ ተፈጥሮላቸዋል።።በዚህ ወቅት ግሪካውያን የአፍሪካን አህጉር የሚያውቁ በሁለት ስያሜዎች ነበር።።ይኸውም ከግብጽ በስተምዕራብ የሚገኘውን የአፍሪካ ሰሜናዊ ክፍል ሊቢያ በማለት ሲጠሩት ሁለተኛውን ደግሞ ከግብጽ በስተደቡብ ያለውን አጠቃላይ የምስራቅ አፍሪካ ክፍል ‹‹ኢትዮጵያ›› በማለት ያውቁት ነበር።።

‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለውን ስያሜ በመጠቀም ጥንታውያን ግሪኮች የመጀመሪያዎቹ እንደሆኑ መረጃዎች ሲጠቁሙ ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለው ቃልም በቀጥታ የሁለት ግሪክኛ ቃላት ጥምር እንደሆነ ይታመናል።። እነዚህም ቃላት፡-

‹‹አይቶ›› - ጥቁር ወይም ጠይም አደረገ

‹‹ኦጵስ›› - ፊት የሚሉት ናቸው።።

በጥቅሉ ኢትዮጵያ ማለት ለጥንት ግሪካውያን ፊታቸውን ፀሐይ ያቃጠለው (Burned Faces) ወይም ጠያይም መልክ ያላቸው ሰዎች ሀገር እንደ ማለት ነው።።ከዚህ በመነሳት

ሀገሪቱን ‹‹ኢትዮጵያ›› ያሰኛት የሕዝቡ (የነዋሪዎቿ) መልክ ጠይምነት ነው የሚለውን አስተሳሰብ ብዙዎቹ ይደግፋሉ፡፡

‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለውን የሀገራችን መጠሪያ ሁለት ታላላቅ የግሪክ ጸሐፊዎች በድርሰቶቻቸው ገልጸውታል፡፡ የመጀመሪያው ‹‹ኦልያድና ኦዲሴ›› በሚባሉ የቅኔ ድርሰቶቹ የሚታወቀው ሆሜር ነው፡፡ታዋቂው ሆሜር ኢትዮጵያን ኦልያድ በተባለው ድርሰቱ ሁለት ጊዜ ኦዲሴ በተባለው ድርሰቱ ደግሞ ሦስት ጊዜ ጠቅሷታል፡፡ለምሳሌ ኦልድያ በተባለው ቅኔው ቁጥር 432 ላይ ሆሜር የኢትዮጵያን ሕዝቦች ሲገልጽ ‹‹የኢትዮጵያ ሰዎች በጉልበት ኃያላን፣ በውበት የተደነቁና በጠባይ ጭምቶች፤ ትህትናን የተሞሉ ናቸው፡፡›› በማለት ነበር፡፡

ስለኢትዮጵያ የተናገረው ሌላኛው ታዋቂ ግሪካዊ ጸሐፊ ሄርደተስ ነው፡፡ሄሮደተስ ከጌታ ልደት በፊት በ490 ዓ.ዓ ገደማ የነበረ የታሪክ አባት (Father of History) በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ሄሮዱተስ በሦስተኛው መጽሐፉ ‹‹ኢትዮጵያውያን ከሰዎች ሁሉ በውበትና በቁመት የሚበልጡ ኃያላን ናቸው፡፡›› በማለት ገልጿቸዋል፡፡ይኸንንም ለመፃፍ ያስቻለው በግብጽ ከኢትዮጵውያን ጋር ለብዙ ጊዜያት ባደረገ ውውይይት መሆኑን ገልጿል፡፡

እንግዲህ የጥንት ግሪካውያን ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለውን ስያሜ ለዚህች ሀገር የሰጡት የነዋሪዎቹን መልክ ጠይምነት (መልክ መልካምነት) ለመግለጽ እንደሆነ ሲገመት ታዋቂዎቹ የግሪክ ፀሐፊዎች ሆሜርና ሄሮደተስም ይህንኑ አጉልተውና አድንቀው ጽፈዋል፡ ይኸውም ለጥንት ግሪካውያን እንግዳ የሆነ ነገር የራሱ ምክንያት እንደሚኖረው መገመት ይቻላል፡፡ ቀለምን ተከትሎ የሰው ዘር - ኮኬዥያን (ነጭ)፣ ኔግሮይድ (ጥቁር)፣ እና ሞንጎሎይድ (ቢጫ-ቀይ) ተብሎ ይጠራል፡፡ኢትዮጵያውያን ግን ከዚህ ውጪ መሆናቸውን መለየት ለማንም አያዳግትም፡፡ይህም የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ የመጀመሪያ አቅኚዎች የኖኅ ልጅ የካም ነገዶች (ኔግሮድ) እንደሆኑ ቢገመትም በኋላ ላይ በተለየ ምክንያት የሴም ነገዶች (ሞንጎሎይድ) ወደ ሀገራችን ገብተው በመዳቀላቸው ነው ይባላል፡፡ ስለሆነም የካም (ኔግሮይድ) እና የሴም (ሞንጎሎይድ) ነገዶች ውህደት መልክ ጠይምነትን እንዳመጣ ይገመታል፡፡ ዓረቦችም የኢትዮጵያውያንን የተለየ መልክ (መልክ ጠይምነት) በመገንዘብ ሳይሆን አይቀርም ‹‹ሐበሻ›› (ድብልቅ) የሚለውን መጠሪያ ሲጠቀሙበት የምንመለከትበት፡፡

ከግሪክኛ ቋንቋ እንደተወሰደ ከሚገመተውና ታዋቂዎቹ የግሪክ ጸሐፊዎች ከጠቀሱት አመለካከት ባሻገር አገራችን ‹‹ኢትዮጵያ›› ተብላ ለመሰየሟ ሌሎች ሁለት ትውፊታዊ ግምቶች አሉ፡፡የመጀመሪያው የካም ልጅ ኩሽ በሚባል ሌላኛ ስሙ ይታወቅ ነበር ስለሆነም ኢትዮጵስ በሚለው ስሙ የአገሪቱ አቅኚዎች አገሪቱን ኢትዮጵያ በሚለው ስያሜ መጥራት ጀመሩ የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከክ/ል/በከነበሩት በርካታ ነገስታት መካከል ‹‹ኢትዮጵስ›› የሚባል ንጉስ ስለነበር አገራችንም የዛሬዋን ስያሜዋ ከዚህ ንጉሥ በኢትዮጵስ ኢትዮጵያ የሚል ስያሜን አግኝታለች (በእርሱ ስም ተጠርታለች)።

1.2.3. የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሌሎች መጠሪያዎች

1. አቢሲኒያ እና የሳባ ምድር ‹‹አቢስ›› እና ‹‹ሳባ›› ከሚባሉት ሁለት የኩሽ ልጆች የተወሰዱ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን ያቀናው የካም ልጅ ኩሽ ‹‹አቢስ›› እና ‹‹ሳባ›› የሚባሉ ልጆች ስለነበሩት የእነርሱን ስም በመውሰድ ኢትዮጵያ በአቢስ አቢሲኒያ በሳባ ደግሞ የሳባ ምድር ተብላ መጠራት ጀመረች ይባላል፡፡

2. ብሔረ አግዓዚያን ይህን ስያሜ ያገኘችው ከደቡብ ዐረቢያ ፈልሰው እንደመጡ በሚነገርላቸው ነገደ አግዓዚያን በተባሉ የሴም ዘሮች እንደሆነ ይነገራል፡፡አግዓዚያን ቋንቋቸው ጥንታዊ ‹‹ግዕዝ›› እንደነበር ሲነገር ‹‹አግዓዚያን›› የሚለው ስምም የተሰጣቸው ስለሁለት ምክንያቶች ነው፡፡የመጀመሪያው እነዚህ የሴም ነገዶች ወደ ሀገራችን ከመግባታቸው በፊት ብራህማ የተባለ የህንድ ንጉስ የኩሽ ነገዶችን ድል በማድረግ ኢትጵያን በወረራ ይዞ ነበር በኋላ ግን እነዚህ የሴም ነገዶች ኢትዮጵያን የወረረውን የሕንድ ንጉሥ ድል አድርገው ሀገሪቱን ነጻ አድርገዋታል የሚል ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ነገዶቹን ‹‹ነፃ አውጪዎች›› ለማለት በግዕዝ ቋንቋ ‹‹አግዓዝያን›› የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል ይባላል፡፡ ሀገሪቱም (ኢትዮጵያ) ‹‹ብሔረ አግዓዝያን›› ተብላ መጠራት ጀመረች፤ በግዕዝ ቋንቋ ‹‹አግዓዘ›› ማለት ነጻ አወጣ ማለት ነውና፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ‹‹ግዕዘ›› የሚለው የግዕዝ ቃል ትርጉሙ ‹‹ተጓዘ›› ማለት ሲሆን በዚህ መሰረት እነዚህ ነገዶች ከደቡብ ዓረቢያ ተጉዘው ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን ለመግለጽ ‹‹ተጉዘው መጡ›› በማለት ፊንታ ‹‹አግዓዚያን›› ተብለዋል የሚለው ነው፡፡

3. ምድረሐበሻ፡- የሚለው ደግሞ አስቀድሞ እንደተገለጸው ዓረቦች የቀይዳማነት ማዕከል ያደረገው የተለያየ የኢትዮጵያን መልክ (ቀለም) በመውሰድ ድብልቅ ለማለት የተጠቀሙበትን ‹‹ሐበሻ›› የሚለውን ቃል በመውሰድ ነው፡፡

4. ጡብያ: ጹብያህ፣ ጹብያ፣ ጦቢያ፣ እጦቢያ፣ ኢትዮጵያ፣ የህያው ቅዱሳን ማለት ነው። አኪጦብ፣ ጦብ፣ ጦባዶንያ ‘ጹብ’ እና ‘ያህ’ (ያህዌ፣ ህያው) ከሚሉ ሁለት ቃላት የተመሠረተ ስም ነው።

ጦብያ የባቢሎንም ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ባቢሎን ከማረካቸው ምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ወደእየከተማቸው ከተመለሱ፥ “የዳላያ ልጆች፥ የጦብያ ልጆች፥ የኔ ቆዳ ልጆች፥ ስድስት መቶ አርባ ሁለት።” (ነህ 7:62)

ጦብያ በንጉሥ ኢዮሳፍጥ ዘመን የእግዚአብሔርን የሕጉን መጽሐፍ ይዘው በይሁዳ ያስተምሩ ከነበር፥ (2 ዜና 17:8 ፣ 2 ዜና 17:8)

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስያሜ ትርጉምና ትርጓሜ

ኦርቶዶክስ (Orthodox)

“ኦርቶዶክስ” የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን የተቀናበረው “ኦርቶ” እና “ዶክስ” ከሚሉት ሁለት ቃላት ነው፡፡ ትርጉማቸውም ኦርቶ ማለት ቀጥተኛ: ትክክለኛ ማለት ሲሆን ዶክስ ማለት ደግሞ እምነት/ሃይማኖት ማለት ነው፡፡ በአንድነት ሲሆኑ ኦርቶዶክስ ማለት ቀጥተኛ፡ ትክክለኛ እምነት/ሃይማኖት ማለት ነው፡፡ኦርቶዶክስ የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋለው በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባዔ ነው፡፡ በኒቅያ “ወልድ ፍጡር ነው” የሚለውን የአርዮስን የክህደት ትምህርት ለማውገዝና ሃይማኖታቸውን ለማፅናት የተሰበሰቡ ሃይማኖታቸው የቀና 318ቱ ሊቃውንት ይህን ቃል የተጠቀሙት ሐዋርያት ያስተማሯት ሃይማኖት ቀጥተኛና ትክክለኛ ናት ለማለት ነው፡፡ሌሎች እንደ አርዮስ ክህደት ያሉት በየዘመኑ የሚነሱት ልዩ ልዩ አዳዲስ ትምህርቶች የምንፍቅና መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይህችን ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ብለዋታል፡፡በዘመናችን የቋንቋ አጠቃቀምም ኦርቶዶክሳዊ መንገድ (orthodox) ማለት ቀጥተኛ (የተለመደ የታወቀ) የችግር አፈታት ሲሆን ኢ-ኦርቶዶክሳዊ (unorthodox) ማለት ደግሞ ከተለመደው ከታወቀው ወጣ ያለ የችግር አፈታት ማለት ነው፡፡ከዚህ ውጭ ይህን ቃል አንዳንዶች ግትርነትን ወይም ለለውጥ ያልተዘጋጀ የሚለውን ለመግለፅም ሲጠቀሙበት ይታያል፡፡ይህ ግን በሂደት የመጣ የትርጉም መዛባት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ተዋሕዶ (Miaphysite)

ተዋሕዶ የሚለው ቃል ከልሣነ ግእዝ የመነጨ ቃል ነው፡፡ ትርጉሙም “አንድ ሆኖ” ማለት ነው። በዚህ ትርጉም ውስጥ አንድ የሆኑት መለኮታዊና ሰብዓዊ ባሕርይ (መለኮትና ትስብዕት) ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የተዋሕዶ ትርጓሜ በአጭሩ “ወልድ ዋሕድ” የሚለው ነው፡፡ ክርስቶስ ሰው የሆነው ያለሚጠት (ያለመመለስ)፣ ያለውላጤ (ያለመለወጥ)፣ ያለቱሳኤ (ያለመቀላቀል)፣ ያለትድምርት (ያለመደመር)፣ ያለቡዓዴ (ያለመለያየት)፣ ያለኀድረት (ያለማደር) ነው፡፡ ክርስቶስ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ፣ከሁለት አካል አንድ አካል የሆነው በተዋህዶ ነው፡፡ስለዚህ ተዋሕዶ የሚለው ቃል ክርስቶስ ሰው የሆነበትን ምስጢር የሚገልፅ ታላቅ ቃል ነው፡፡ክርስቶስ ሰው የሆነው በተዋሕዶ ነው! የተዋህዶ ምሳሌዎች (Examples of Miaphysite)

- ✓ የነፍስና የሥጋ ተዋህዶ፡- ነፍስና ሥጋ ተዋህደው አንድ ሰው ይባላል እንጂ ሁለት አይባልም፡፡
- ✓ የብረትና የእሳት ተዋህዶ፡- ብረት በእሳት ሲግል የጋለ ብረት እንጂ ይህ ብረት ነው፣ ይህ ደግሞ እሳት ነው ተብሎ አይለይም፡፡
- ✓ የሲና ሐመልማል፡- እሳቱ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው፣ሐመልማሉም እሳቱን ሳያጠፋው በአንድነት (በተዐቅቦ) መታየታቸው የተዋህዶ ምሳሌ ነው (ዘፀ 3፡2)፡፡

ይህንን አስተምህሮ የተቀበሉት (Miaphysite churches)

የተዋህዶን (Miaphysite) **አስተምህሮ የተቀበሉት ኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ይባለሉ፡፡ እነዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን** (Ethiopian Orthodox Tewahedo Church)፡ **የኤርትራ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን** (Eritrean Orthodox Tewahedo Church)፡ **የግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን** (Coptic Orthodox church)፡ **የአርመንያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን** (Armenian Orthodox Church)፡**የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና** (Syrian Orthodox Church) **የህንድ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን** (Indian Orthodox church) **ናቸው፡፡እነዚህ ጉባዔ ኬልቄዶንን የማይቀበሉ የምሥራቅ ኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት በዶግማቸው አንድ ናቸው፡፡አንዳንድ ወገኖች "ኦርቶዶክስ የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም::" ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ነገር ግን በትንቢት "በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ለነፍሳችሁ ምዕረፍት ታገኛላችሁ፤ እነርሱ ግን። አንሄድባትም አሉ** (ኤር 6፡16)።" **ይላል፡፡ በአዲስ ኪዳንም "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው** (ዕብ 13፡8)።" **ይህ የሚያሳየው አንዲት ቀጥተኛ መንገድ/ሃይማኖት እንዳለች ነው፡፡**

ምእራፍ ሁለት

2.የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን በቅድመ ክርስትና

2.1 የኢትዮጵያ እምነት በሕገ ልቡና ዘመን

ኢትዮጵያ ያለ ሃይማኖት (ያለ አምልኮተ እግዚአብሔር) የኖረችበት ጊዜ እንዳል ነበር መጽሐፍ ቅዱስና ትውፊታዊ ማስረጃዎች ተባብረው ይመሰክራሉ፡፡ በሦስቱ ሕግጋት ውስጥ (በሕገልቡና፣ በሕገኦሪትና፣ በሕገወንጌል) ኢትዮጵያ ከአምልኮተ እግዚአብሔር እንዳልተለየች ይታወቃል፡፡

ሕገልቡና ለሰው በጥንተ ተፈጥሮ ከልዑል እግዚአብሔር የተሰጠው የመጀመሪያው ሕግ ነው፡፡ ይህ ዘመን ከአዳም እስከ ሙሴ ያለውን አራት ሺህ ዘመን ያጠቃልላል፡፡በዚህ ዘመን ሌላው ዓለም (ከእስራኤላውያን በስተቀር) በአምልኮተ ጣዖት ውስጥ በሚባዝንበት ዘመን የኖኅ የልጅ ልጆች የአባታቸውን እምነት ወደ ኢትዮጵ ይዘው በመግባታቸው አገራችን በአምልኮተ እግዚአብሔር ልትታወቅ ችላለች፡፡በጥፋት ውኃ ዘመን ከስምንት ቤተሰቦቹ ጋር በመርከብ አማካኝነት ከሞት ተረፈው ጻድቁ ኖኅ ሴም፣ካምና ያፌት የሚባሉ ሦስት ልጆች እንደነበሩት ይታወቃል፡፡ከሦስቱ ልጆቹም ወደ አፍሪካ ምድር የመጣውና ለልጆቹ ኢትዮጵያን ያቀናው ካም እንደነበር ትውፊታዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡በሕገ ልቡና ዘመን አምልኮተ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ እንደነበር ከሚያመላክቱ ማስረጃዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

2.1.1. ሄኖክ

የአዳም ሰባተኛ ትውልድ ነው ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ተብሎ የተጻፈለት በደብር ቅዱስ ከገነት አቅራቢያ የሚኖር ነበር ሰባት ልጆችንም ወልዷል ዘፍ፭፥፪፪ መጽሐፍ ቅዱስ ገነትን ከሚያጠጡ ወንዞች ዘፍ፪÷፲፫፡- ‹‹የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ይከባል፡፡›› ይሁዳ መልእክት ፩፥፲፬ ስለሄኖክ የጻፈው መልክት መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ በሚገኘው ለዛውም በግእዝ ብቻ ተጽፎ ሲገኝ በአባቶች አስተምሮ ይህም መሰረት በማድረግ ሄኖክ ገነትን በሚያጠጣው በግዮን ወንዝ ዙሪያ ይኖር ነበር ብለው ያስተምራሉ።

2.1.2. መልከጼዲቅ

ዘፍ፲፬ አብርሃምን የባረከው እንዲሁም ልዩ ካህን ምንም እንኳን እናትና አባት የለውም ተብሎ ቢጠቀስም የሐዲስ ኪዳን ሊቀካህን ተብሎ ለጌታችን ክህነት ምሳሌ ሲሆን ዕብ፯፥፩ የሳሌም ንጉስ ተብሎ ቢጠቀስም ሳሌም የተባለችው የኢትዮጵያውያን የመጀመሪያ

ከተማ ነች ብለው የስነ መለኮትና የፊሎሎጂ ምሁራኑ ይናገራሉ እንዲሁም ከክህነቱ ከመስዋእቱ እንዲሁም ከስሙ በመነሳት የኢትዮጵያውያን አባት ነው ብለው ይናገራሉ።

መልከጼዲቅ የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የእውነት ገላጭ ተብሎ ይተረጎማል ይህም ስሙ በተለያየ ቋንቋ ቢጠራም የስሙ መጠሪያ የግእዝ ቋንቋ መሰረትነት አለው።

2.1.3. ዮቶር ራጉኤል

ይህ ሰው ከሄኖክ ጀምሮ የአብርሃምን ሙሉ ታሪክና ከአባቶቹ የተቀበለውን ትውፊት እንዲሁም በብርሃና ላይ እየከተበ ያስቀመጠ ሰው ነውዘጸ፲፰፥፩ ፍጻሜው

የምድያም ካህን ነው ይህ ሰው ክህነቱ ተገልጦ ሲገኝ ይህንን ክህነቱን ሲወርድ ሲዋረድ ያገኘው ከነመልከጼዲቅ ነው ይህም ሰው እንደ መልከጼዲቅ መስዋትን ለእግዚአብሔር የሚሰዋ ነበር

ሙሴ ከፈርኦን ሸሽቶ ከግብጽ ሲመጣ የተቀበለው ይህ ሰው ነው የሙሴን ብልህነትና ቀልጣፋነት ተመልክቶ ሴት ልጁን ሲጳራን ድሮለት ነበር

ህዝበ እስራኤል ከባርነት እንዲወጡ ለሙሴ ያስተማረው ይህ ሰውነበር ከዚህም በተጨማሪ የዳኝነትን እንዲሁም የአመራርን ስርአት ያሳየው ዮቶር ነበር

ዮቶር ለሙሴ ህግን ፍርድን በጥልቅት አሳይቶት ነበር ይህንንም ሙሴ ከላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ክፍል ገልጦታል።

2.1.4. ሲጳራ

ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሲጳራ ሙሴን ያስተማረው የዮቶር ልጅ ናት “ሙሴም ኢትዮጵዊቷን አግብቷልና ባገባት በኢትዮጵያዊቷ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተነጋገሩ” ዘፍ፲፪÷፩፡- ይላል።ከዚህ ጥቅስ መረዳት የሚቻለው እስራኤላውያን በሕጋቸው ከአረማውያን (በእግዚአብሔር ከማያምኑ ሰዎች) ጋር መጋባት ክልክል ስለ ነበር ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን በማግባቱ የተሳሳተ ስለመሰላቸው ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም ወንድማቸውን በማማታቸው መጎዳታቸውን ነው።ሙሴ በሰው ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር የተመሰከረለት ታላቅ ነቢይ ነው።ስለሆነም ሕግ መተላለፍ ሳይሆን ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ያገባው በሕገልቡና በአምልኮተ እግዚአብሔር ስለምትመስለው ነው።

2.2. የኢትዮጵያ እምነት በሕገ ኦሪት ዘመን

ትውፊትን መሰረት ያደረገው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲን የታሪክ ሂደት ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገችው ጉዞ በአገራችን የብሉይ ኪዳን እምነትና የሕገ ኦሪት ሥርዓት እንዲገባ መሰረታዊ ምክንያት መሆኑን ያትታል።የንግሥተ ሳባ ጉዞ ደግሞ በቅዱስ መጽሐፍ በመጀመሪያው መጽሐፈ-ነገሥት የተመዘገበው ነው።ሆኖም ግን ከንግሥተ ሳባ

ማንነትና ታሪክ ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ በብዙዎች የሚነሡ ሁለት አወዛጋቢ ጉዳዮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ዐረቦችና ኢትዮጵያውያን ሁለቱም ንግስቷን ‹‹የእኛ ናት›› በማለት የሚያሰሙት ክርክር ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ከንግስተ ሳባና ከንጉሥ ሰለሞን ጋር ተያይዞ በሀገራችን የሚተረከው ነገር እውነት ወይስ ተረት ተረት (Legend) ነው የሚለው ነው፡፡ስለዚህ ወደ ሌሎች ጉዳዮች ከመግባታችን በፊት እነዚህን ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች እናብራራለን፡፡

2.2.1. ንግስተ ሳባ ኢትዮጵያዊት ወይስ ዐረባዊት (የመናዊት)

መጽሐፍ ቅዱስ የንግሥቷን ስም ሳይጠቅስ በጻፈው ‹‹የሳባ ንግስት (ንግስተ ሳባ)›› በማለት ታሪካዊ የኢየሩሳሌም ጉዞ ዋና ከንጉስ ሰለሞን ጋር ያደረገችውን ግንኙነት በዝርዝር ያትታል፡፡

ዐረቦች ደግሞ ከእስልምና በፊት በየመን አካባቢ (ደቡብ አረቢያ) ‹‹ሳባ›› (Sheba) የሚባል መንግስት እንደነበር ስለሚነገር ንግስቷን የእኛነች በማለት ይከራከራሉ፡፡ሌሎች በርካታ ትውፊታዊ መረጃዎች ደግሚ ንግስቷ የኢትዮጵ ንግስት ሆና ሳለ ንግስተ ሳባ (የሳባ ምድር)›› ተብላ በቅዱስ መጽሐፍ መጠቀሷ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል፡፡

የመጀመሪያው አስቀድሞ እንደተገለጸው በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ ‹‹የሳባ ምድር›› ተብላ ትጠራ ነበር፡፡ለዚህም ምክንያቱ ኢትዮጵያንያ ቀኗት የኖኅ የልጅ ልጅ የኩሽ ዘሮች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው ሳባ ደግሞ የኩሽ የመጀመሪያ ልጁ ስም ነው (ዘፍ10)፡፡ስለዚህ ኢትዮጵያ በአቅኝዋ በሳባ የሳባ ምድር ተብላ መጠራት ጀመረች፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ ንግሳቷን-ንግሥተ ሳባ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ማስፈሩ ንግሥት መሆኗን የሚያመለክት ነው የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ከጌታችን ልደት በፊት በአንድ ሺ ዓመተ ዓለም ገደማ ከደቡብ ዓረሚያ (ከየመን አካባቢ) ፈልሰው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የሴም ዘሮች እንደነበሩ ታሪክ ያስረዳል፡ ፡እነዚህ የሴም ዘሮች ብዙዎቹ ሳባ ተብሎ ይጠራ የነበረው የየመን ክፍል እንደመጡ ይታወቃል፡፡ እነዚህ መጻተኛ ሴማውያን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በአገሪቱ ቀድመው ከነበሩት የካም (የኩሽ) ዘሮች ጋር በመቀላቀል በባህል፣ በኢኮኖሚ፣በማሕበራዊ ሕይወትና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ ለውጦች እንዲፈጠሩ አድርገዋል፡፡የሳባን ቋንቋ ለኢትዮጵያ ያስተዋወቁትም እነሱ ናቸው፡፡የሳባ ቋንቋ ከግእዝ በፊት ኢትዮጵውያን ይጠቀሙበት እንደነበር እስከዛሬ ድረስ በአገራችን ከሚገኙ በርካታ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች (Inscription) መረዳት ይቻላል፡፡ እንግዲህ ‹‹በእነዚህ ከሳባ (የመን) አካባቢ መጥተው በኢትዮጵ ምድር በሰፈሩ ሴማውያንና በሳባ ቋንቋ ምክንያት ንግስቷም ንግሥተ ሳባ ተብላ ልትጠራ ችላለች›› የሚለው ሌላኛው አስተያየት ነው፡፡

ሦስተኛው ታሪኩ የተፈጸመበት ዘመን የኢትዮጵያ ግዛት በጣም ሰፊ ሆኖ እስከ ደቡብ ዓረቢያ ድረስ ዘልቆ የየመንን ግዛቶች ሳባንና ሌሎችን ያጠቃልል ስለነበር

ንግሥቷን መጽሐፍ ቅዱስ ንግሥተ ሳባ ብሎ የጠራት ሳባ የተባለው ቦታ ራሱ የኢትዮጵያ ግዛት ስለ ነበር ነው፡፡ለምሳሌ ንጉሥ ኢዛና ክርስትናን ከመቀበሉ በፊትም ሆነ በኋላ በሐውልቱ ላይ የጻፈው ጽሁፍ (Ezana Inscription) ከምንለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

“Ezana... King of Aksum, and of Himyar and of Raydan and of saba, and of Salhen, and of Seyamo, and of Kassu, king of kings....” ትርጉሙም፡-

“ኢዛና... የአክሱም ንጉሥ፣ የሂምያር፣ የረይዳን፣ የሳባ፣ የሳልሂን፣ የሲያም፣የቤጃ እና የካሱ ንጉሠ ነገሥታት...” የሚልነው፡፡ ከእነዚህ ቦታዎች (ግዛቶች) መካከል አንዳንዶቹ በደቡብ ዐረቢያ (የመን) አካባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡ ሳባ ምድር ደቡብ አረቢያ በንጉስ ኢዛና ሥር ከነበሩ ግዛቶች ውስጥ አንዷ በመሆኗ ኢዛና “የሳባ ንጉሥ” (kings of Saba) ተብሎ እንደተገለጸ እንመለከታለን፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ንግሥቷ ንግሥተ ሳባ (Queen of Sheba) ተብላ መጠራቷም ዓረባዊ ትሁና ሳይሆን የአካባቢ ግዛቷ ስለነበር ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡ በተጨማሪም ምን አልባት ንግሥቷ የሰለሞንን ጥበብ ለመረዳት ከኢትዮጵያ ተነስታ በግዛቷ በሳባ በኩል አድርጋ ወደ ኢየሩሳሌም ስለተጓዘች ሳባ ተብላ ልትታወቅ ችላ ይሆናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የንግሥቷን ስም ባይጠቅሰውም በኢትዮጵያውያን ትውፊታዊ መረጃዎች መሠረት ማክዳ በመባል ትታወቃለች፡፡ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ንግሥተ አዜብበ ማለት ይጠራታል፡፡ ንግሥተ አዜብ ማለትም የደቡብ ንግሥት ማለት ነው፡፡ ‹‹ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነስታ ትፈርድበታለች፡፡የሰለሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፤ እነሆ ምክ ሰለሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ፡፡›› ማቴ 12÷42 እስከ አሁን ድረስ ከክ/ል/በፊት በ900 ዓመት ገደማ ከኢትዮጵያ ተነስታ የሰለሞንን ጥበብ ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ስለተጓዘች ንግስት መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ንግስተ ሳባ እንዳላት ለማየት ሞክረናል፡፡ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት ንግሥት ስለመሆኗ የሚያስረግጡ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ማቅረብና ከንግሥት ሳባና ከንጉሥ ሰለሞን ጋር ተያይዞ የሚነገረው ተራ አፈታሪክ አለመሆኑን ለመግለጽ እንሞክራለን፡

ሀ) የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት፡-

አስቀድሞ እንደተገለጸው ቅዱሳት መጻሕፍት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በዓበይትነት የሚጠቀሡ የታሪክ መረጃዎች ናቸው፡፡የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ራሱ ዋነኛው የቤተክርስቲያን ታሪክ አካል ነው፡፡የንግሰሥተ ሳባ ታሪክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በቀዳማዊ ነገሥት በሚገባ ተገልጿል፡፡ (1ኛነገ 10÷13) ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደሚያትተው ንግሥተ ሳባ የሰለሞንን ጥበብ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛ ከማየቷ በፊት አገሯ እያለች በዝና ታውቀውና ትሰማው እንደነበር እንዲህ በማለት ተገልጿል፡፡

‹‹ንጉሡንም አለችው፤ ስለነገርህ ስለጥበብህ በሀገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው፡፡እኔም መጥቼ በአይኔ እስከማይ ድረስ ነገሩኝን አላመንኩም ነበር፡፡እነሆም ጥበብህና ሥራህ ከሰማሁት ዝና ይበልጣል፡፡›› (፩ኛነገ፲÷፮)

ንግሥተ ሳባ ስለጥበበኛው ሰለሞን በዝና የምታውቀው ሁሉ በሁለቱ ሀገሮች መካከል በነበረው ግንኙነት ለንግድ ከእስራኤል አገር ደርሰው በሚመጡ ነጋዴዎች ነበር፡፡ሌላው ከዚህ ውጪ ባለው ንግግሯ ደግሞ በእርሷ ግዛትና በእስራኤል መካከል ግልጽ ሆነ የሃይማኖት አንድነት (አምልኮተ እግዚአብሔር) መኖሩን ያሳያል፡፡ያኔ ደግሞ ሳባን ጨምሮ ሌሎች የደቡብ ዓረቢያ ታናናሽ መንግስታት በእግዚአብሔር ሳይሆን በአምልኮተ ጣኦት እንደሚታወቁ ታሪክ ራሱ ምስክር ነው፡፡

በሌላ በኩል ንግሥተ ሳባ የሰለሞንን ጥበብ ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ስትጓዝ ለጥበበኛው ንጉሥ ወስዳ ካበረከተቻቸው ስጦታዎች መካከል ሽቶ፣ ወርቅ፣ የከበረዕንቁ፣ ተንከራዘኢትዮጵያ የሚባል የሽቶ አይነት የሰንደል እንጨትና የመሳሰሉት ከደቡብ ዓረቢያ ይልቅ በብዛት በኢትዮጵያ ይገኙ እንደነበር በርካታ ጠቋሚ ነገሮች አሉ፡፡አስቀድሞ እንደተገለጸው ጥንታውያኑ ግብጾች ኢትዮጵያን ‹‹ቶኔቶር›› (የአምላክ ሀገር) በማለት ሲጠሯት የነበረው እነዚህንና ሌሎች መሰል የከበሩ ውጤቶችና ማዕድናት መገኛ በመሆኗ ጭምር ነው፡፡

ለ) ክብረነገስት፡-

ይህ መረጃ ቀደም ብሎ እንደተዘጋጀ ቢገመትም ይበልጥ ግን የታወቀው የዓረብኛው ትርጉም ፲፫ኛው መቶክ/ዘ ብቅ ማለት ከጀመረ ወዲህ ነው፡፡ክብረነገሥት በተዓማኒነቱ ጉዳይ የተለያዩ ቢኖሩም ሥነጽሑፍ ባልዳበረበት በዚያ ዘመን የተገኘ በመሆኑ በመረጃነት ያለው ተፈላጊነት የጎላ መሆኑ ግን አጠራጣሪ አይደለም፡፡

ክብረነገሥት ሳባ በአገሯ ‹‹ማክዳ›› ተብላ እንደምታወቅ፤ኢትዮጵያዊት ንግስት ሆና የሰለሞንን ጥበብ ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም እንደተጓዘችና ከዚያም በኋላ ያለውን በንጉሥ ሰለሞንና በንግስተ ሳባ መካከል የነበረውን ግንኙነትና ፍሬ በዝርዝር ያስረዳል፡፡ወደ ኢየሩሳሌም ከመጓዟ በፊት ለንግስተ ሳባ ስለዚህ ጥበበኛ ንጉሥ የሚያጓጓና ድንቅ ነገር ነግሯት የነበረው ታምሪን (ዘምሪን) የተባለ ነጋዴ ነበር፡፡ያኔ ንጉሥ ሰለሞን ታላቁን ቤተመቅደስ ለማሰራት በዝግጅት ላይ ስለነበር ለቤተመቅደስ ማሰሪያም ብርቅና ድንቅ ዕቃዎችን ያቀርቡለት ከነበሩ የተለያዩ አገር ነጋዴዎች መካከል አንዱ ኢትዮጵያዊው ታምሪን እንደ ነበር ክብረነገሥት ይገልጻል፡፡ታምሪንም በዚህ አጋጣሚ ነበር የንጉስ ሰለሞንን ጥበብ፣ ክብር፣ ግናናነትና ዝና ለማየት ችሎ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ለንግሥተ ሳባ የነገራት፡፡ንግሥተ ሳባም ‹‹... ስለነገርህና ስለጥበብህ በሀገሬሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው፡፡›› (፩ኛነገ፲÷፮) ብላ የተናገረችው ለዚሁ ነው፡፡ክብረነገስት ስለንግሥተ ሳባ ጉዞና ከንጉሥ ሰለሞን ጋር የነበራትን ግንኙነት በሰፊው ያብራራ ሲሆን ይበልጡን ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጸው ታሪክ ጋር ተመሳሳኒት አለው፡፡

ሐ) ትውፊታዊ የጥንት ጥናት መካናት (Archeological Site) በአገራችን መገኘታቸው

ከንግስተ ሳባ ማንነት ጋር በተያያዘ መልኩ እስከ አሁን ድረስ በደቡብ ዐረቢያ በአርኪዎሎጂ ጥናት ምንም ዓይነት ፍንጭ እንዳልተገኘ ይታወቃል፡፡በሌላ በኩል ምንም እንኳ በቂ የሆነ ጥናትና ምርምር ባይካሄድም ከንግስተ ሳባ ጋር የተገናኙ በርካታ ትውፊታዊ የጥንት ጥናት መካናት በአገራችን (በአክሱም) ተገኝተዋል፡፡ከእነዚህ መካከል የንግስተ ሳባ ቤተመንግስት፣ የንግስተ ሳባ መቃብር፣የንግሥተ ሳባ መታጠቢያ ገንዳና የመሳሰሉት ነገሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡የንግሥተ ሳባ ቤተመንግስት በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ ሊገኝ የቻለው ህዝቡ ከትውፊት ባገኘው እውቀት መሠረት ቦታው ንግሥተ ሳባ ቤተመንግሥት እየተባለ ይጠራ ስለነበር ተመራማሪዎች ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተባለው አካባቢ ጥናት ማድረግ በመቻላቸው ነው፡፡ንግሥተ ሳባ ቤተመንግሥት ፍርሥራሽ ወደ 3ሺ ካሬ ሜትር የሚሆን ቦታ የያዘ ሲሆን ወደ ሀምሳ (፶) የሚደርሱ ክፍሎችም የሚገኙበት ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቤተመንግሥቱ ተቆፍሮ በሚወጣበት ጊዜ አብሮ የተገኘ ከአንገት በላይ ሆኖ ከድንጋይ የተቀረጸ የአንዲት ሴት ምስል (የንግሥተ ሳባ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይነገራል፡፡) አሁን ቤተክርስቲያኑ ንዋያተ ቅዱሳትና ቅርሶች ከሚታዩበት ጋር አብሮ ይጎበኛል የአክሱም ሀውልቶች ተጠርበው ከመጡበት ጎቦድራ ከሚባለው ቦታ አካባቢም ከክርስትና በፊት በርካታ ዘመናትን ያስቆጠረ ከድንጋይ ላይ የተቀረጸ ሴት አንበሳ ምስል ይገኛል፡፡በእኛ አገር በብዛት የተለመደው ሞአ አንበሳ ከሚለው ትውፊት ጋር የወንድ አንበሶች ምስል ሲሆን በአክሱም ግን በርካታ ዕድሜ ያስቆጠረው የሴት አንበሳ ምስል ከንግሥተ ሳባ ጋር ተያያዥነት ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል፡፡

2.2.2. ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን ያደረገችው ጉዞ ያበረከተው አስተዋጽዖ

በቅዱስ መጽሐፍና በሌሎች ማስረጃዎች እንደተገለጸው ንግስተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘችባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ በወሬ ትሰማውና በዝና ታውቀው የነበረውን የንጉሥ ሰለሞንን ጥበብ በዓይኗ አይታ ለማረጋገጥ
- ✓ ንጉሥ ሰለሞንን በእንቆቅልሽና በምሳሌ ለመፈተን
- ✓ ለጥበበኛው ንጉሥ ብርቅና ድንቅ ስጦታዎችን ለማቅረብ
- ✓ በእርሷና በንጉሥ ሰለሞን መንግስት መካከል የነበረው ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ ነበር፡፡

ንግስተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉዞዋ ተሳክቶላት ያሰበችውን ሁሉ ፈጽማ ወደ ሀገሯ እንደተመለሰች መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል፡፡እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ የንግስተ ሳባንና የንጉሥ ሰለሞን ግንኙነት ሲያጠቃልል ‹‹ንጉስ ሰለሞን በገዛ እጁ ከሰጣት ሌላ የወደደችውን ሁሉ ከእርሱ የለመነችውን ሁሉ ለሳባ ንግሥት ሰጣት፤እሷም ተመልሳ ከባሪያዎቿ ጋር ወደ ምድርዋ ሄደች፡፡›› (፩ኛነገ፲÷፲፫) በማለት ነው፡፡

ይህ ከጌታ ልደት በፊት ዘጠኝ መቶ ዓመት ገደማ ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም ደረገችው ጉዞና ከንጉሥ ሰለሞን ጋር የነበራት ግንኙነት በኋላ ዘመን የተመሰረተችው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ አዲስ ምዕራፍ እንደ ተከፈተ ይታመናል፡፡ይህ ታሪካዊ አጋጣሚ ከዚህ በፊት በእስራኤልና በኢትዮጵያ መካከል ለዘመናት የነበረውን ትውፊት፣ የባህል፣የሃይማኖትና የቋንቋ ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ አድርሶታል ከዚህ ታሪካዊ የንግሥተ ሳባ ጉብኝትም በኋላ ኢትዮጵያ፡-

- ✓ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ባለቤት
- ✓ የታቦተ ጽዮን መንበር
- ✓ የሥርዐተ ካህናት ተገልጋይ ሀገር ለመሆን በቅታለች፡፡

2.2.3. ቀዳማዊ ምኒልክ ማነው?

የንግስተ ሳባና የንጉሥ ሰለሞን ታሪካዊ ግንኙነት ለቀዳማዊ ሚኒሊክ መገኘት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል፡፡ከዚህ ታሪክ ጋር ተያያዥነት ያለው ትውፊት እንደሚያስረዳው ንግሥተ ሳባ ወደ ሀገሯ የተመለሰችው ቀዳማዊ ምኒልክ ከንጉሥ ሰለሞን ፀንሳ ነው፡፡ይህ የንግስት ሳባና የንጉሥ ሰለሞን ልጅ ከክብረነገስት ላይ ስሙ ‹‹ቦነለሐኪም›› ተብሎ ተገልጿል፡፡ ይህ ‹ቦይነለሐኪም› በዕብራይስጥ ቦንሀሐኪም በዓረቦች አብንኤልሐኪም የሚል ስያሜ ሲኖረው ፍቺውም በሁሉም ዘንድ ‹‹የጠቢብ ልጅ›› እንደ ማለት ነው፡፡ ግእዝ፣ዕብራይስጥና ዐረብኛ የሴም ቋንቋ ክፍሎች (Semetic Language Groups) ስለሆኑ በመካከላቸው ብዙ ተመሳሳይነት እንዳለ ግልጽ ነው፡፡እንግዲህ በጊዜ ብዛት በብዙ ጸሐፊዎች እጅ ሲተላለፍ ‹‹ቦይነለሐኪም›› የሚለው የመጀመሪያው ስያሜ ዛሬ ‹‹ምኒልክ›› የሚለውን ሊተካ እንደቻለ ተገምቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ትውፊታዊ መዛግብት ‹‹ምኒልክ›› የሚለው ስም በግዕዙ ‹‹መኑ ይልህቅ›› ከሚለው የተወሰደ እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡ ትርጓሜውም ‹‹እንደ እርሱያለ ትልቅ ማን አለ›› ማለት ነው፡፡ቀዳማዊ ምኒልክ በሀገሩ ‹‹ኢትዮጵያ›› ተወልዶ ካደገ በኋላ ሃያ ሁለት ዓመት ሲሞላው አባቱን ለመጠየቅና ከአባቱ ጋር ለመተዋወቅ ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ተጓዘ ይነገራል፡፡ንጉሥ ሰሎሞንም ሮብዓም የተባለው ሌላኛው ልጁ ገና የስድስት ዓመት ሕፃን ስለነበር ምኒልክን አልጋወራሽ ሊያደርገው ቢያስብም ምኒልክ ወደአገሩ ለመመለስ ስለወደደ ፈቃደኛ አልሆለትም፡፡ንጉሥ ሰሎሞንም ልጁ ምኒልክን ለካህኑ ሳዶቅ ቅብዓተ ንግሥና አስፈጽሞለት ከበኩር እስራኤላውያን ልጆች ጋር ወደ ሀገሩ ላከው፡፡በዚህ ጊዜ እነዚህ እስራኤላውያን /ካህናተ ኦሪት/ ጽላተ ሙሴን ይዘው ከምኒልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ የልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ሆኖ ኢትዮጵያን የታቦተ ጽዮን መንበር እንድትሆን ያደረጋት ይህ አጋጣሚ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ባለቤት ሆነ ስርዓተ ኦሪት በአገራችን መፈጸም የተጀመረውም ከዚህ በኋላ እንደነበር ይታመናል፡፡

2.2.4. የታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት

እግዚአብሔር ኢትጵያን እንደሚወዳት በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ክፍሎች የተገለጸ ቢሆንም ከሁሉም በላይ በልዩ ጥበቡ የታቦተ ጽዮን ባለቤት ሲያደርጋት ተረጋግጧል፡፡ ታቦተ ጽዮን ከሙሴ ጀምሮ ለብዙ ዘመናት በድንኳን ውስጥ ተቀምጣ ስትኖር ለመጀመሪያ ጊዜ ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ አሰራላት፡፡ (1ኛነገ.8) ታቦተ ጽዮን ከንጉሥ ሰለሞን ዘመን በኋላ ግን በእስራኤል ቤተ መቅደስ አልነበረችም፡፡

ስለ ታቦተ ጽዮን በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እስከ ንጉሥ ሰለሞን ዘመነ መንግስት ድረስ ከሁለት መቶ ጊዜ በላይ የተጠቀሰ ሲሆን ከንጉስ ሰሎሞን ጊዜ በኋላ ግን የታቦተ ጽዮን ታሪክ አንድ ጊዜም አልተወሳም፡፡እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮ በኋላም ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ዘሩባቤል ባሳነፀው ቤተመቅደስም ታቦት አልነበረም፡፡ስለሆነም አንዳንድ ፀሐፊዎች ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ሲያፈርስ ታቦተ ጽዮን ያን ጊዜ እንደጠፋች ይገልጻለ፡፡በዚህ ምክንያት የታቦተ ጽዮን የመሰወር ጉዳይ ለሌላው ዓለም እንቆቅልሽ ሆኖ ለዘመናት ኑሯል፡፡ታቦተ ጽዮን ግን ከእስራኤል ከተሰወረች ጀምሮ የነበረችው በኢትዮጵውያን ቤተ መቅደስ ነው፡፡ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ የመጣችውም አስቀድሞ እንደተገለጸው ከንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት በኋላ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት መሆኑ ይታመናል፡፡ይህች ታቦተ ጽዮን አሁን የምትገኘውም በአክሱም ለራሷ በተለየ ቤተ ክርስቲያን መሰል ትንሽ ሕንጻ ውስጥ ነው፡፡ዙሪያዋም በአጥር የተከለለ ሲሆን የሚጠብቃትም በድንግልና የመነኮሰ መላ ዕድሜውን ለዚህ አገልግሎት የሚያውል አባት ነው፡፡

2.2.5. የብሉይ ኪዳን ዕምነት እና ሥርዓት በኢትዮጵያ

ከክ/ል/ በፊት የብሉይ ኪዳን እምነትና የሕገኦሪት ሥርዐት ባለቤት የሆነችውም ከንግሥተ ሳባ ታሪካዊ የኢየሩሳሌም ጉብኝት በኋላ መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጿል፡፡የብሉይ ኪዳን እምነትና የሕገ ኦሪት ሥርዓት በኢትዮጵያ እንደነበር የሚገልጹ የተለያዩ ማስረጃዎች ሲኖሩ ዋና ዋናዎቹ፡-

1. በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመዱና የሚታወቁ አይሁዳዊ ትውፊቶች (Judaic Elements)

ሀ) የታቦተ ጽዮን መኖርና አከባበሩ

እንደሚታወቀው የታቦተ ጽዮን መኖርና የአከባበር ሥነ-ሥርዓቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትልቁ የእምነቷና የሥርዓቷ መገለጫ ነው፡፡ታቦት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ በምህረት በሚገለጥበት ጊዜ ዙፋኑ ነው፡፡ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳን ሀገር የነበረችው ኢትዮጵያ በክርስትና ጊዜ ታቦትን በክርስትና መንፈስ ትጠቀምበታለች፡፡እግዚአብሔር ጎቡዕ ስሙ የተጻፈበት ይህ ታቦት አሁን

በቤተክርስቲያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚቀርብበትና የሚፈተትበት መሠዊያ ነው፡፡በሐዲስ ኪዳን ኢትዮጵያ የታቦት ባለቤት መሆኗ ብቻ ሳይሆን በጥምቀትና በሌሎች በዓላት ንግሥ ጊዜ የሚታየውን ታቦትን ተሸክሞ በሆታ፣ በዕልልታ፣ በመዝሙር .... ወዘተ መንገዝና አጠቃላይ አከባበሩ የብሉይ ኪዳን እምነት ባለቤት እንደነበረች የሚገልጽ የእምነት ነጸብራቅ ነው፡፡

ለ) ቀዳሚት ሰንበትን ማክበር

ቀዳሚት ሰንበትን ማክበር በሕገ ኦሪት ተሰጠ አምላካዊ ትዕዛዝ ነው፡፡የቀዳሚት ሰንበት መከበር ከዐስርቱ ቃላተ ኦሪት ጋር አንድ ሆኖ በብሉይ ኪዳን የታዘዘ ሲሆን እሁድ ደግሞ ሰንበተክርስቲያን ተብላ በሐዲስ ኪዳን ትከበራለች፡፡መጽሐፍ ቅዱስ እሑድን ጌታ ከሙታን ተለይቶ የተነሳበት ስለሆነ ‹‹የጌታ ቀን›› ብሎ ይጠራታል (ራእ፲፥፩ኛቆሮ፲፮÷፪)፡ ፡ስለዚህ ቅዳሜና እሑድ የኢትዮጵያ ቤ/ክ የምታከብር ሲሆን የቀዳሚት ሰንበት መከበር የብሉኪዳን እምነት በኢትዮጵያ ስለመኖሩ አንዱ ማስረጃ ነው፡፡

ሐ). ልብሰ ተክህኖ (የካህናት ልብስ)

ልብሰ ተክህኖ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ካህናት የሚስጢራተ ቤተክርስቲያን ለምእመናን ለመፈጸም በቤተክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ የሚለብሱት ልብስ ነው፡፡ይህ ካህናት የሚለብሱት ልብስ በአሰራሩም ሆነ በሚቀመጥበት ቦታ የተለየየ መንፈሳዊ አገልግሎት ልብስ ነው፡፡ (ሕዝ፵፬÷፲፯÷፲፱) ይህ ዛሬ በቤተክርስቲያን ያለው ልብስ ተክህኖ መሰረቱ የኦሪት ሌዋውያን ካህናት አገልግሎት ስለሆነና መላ ሥርዓቱም ከጥንቱ ጋር ስለሚመሳሰል ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ባለቤት እንደነበረችም የሚገልጽ ሌላኛው ማስረጃ ነው፡፡

መ) ግዝረት

ግዝረት ለአብርሃም ከእግዚአብሔር የተሰጠው የቃልኪዳን ምልክት እንደነበር በቅዱስ መጽሐፍ ተጠቅሷል፡፡ (ዘፍ፲፯÷፱-፲፯) በቅድመ ክርስትና በስምንተኛው ቀን ያልተገረዘ ሁሉ በአብርሃም ቤተሰብነት አይጠራም፤ ምድረ ርስትን አይወርስም፤ ከተስፋውም አይካፈልም፤ የእግዚአብሔር ወገንም አይባልም ነበር (ዘሌዋ፲፪÷፫) እንደእስራኤላውያን ኢትዮጵያም የብሉይኪዳን እምነት ባለቤት ስለነበረች ልጆቿን በስምንተኛው ቀን ማስገረዝ የተለመደ ተግባር ሊሆን ችሏል፡፡ በእርግጥ በሐዲስ ኪዳን በግዝረት ፈንታ ጥምቀት ስለተተካ በሀገራችን የሚከናወነው ግዝረት የኦሪትን ሥርዓት (ሕግ) ስለምንከተል ሳይሆን ሕዝባዊ ልማድ ሆኖ በመቅረቱ ነው፡፡በአጠቃላይ ግን ግዝረት ኢትዮጵያ በቅድመ ክርስትና የነበራትን ሥርዐተ እምነት የሚመለከት ነው፡፡

ሠ) የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትን መለየት

በቅዱስ መጽሐፍ የብሉይ ኪዳን ክፍል ውስጥ ለእስራኤላውያን የታዘዙ የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት ዝርዝር ተገልጿል። (ዘዳግም፲፬÷፫-፳፯፣ ዘሌ፲፩÷፵፯) ኢትዮጵያውያንም ሸኮናው የተሰነጠቀና ያልተሰነጠቀ፣ የሚያመሰኳና የማያመሰኳ ወዘተ እያለ የሚበሉትና የማይበሉትን መለየታቸው በቅዱስ መጽሐፍ በተገለጸው የዕብራውያን ልማድ መሠረት ነው።

ረ) የማሕሌት ሥነ-ሥርዓትና የመዝሙር መሣሪያዎች

ሰ) እንግዳ መቀበል

ሸ) በደስታና በሐዘን ያለጊዜ ያለው ሁኔታ፤... ወዘተ

ምዕራፍ ሦስት

3. ክርስትና በጥንታዊት ኢትዮጵያ

3.1. የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ መግባት

የክርስትና ሃይማኖት በፍጥነት ወደ ሀገራችን እንዲገባ አስተዋጽኦ ያደረጉ በርካታ ነገሮች ሲኖሩ ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

3.1.1. የብሉይ ኪዳን እምነት፣ ሥርዓትና ትንቢት ቀድሞ በሀገራችን መታወቁ

ከዚህ በፊት ተደጋግሞ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ከእስራኤል ቀጥላ የብሉይ ኪዳን እምነት፣ትምህርትና ሥርዓት ባለቤት ስለነበረች የክርስትና ሃይማኖት ለመቀበል አልተቸገረችም፡፡የዓለም መድኃኒት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወለድበ ትንቢት ታውቀውና ትጠብቀው ስለነበር ክርስትናውን ለመቀበል ጊዜ አልወሰደባትም፡፡እንዲያውም የመወለዱን ዜና በሰማች ጊዜ ወርቅ፣እጣንና ከርቤ ይዛ ከሰብዓ ሰገል ጋር በኮከብ መሪነት ቤቴልሔም ተጉዛ ከስግደት ጋር እጅ መንሻ ማቅረቧ ይነገራል፡፡

ንጉስ ባዜን

"ያገንዩቅድሜሁኢትዮጵያወጸላእቱሂሐመደይቀምሉነገሥተተርሴስወደሰያትአመኃያበውኡነገ ሥተሳባወአረብጋዳያመጽኡወይሰግዱሎቱኩሉሙነገሥተምድርወይትቀነዩሎቱኩሉሙአሕዛ ብ "

"በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳለ፥ ጠላቶቹም አፈር ይልሳለ።የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ።ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል። አሕዛብም ሁሉ ይገዙለታል።" መዝ፸፩፥፱-፲፩።

ቅዱስ ዳዊት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከ፱፻ /ዘጠኝ መቶ/ ዓመት በፊት ከተናገራቸው ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያን ከተመለከቱ ትንቢቶች መካከል አንዱ እና ተጠቃሹ ይህ ከፍ ብለንበር እስ ደረጃ ያነሣ ነው ሲሆን እጅግ የሚያስደምም መልእክት ያለውነውና በጥንቃቄ ልንመረምረው ይገባል፡፡

ከሁለ አስቀድመን ቅዱስ ዳዊት ስለኢትዮጵያ ሲናገር ይኽ የመጀመሪያው እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ከዚህ ቃል አስቀድሞ "ኢትዮጵያ ታበጽ ሕእደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር- ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ሲል መናገሩን ያስታውሷል፡፡መዝ፷፯፥፴፩።

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት እጆቿን ሲል እጅ ኃይል ነው፡፡ ወድቀው ይነሣል በእጅ፣ አጥተው ይከብሯል በልጅ እንዲሉ በእጅ የራቀውን ያቀርቡበታል፣ የቀረበውን ያርቁበታል፡ ፡በእጅ ቢይዙ ያጠብቁበታል፣ ቢሰነዝሩ ያደቅቁበታል፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ እጅ ሲል

ኃይል፣ጉልበት፣ መመኪያ ለማለት ሲሆን እርሱም እግዚአብሔር መሆኑን ያጠይቃል፡፡ ትመካበታለች እና ጠላት ሲመጣባት እርሱን ይዛ እርሱን ተማምና ተዋግታለች፡፡ድል አቀዳጅቷትም ለዓለሙ የነፃነት ፋና ወጊ ሆና ስታበራ ትኖራለች፡፡ ስለሆነም በእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ስፍራ ያላት ቅድስት ሀገር ናት ለማለት ሁለት ጊዜ ማሰብ አያስፈልግም፡፡

ከፍ ብሎ በተነሣው ቃለ እግዚአብሔር መሠረት ኢትዮጵያ በፊቱ ይሰግዳሉ የሚል ትንቢት አለ፡፡ይኸ ትንቢት ደግሞ ከወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ጋር ተያይዞ የተነገረነውና ልብ ብሎ ለተመለከተው ስለ ዳግማዊ ልደት የተነገረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ሲወለድ ይኸ ቃለ ትንቢት ተፈጽሟልና፡፡

ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ ጌታችን በተወለደ ጊዜ ከተፈጸሙት ድርጊቶች መካከል ሰብአሰገል ለሕፃኑ ስግደት አምኃ ማቅረባቸውን ነግሮናል፡፡ እንዲህ ሲል "እነሆም፥ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር። ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው።ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር ዐዩት፥ ወድቀውም ሰገዱለት፥ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅመንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት።" ማቴ፪፥፱-፲፩።

ሕፃኑን ዐዩት፣ ሰገዱለት፣እጅ መንሻ አቀረቡለት የሚሉት ተከታታይነት ያላቸው ቃላት እጅግ ትኩረት የሚስቡ ናቸው፡፡ሰብአሰገል ሕፃኑን ዐዩት ሲል በሥጋ ማርያም በክበበ ትስብእት በግርማ መለኮት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ምክንያቱም ዐዩት ብሎ አልቆመም፡፡አስከትሎ ሰገዱለት አለ አንጂ፡፡ግርማ መለኮቱን ቢያዩ የእነርሱን ማዕረግ ትተው ዘውዳቸውን አውልቀው ለጌቶች ጌታ ለነገሥታት ንጉሥ ጎንበስ ቀና ብለው ሰግደውለታል፡፡ሕፃን ነው ብለው አልተጓደዱም ወይ አላመነቱም፡፡ቀጥለውም ለእርሱ መንግሥት ገባሪዎች መሆናቸውን ሲያጠይቁ እጅ መንሻን ሰጥተውታል፡፡

በነቢዩ ቅዱስ ዳዊት የተነገረው ትንቢት እንደሚገልጠው እጅመንሻ የሚያቀርቡ ሰዎች ማንነት ነገሥታት መሆናቸው እርግጥ ነው፡፡ በከብቶች ግርግም በእመቤታችን እቅፍ በግእዘሕፃናት ሲነጋገር አግኝተውት ለጌታችን እጅመንሻ ያቀረቡትን ቅዱስ ማቴዎስ ሰብአሰገል ይላቸዋል፡፡ቅዱስ ዳዊት ነገሥታት ሲላቸው ቅዱስ ማቴዎስ ሰብአሰገል በማለት ጠርቷቸዋል፡፡ ሁለቱንም ግን አምኃና ሰጊድ ማቅረባቸው አንድ ያደርጋቸዋል፡፡ ቅዱስ ዳዊት በፊቱ ይሰግዳሉ እንዳለው ቅዱስ ማቴዎስ ደግሞ ወድቀውም ሰገዱለት ብሏልና፡፡

ቅዱስ ዳዊት እነዚህን ቅዱሳን ከኢትዮጵያ ጋር ማዛመዱ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም፡፡ሲጀምር "ኢትዮጵያ በፊትህ ይሰግዳሉ" ብሎ ሲሆን ሲፈጽምም "የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅመንሻን ያቀርባሉ" ብሎ ነው፡፡በዚህ ቃለ ትንቢት ውስጥ ጉልህ ድርሻ የተሰጣት ኢትዮጵያ ለመሆኗ አንድ ጊዜ ኢትዮጵያ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሳባ በሚሉ የሀገሪቱ ተለዋዋጭ መጠሪያ ስሞች ደጋግሞ መጥራቱ ራሱ ምስክር ይሆናል፡፡ስለሆነም ከሰብአሰገል መካከል አንዱ ኢትዮጵያዊ መሆኑን በኩራት መናገር ይቻላል፡፡

ሰብአሰገል፣የጥበብ ሰዎች እየተባሉ ከሚነገሩት ሦስት ነገሥታት አንዱ ኢትዮጵያዊው ባዜን በተነገረለት ትንቢት በተቆጠረለት ሱባኤ መሠረት ገስግሶ ተጉዞ ቤተልሔም ከከብቶች ግርግም ደርሶ ሰግዶ አምኃውን አቅርቦ ተባርኮ ተመልሷል፡፡ስለልደተ ክርስቶስ ለመናገር በሀገር ደረጃ ሊቀድመን የሚችል ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ነቢዩ እና ወንጌላዊው ተባብረው መስክረውልናልና፡፡ ስለሆነም የጌታችን ልደት ለኢትዮጵያ የተለየ ትርጉም አለው፡፡ ለማን መስገድ እንዳለብን የምናውቅ ሕዝቦች ነን፡፡ጌታችንንም እመቤታችንንም ያወቅናቸው እዚያው ቤተልሔም ተገኝተን ግርማውን ዐይተን፣ቅዱሳን መላእክት ከእረኞች ጋር ሲዘምሩለት ሰምተን፣ አድግና ላሕምትን ፈሻቸውን ሲገብሩለት ተመልክተን፣ የሌሊቱን ግርማ በመሎኮታዊ ሥልጣኑ በብርሃን ጸዳል ሲሞላው ዐይተን እንጂ በሰሚ ሰሚ ያወቅነው አይደለንምና ፍቅሩን ከልቡናችን ያወጣብን ዘንድ የሚችል አይኖርም፡፡እኛው ሸተነው እኛው ፈልገነው ሄደናልና፡፡

3.1.2. ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የነበራት የጠበቀ ግንኙነት

ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋር የነበራት ግንኙነት ከክርስትና በፊት ብዙ ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑ በመረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ከሁሉም በላይ በቅድመ ክርስትና በኢትዮጵያና በእስራኤል መካከል የነበረው የጠበቀ የንግድ፣የባሕልና የሃይማኖት ግንኙነት እንደ አብነት የሚጠቀስ ነው፡፡ይህ ቀድሞ የነበረው ግንኙነትም ክርስትና በምድረ እስራኤል ሲጀመር (ሲሰበክ) በተለያየ ሰዎች አማካኝነት የክርስትናው ዜና በሀገራችን በቶሎ እንዲደርስ የበኩሉን አስተዋጽ ማበርከቱን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በንግሥት ህንደኬ ጃደረባ አማካኝነት በ34 ዓ.ም ነው ብንልም ከዚያ በፊት ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋር የነበራት የጠበቀ ግንኙነት ጌታችን በተወለደ ሰሞን ከዛ አካባቢ በሚመጡ ሰዎች ምክንያት የክርስትናው ወሬ በሀገራችን ተዳርሶ ነበር፡፡ ጌታችን በተወለደ ዘመን የነበረው ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ባዜን በመባል ይታወቃል፡፡

3.1.3. የንግስት ህንደኬ ጃንደረባ ጉዞ ወደ ኢየሩሣሌም

የንግሥት ህንደኬ ጃንደረባ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል (ሐዋሥ 8÷26-40)፡፡ኢየሩሣሌም ሄዶም በዓል አክብሮ ሲመለስ የነብዩ የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ (ኢሳ 53) እግዚአብሔር ቅዱስ ፊሊጶስን ልኮለት የክርስትና ትምህርት ከተረዳን ከተጠመቀ በኋላ ወደ ሃገሩ ተመልሷል፡፡ከዚህ በኋላ ጃንደረባው ይህን የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲጀመር በማድረጉ ምክንያት ግምባር ቀደም የሆነ አፍሪካዊ ሐዋርያ ነው፡፡ታዋቂው የቤተክርስቲን አባት አውሳብዮስ ዘቂሳርያ ‹‹ሕጽው ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆነ›› እንዳለ፡፡

3.1.4. ኢየሩሳሌም ተገኝተው በዓለ ኃምሳን ያከበሩ ኢትዮጵያውያን

በዓለ ኃምሳን ለማክበር ከተለያየ አካባቢ ተሰብስበው በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ያመኑ ሦስት ሺ ምዕመናን ነበሩ፡፡ (የሀዋ.ሥራ 2) ከነዚህም መካከል ኢትዮጵያውያን ስለነበሩ ከበዓሉ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው የክርስትና እምነት እንዲታወቅ በማድረግ በኩል የበኩላቸው አስተዋጽኦ እንደነበራቸው ይታመናል፡፡ኢትዮጵያውያን በበዓሉ ወቅት ኢየሩሳሌም እንደነበሩ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በበዓለ ኃምሳ ድርሳኑ ‹‹ቅዱሳን ሐዋርያት ጸጋ መንፈስቅዱስ በተቀበሉት ወቅት ኢትዮጵያውያንም ተገኝተው ነበር ብሏል››

3.1.5. የሐዋርያት አስተዋጽኦ

የታወቁት የቤተክርስትያን ታሪክ ጸሐፊዎች ሩፊኖስና ሶቅራጥስ ወንጌላዊ ቅዱስ ማቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወንጌል እንደሰበከ ጽፈዋል፡፡አባ ጀሮም ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ እንዳስተማረ ሲገልጽ ዩሐንስ አፈወርቅ ደግሞ ቅዱስ ቶማስ እንዳስተማረ ጽፏል፡፡ይህ የተለያየ አገላለጽ በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያ ግዛት ሰፊ ስለነበር አንዱ ሐዋርያት በአንዱ አካባቢ ሲያስተምር ሌላኛው ደግሞ በሌላ ግዛት (አካባቢ) እንዳስተማረ እንረዳለን፡፡

3.1.6. ክርስትና አስቀድሞ በነገሥታት አካባቢ ተቀባይነት ማግኘቱ

የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ ነው የሚያሰኘው በሌላው ዓለም ክርስትና ቀድመው የተቀበሉት አብዛኛዎቹ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሲሆኑ በኢትዮጵያ ግን ነገሥታቱ ናቸው፡፡ይህም የክርስትና ሃይማኖት በሀገራችን በነገሥታቱ አካባቢ ቀድሞበ መዳረሱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመላ ሀገሪቱ ለመስፋፋትና በሌላው የኅብረተሰብ ክፍል በፍጥነት ተቀባይነት ለማግኘት እንደቻለ እንገነዘባለን፡፡

3.2. በኢትዮጵያ ለክርስትና ሃይማኖት መታወቅና መስፋፋት አስተዋጽኦ ያበረከቱ ቅዱሳን

3.2.1. ኢትጵያዊው ጃንደረባ

በሀገራችን የክርስትና ሃይማኖት ታሪክ የክርስትናን ዜና ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት ጃንደረባው የመጀመሪያው ሰው ነው፡፡ አስቀድሞ እንደተገለጸው ጃንደረባው በ34 ዓ.ም በአሪት ዕምነት መሰረት ለስግደት ኢየሩሳሌም ደርሶ ሲመለስ ጋዛ አካባቢ በፊልጶስ አስተማሪነት አምኖና ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ተመልሷል፡፡በዚህም መሰረት ቅዱሳን ሐዋርያት ገና ከኢየሩሣሌም ሳይወጡ ጃንደረባው የክርስትናውን እምነት ለሀገሩ በማድረስ ቁልፍ ሚናን ተጫውቷል፡፡

3.2.2. ቅዱስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማከሣቴ ብርሃን)

ቅዱስ ፍሬምናጦስ በጃንደረባው የተዘራው የክርስትና ዘር ሥር እንዲሰድና እንዲያፈራ ያደረገ ትልቅ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ባለውለታ ነው።የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ34 ዓ.ም በጃንደረባው አማካኝነት ቢሆንም ቤተክርስቲያን በሲኖዶስ ሕግ የኢጲስ ቆጶስ መንበር የተሰጣት እና ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን መፈጸም የተጀመረው በ4ተኛው መ/ክ/ዘ በ20ኛው የእስክንድሪያው ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ በተሾመው በቅዱስ ፍሬምናጦስ ነው።

ቅዱስ ፍሬምናጦስ ብርሃነ ወንጌልን በመላው ኢትዮጵያ እንዲዳረስ ታላቅ ሐዋርያዊ ተጋድሎ የፈጸመ የሰላም አባት በመሆኑ በኢትጵያውያን ዘንድ አባ ሰላማከሳቴ ብርሃን (የሰላም አባት የብርሃን ገላጭ) ተብሎ ይጠራል።ቅዱስ ፍሬምናጦስ በትውልዱ ግሪካዊ ሲሆን በምን ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ እንደቻለ ሩፊኖስ የተባለው የቤተክርስቲያን ጸሐፊ ታሪኩን እንዲህ ጽፎታል (ታሪኩን የጻፈው በኢትዮጵያ ብዙ ዘመናት ኖሮ ወደ ሀገሩ ሶሪያ ከተመለሰው ከፍሬምናጦስ ወንድም ከኤድስዮስ (ሲደራከስ (ካህን ሆኗል) ሰምቶ እንደሆነ አትቷል) ሜሮጵየስ ተባለ አንድ ነጋዴ (ፊላስፋ) ከሁለት ወጣት ዘመዶቹ ጋር ሆኖ ከጢሮስ ወደ ህንድ አቅጣጫ በጀልባ ተጓዘ።ከነዚህ ሁለት ወጣቶች ትልቁ ፍሬምናጦስ ትንሹ ደግሞ ኤዴስዮስ ይባሉ ነበር።ሁለቱም ክርስትያኖች ነበሩ በጉዟቸው ጊዜ በአፍሪካ የባሕር ጠረፍ በቀይ ባሕር ወደብ ውኃ ለመጠጣት ሀገር ለማየት ከጀልባቸው ወርደው ጅልባቸውንም ከወደብ አስጠግተው ሳሉ በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በጀልባይቱና በተሳፋሪዎቹ ላይ አደጋ ጥለው ዕቃቸውን ዘረፏቸው።ሜሮጵዮስንና የጀልባይቱንም ቀዛፊዎች እዚያው ገደሏቸው እንደ አጋጣሚ ሁኖ ሁለቱ ወጣቶች ብቻ ከመገደል አምልጠው ባንድ ዛፍ ስር ተጠግተው ሲፀልዩና መፅሐፍ ሲያነቡ ተገኙ፤ ያገኙዋቸውም ሰዎች በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሳያደርሱ በፈረስ አንገት በጦር እንደበት የተማረኩ ሰዎችን አመጣንልህ ብለውለ ንጉሳቸው ሰጡት።እነዚህ ሁለት ወጣቶች አየዋለ እያደሩ በቤተመንግስቱ ተወዳጅነትና ታማኝነትን በማግኘታቸው ንጉሱ አይዛና (የአብርሃና አጽብሐ አባት) ኤዴስዮስን ጋሻ ጃግሬ ፍርምና ጦስን ደግሞ በጅሮንድ (ገንዘብ ያዥ) አድርጎ ሾማቸው።ንጉሱ ሊሞት በተቃረበት ልጆቹ ገና አካለ መጠን አልደረሱም ነበርና መንግስቱን በሞግዚትነት እንድትይዝ ለእቴጌይቱ አደራ ሲል ሁለቱን ሶሪያውያን ምርኮኞች ለቀቃቸው።ነገር ግን በእቴጌይቱ ልመና ወደ ሀገራቸው መመለሳቸው ቀርቶ ልጆችዋ እስኪያድጉ ድረስ በአስተዳደር በኩል ሲመክሯት ቆዩ።ፍሬምና ጦስበ አክሱም በነበረበት ጊዜ የቤተመንግሱቱ አማካሪ ብቻ ሳይሆን የክርስትና ሃይማኖት በሚገባ የሚስፋፋበትን መንገድ ይፈልግ ነበር።ልዑላኑ አካለ መጠን ደርሰው የአባታቸውን መንግስት ሲረከቡ ኤዴስዮስ ወደ ሀገሩ ጢሮስ ሲመለስ ፍሬምናጦስ ግን ስለጵጵስና ጉዳይ በቅርብ ከምትገኘው ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ጋር እንዲወያይ በአክሱም ቤተመንግስት ተልኮ ሄደ። የእስክንድርያው ፓትርያርክ አትናቴዎስም በጉዳዩ በጣም ተደስቶ የኢትጵያውያንን ቋንቋና ባህል የሚውቅ ሌላ ሰው ባለመገኘቱ ፍሬምናጦስን ጳጳስ አድርጎ ሾሞ ልኮታል።

ቅዱስ ፍሬምናጦስ ካበረከታቸው መንፈሳዊ ተድባራት መካከል

- በኢትዮጵያ የክርስትና ትምህርትንና ሥርዓትን አስፋፋ፡፡ለምሳሌ አበነፍስ እንዲኖር ሥርዓት ሠርቷል፡፡ የፅዋ ማህበራት እንዲስፋፉ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡
- የቁርባንና የክህነትን ሕግ አጠናክሯል፡፡በመላው ኢትዮጵያ የወንጌል ትምህርት ለማዳረስና ምስጢራተ ቤተክርስቲንን ለመፈፀም የሚረዱትን ቀሳውስትና ዲያቆናትን ሾሟል፡፡
- ቅዱስ መጻሕፍትን ከሱርሰት፣ ከዕብራይስጥና ከግሪክ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተርጉሟል፡፡
- የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ ለውጦ ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍና የማንበብ ዘዴን ፈጥሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉ አናባቢዎችን በማስገባት የግዕዝ ፊደላትን ባለሰባት ዘር እንዲሆኑ አድርጓል፡፡
- በ350 ዓ.ም ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን አስደርጓል፡፡
- ኢዛናና ሳይዛና በትምህርተ ክርስትና ኮትኩቶ በማሳደግ መንፈሳዊ ፍሬ እንዲያፈሩ አድርጓቸዋል፡፡ሥልጣነ መንግስት ሲይዙም አብርሃና አጽብሃ ብሎስም ያወጣላቸው እርሱ እንደሆነ ይታመናል፡፡
- በአክሱም ባለ 13 መቅደስ በጽዮን ማርያም ስም የምትጠራ ትልቅ ቤተክርስቲያን አሰርቷል፡፡ ይህች በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ቤተክርስቲያን ነች፡፡

ቅዱስ ፍሬምናጦስ ከዚህ ሁሉ ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎት በኋላ ሐዋርያዊ ተልእኮውን ፈጽሞ ሐምሌ 26 ቀን በ380 ዓ.ም ዐርፏል፡፡በዚህ ዕለት በየአመቱ ይህ ታላቅ ሰው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታስቦ ይውላል፡፡ በትግራይም ዓብዩ ዓዲ በተባለ ቦታ ቤተክርስቲያንና ገዳም በፍሬምናጦስ ስም መሥርታ ታስታውሰዋለች፡፡

3.2.3. ዘጠኙ ቅዱሳን

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ዘጠኙ ቅዱሳን በመባል የሚታወቁት በሁለተኛው የኢትዮጵያ ጳጳስ በአባ ሚናስ ጊዜ በንጉሥ አልዓሜዳ ዘመን መንግሥት በ5ኛው መ/ክ/ዘ ማለቂያ ላይ (በ480 አካባቢ) ወደ ሀገራችን የገቡት ናቸው፡፡እነዚህ ቅዱሳን የመጡት ከሮምና ቪዛንታይን ግዛት አካባቢዎች ሲሆን የመጡበት ምክንያት በ451 ዓ.ም በሁለት ባሕርይ ትምህርቱ የተወገዘውን የኬልቄዶን ጉባኤና ውሳኔውን አንቀበልም ስላሉ በነገስታቱ መከራ ስለበዛባቸው ነው፡፡ዘጠኙ ቅዱሳን የእምነት መሰሎቻቸው ወደ ሚኖሩባት ቅድስት አገር ሲመጡም የተለመደው አብርሃማዊ የእንግዳ አቀባበል ተደርጎላቸዋል፡፡እነርሱም በበኩላቸው በኢትዮጵያ በርካታ መንፈሳዊ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡

- ክርስትናን በብዙ ቦታዎች አስፋፍተዋል፡፡
- በስማቸው የሚጠሩትንና ሌሎችንም ገዳማት መስርተዋል፡፡ከእነዚህም መካከል በአቡነ አረጋዊ የተመሰረተው የደብረ ዳሞ ገዳም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው፡፡
- በኢትዮጵያ ለገዳማዊ ኑሮና ለምንኩስና ሥርዐት መሰረት ጥለዋል፡፡የቅድስና ህይወትንም በኑሮ አሳይተዋል፡፡ለምሳሌ አፄ ካሌብ ዙፋኑን ጥሎ ገዳም የገባው በእነርሱ ተማርኮ ነው፡፡

- የግዕዝን ቋንቋ አጥንተው በርካታ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ መልሰዋል (ተርጉመዋል)፡- ከእነዚህም መካከል፡-
- መጽሐፍ ቅዱስን
- ቁርሎስ ዘእስክንድርያንና ዩሐንስአፈወርቅን የመሳሰሉ አበው ያዘጋጇቸው የትምህርተ ሃይማኖት ድርሳናትን በአባ ጳኩሚስ የተዘጋጀው መፅሐፈ መነኮሳትና በቅዱስ አትናቴዎስ የተዘጋጀው የአባ እንጦንዮስ የህይወት ታሪክ ይገኙባቸዋል፡፡በዚህም ዘጠኙ ቅዱሳን ለግዕዝ ሥነጽሑፍ እድገትና መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡
- ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዐይን የሆኑ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል፡፡በተለይ በዜማ ድርሰቱ የሚታወቀው ቅዱስ ያሬድ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ቅዱስ ያሬድ ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ የሆነው የአቡነ አረጋዊ (ዘሚካኤል) ደቀ መዝሙር ነው፡፡

ሰንጠረዥ 3.1

ተ.ቁ	ስማቸው	የመጡበት ሀገር	ገዳማቸው	የመታሰቢያ ዕለት
፩	አቡነ አረጋዊ	ሮም	ደብረ ዳሞ	ጥቅምት 14(ዘሚካኤል)
፪	አባ ገሪማ	ሮም	መደራ	ሰኔ 17 (ይስሐቅ)
፫	አባ ጴንጠሌዎን	ሮም	አክሱም አጠገብ	ጥቅምት 6
፬	አባ አፍፄ	ታናሿ እስያ (የዛሬዋ ቱርክ)	የሐ	ግንቦት 29
፭	አባ ጎባ	ኪልቅያ (ምሥራቅአርመን)	ገርዓልታ	ግንቦት 29
፮	አባ ሊቃኖስ	ቁስጥንጥንያ (ግሪክ)	ደብረ ቆናጽል	ጎዳር 21
፯	አባ ይምዓታ	ታናሿእስያ (ቱርክ)	ገርዓልታ	ጥቅምት 23
፰	አባ ጽሕማ	አንጾኪያ (ግሪክ)	ጼዴንያ	ጥር 16
፱	አባ አሌፍ	ቂሣርያ	ብጎዛን	መጋቢት 11

ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል ሁለቱ ወደ ሃገራችን ከገቡ በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ የሚታወቁት ኢትዮጵያውያኑ ባወጣላቸው ስም ነው፡፡እነዚህም ቀድሞ ዘሚካኤል የሚባሉት አቡነ አረጋዊና ቀድሞ ይሥሐቅ ይባሉ የነበሩት አባ ገሪማ ናቸው፡፡አቡነ አረጋዊ በትሕትናቸው አባ ገሪማ ደግሞ በገቢረተ አምራቸው አዲስ ስም በኢትዮጵያዊያን እንደወጣላቸው ይነገራል፡፡

3.2.4. ዐፄ ካሌብ

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የታሪክ ሂደት ከአብርሃና አጽብሐ ቀጥሎ የዐፄ ካሌብ መንፈሳዊ አስተዋፅኦና ክርስቲያናዊ ተጋድሎ በቋሚነት የሚዘከር ነው፡፡ዐፄ ካሌብ በ6ኛውመ/ክ/ዘ የነበረ ጠንካራና ስመጥር አክሱማዊ መሪ ሲሆን በዘመኑም የአክሱምን ሥልጣኔ፣ኃያልነትና ክብር ከፍተኛ ደረጃ ላይ አድርሶታል፡፡ በተለይ የናግራን ክርስቲያኖችን ከዕልቂት ለመታደግ ወደ ደቡብ ዓረቢያ (የመን) ያደረገው ዘመቻ ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀር ዐፄ ካሌብን በደንብ እንዲታወቅና እንዲታወስ አድርጎታል፡፡

እንደ ሚታወቀው ከዐፄ ካሌብ ዘመቻ በፊት የመን አካባቢ በርካታ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ይኖሩ ነበር፡፡ሆኖም ግን በተለያየ ምክንያት ከኢየሩሳሌም የመጡ አይሁዶች ፊንሐስ (ድሆኖኅስ) በተባለው መሪያቸው አስተባባሪነት ተነሳስተው በክርስቲያኖች ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ በማድረጋቸው በርካቶች እንዲሞቱና አገርጥለው እንዲሰደዱ አድርገዋቸዋል፡፡ አብያተ ክርስቲያናቱም እንዲቃጠሉና እንዲፈራርሱ አድርገዋል፡፡ይህም ዘግናኝ እልቂት የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጢሞቴዎስ ከቁስጥንጥንው ንጉሥ ዮስጢኖስ ቀድመው በመስማታቸው ለዐፄ ካሌብ ጉዳዩን በደብዳቤ ገልፀውለታል፡፡ዐፄ ካሌብም እጅግ አዝኖ በፀሎተ ምሕላ ፈቃደ እግዚአብሔርን ከጠየቀ በኋላ ወደ ደቡብ ዐረብያ ዘምቷል፡፡ዘመቻው እጅግ የተሳካ ነበርና አይሁዶችን ደምስሶ ክርስቲያኖችን ነፃ በማውጣትና በማረጋጋት የፈረሱ አብያተክርስቲያናትንም በማሳነጽ አጠቃላይ ሁኔታውን ሥርዓት ካስያዘ በኋላ በድል ወደ ሀገሩ ተመልሷል፡፡ዐፄ ካሌብ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ በዙፋኑ ልጁ ገብረመስቀልን በመተካት ወደ አባ ጴንጠሌዎን ገዳም ለምናኔ ሄደ፡፡ የከበረ ዘውዱንም በጌታችን መቃብር (በጎለጎታ) ላይ መታሰቢያነት እንዲቀመጥለት ወደ ኢየሩሣሌም ልኮታል፡፡ ዐፄ ካሌብ በምናኔ 12 ዓመት ከኖረ በኋላ በግንቦት 20 ቀን 536 ዓ.ም አርፏል፡፡ከዚህ በተጨማሪ አፄ ካሌብ በዘመነ መንግሥቱ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትንም በማነፁ ይታወቃል፡፡የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅድስና ማዕረግ በመስጠት ቅዱስ ብላ ትጠራዋለች፡፡

3.2.5. ቅዱስ ያሬድ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትገለገልበትን ዜማ የደረሰው ቅዱስ ያሬድ የተወለደው በ505 ዓ.ም በአክሱም ከተማ ነው፡፡ እናቱ ታውክልያ አባቱ አብዩድ ይባላሉ፡፡ ቅዱስ ያሬድ በዘመኑ የነበረውን ትምህርተ ቤተክርስቲያን በሚገባ አጠናቆ እስከ መምህርነት የደረሰ ሊቅ ነበር፡፡ቅዱስ ያሬድ ግዕዝ ዕዝልና አራራይ ተብለው በሦስት የተከፈሉ የዜማ ስልቶችን የጀመረ ትልቅ የቤተክርስቲያን ባለውለታ ነው፡፡ ለዜማውም ድፋት፣ ሂደት፣ ቅናት፣ ቁርጥ፣ ጭረት፣ ርክርክ፣ ደረት፣ አንብር እና ድርስ የተባሉ አሥር ምልክቶችን እንዳዘጋጀ በትውፊት ይነገራል፡፡ ቅዱስ ያሬድ በብሉያት፣ በሐዲሳት፣ በቅዱሳን አበው ታሪክና በሰማዕታት ገድሎች ላይ መሠረት ያደረጉ አምስት የዜማ መጻሕፍትን ደርሷል፡፡ እነዚህም ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ አዋሥዕት እና ምዕራፍ ናቸው፡፡

ቅዱስ ያሬድ ዜማዎቹን በአራት ከፍሎ በክረምት፣ በበጋ በመፀውና በጸደይ ወራት ከሚከሰቱ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ጋር እያስማማ አዘጋጅቶታል። ከቅዱስ ያሬድ በፊት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዐተ ጸሎት ይፈጸም የነበረው የጸሎት መጻሕፍቱን በውርድ ንባብና በለሆሳስ በመድገም እንደነበር ይታመናል። ከዚህ ሌላ ቅዱስ ያሬድ አንቀጸ ብርሃን የተባለውን ጸሎት መስረሱ ይታወቃል። የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ለቅዱስ ያሬድ የቅድስና መዐረግን ሰጥታ የመታሰቢያውም በዓል ግንቦት 11 ቀን ታከብራለች።

3.2.6. ዐፄ ገብረመስቀል

የንጉስ ካሌብ ልጅ የሆነው ዐፄ ገብረመስቀል በአባቱ እግር ተተክቶ ኢትዮጵያን ያስተዳደረ መንፈሳዊ መሪ ነው።ዐፄ ገብረ መስቀል ከአቡነ አረጋዊና ከቅዱስ ያሬድ ጎን ተሰልፎ በርካታ መንፈሳዊ ተግባራትን አከናውኗል። ከነዚህም መካከል፡-

- በርካታ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጿል።
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ከውጭ ዓለም ጋር የነበራት መልካም ግንኙነት እንዲያድግና ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ አድርጓል።
- በሀገራችን በዘመኑ ለነበሩ ገዳማትና አድባራት የመተዳደሪያ ርስት ጉልት እንዲያገኙ አስችሏቸዋል።
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን በኢየሩሣሌም ቅዱሳት መካናት እንድታገኝ አስችሏል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በወጣትነት ዕድሜው የመነኮሰው ሙሴ የተባለው ልጁ ኢየሩሣሌም በሚገኙ የኢትዮጵያ ገዳማት ሙሉ ሕይወቱን በምንኩስና እንዳሳለፈ ይተረካል።
- ከቅዱስ ያሬድ ጋር በመሆን የሆሳዕናና የተቀጸል ጽጌ በዓላት የአከባበር ሥርዓትን ሠርተዋል። ተቀጸል ጽጌ የዐጼ መስቀል ተብሎ መስከረም 10 ቀን በቤተክርስቲያን በድምቀት የሚከበረው ነው። በተለይ አዲስ አበባ ከፍተኛ የቤተክርስቲያንና የመንግስት አካላት በተገኙበት በልዩ ሥነሥርዓት በቅድስት ሥላሴካቴድራል በየዓመቱ ይከበራል።

የተቀጸል ጽጌ መሠረታዊ መነሻው በኦሪት ዘመን ይከበር የነበረው የአበባ በዓልነው። በእኛ ሀገር ግን በተለይ ከአፄ ዳዊት ዘመን በኋላ (14ኛው መ/ክ/ዘ) ገደማ መስቀሉ ወደ ሀገራችን የገባበትን ዕለት መሠረት በማድረግ መስከረም 10 ቀን በዓሉ መከበር ተጀምሯል።

ዐፄ ገብረመስቀል ያበረከተው መንፈሳዊ (ክርስቲያናዊ) አስተዋጽኦ ታላቅ በመሆኑ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የቅድስና ማዕረግ ሰጥታ የመታሰቢያ በዓሉን ኅዳር 30 ቀን ታከብራለች።

3.3. የጨለማው ዘመን ተጽዕኖዎች

በሀገራችን ታሪክ ሂደት ከአክሱም መንግሥት መዳከም ጀምሮ እስከ ዛጉዌ ሥርወመንግስት መነሳት ድረስ ያለው ጊዜ የጨለማው ዘመን በመባል ይታወቃል። ለስያሜው መነሻ የሆነው ዋና ምክንያት በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ታሪካዊ ክሥተት

የሚገልጹ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሊገኝ ባለመቻሉ ነው።።በዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሁለት ዓበይት ፈተናዎች ተውጣ የተዳፈነች እሳት ትመስል ነበር።።

3.3.1. የእስልምና እምነት መስፋፋት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ያደረሰው ተጽዕኖ

እስልምና መሀመድ በተባለ የመካ (ሳውዲ ዓረቢያ) ሰው በ7ኛው መ/ክ/ዘ መጀመሪያ ተመሥርቶ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በበርካታ የዓለም አካባቢዎች ሊስፋፋ የቻለ እምነት ነው።።መሥራቹ መሀመድ አዲሱን እምነት በትውልድ አገሩ ማስተማር ሲጀምር ቁራይሾች በተባለ የአካባቢው ሕዝቦች ተቃውሞ ስለደረሰበት ከመካ ወደ መዲና የተሰደደ ሲሆን ወደ ሰባ የሚሆኑ ሌሎች ተከታዮች ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል።።በወቅቱ የነበረው ኢትዮጵያዊ ንጉሥና የክርስቲያን ማኅበረሰብበ ተለመደው የአብርሃማዊ ተግባራቸው ስደተኞቹን ተቀብለው ወደ ሀገራቸው እስኪ መለሱ ድረስ በሰላም እንዲኖሩ አድርገዋቸዋል።።መሀመድም ወገኖቹ በኢትዮጵያውያን የተደረገላቸውን ሰብዓዊ ርኅራሄ ሰምቶ ለተከታዮቹ ‹‹ሀበሻን አትንኩ›› የሚል መልእክት እንዳስተላለፈላቸው ይነገራል።።

ከጅሃድ ጦርነት በተጨማሪም በኬልቄዶን ጉባኤ የተፈጠረው አለመግባባት፣ የቤተክርስቲያን መከፋፈልና የቤዛንታይን ነገሥታት የሁለት ባሕርይን እምነት አንቀበልም በሚሉ ክርስቲያኖች ላይ ያደርሱት የነበረው ግፍና ጭቆና ለእስልምና እምነት መስፋፋት ዓበይት ምክንያት እንደሆነ ይታመናል።።በዚህ ወቅት ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የነበራቸው የየመን አካባቢ፣ግብጽ ቀይ ባህርና ሌሎች ጎረቤት ሀገሮች በእስልምና ሃይማኖት ተፅዕኖ ሥር ወድቀዋል።።ሌሎች በርካታ ችግሮች በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የደረሱ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም፡-

- አስቀድሞ በፋርሶች (Persian) ምክንያት የፈራረሱ የመን አካባቢ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በእስልምና ሲወረሩ ጨርሶ ደብዛቸው ጠፋ።። ክርስቲያኖቹም መነመኑ።። አካባቢው እስከ ዛሬ የእስላሞች መናኸሪያ ኾኖ ቀረ።።
- የቀይ ባሕር ደሴቶችና ንግድ መስመሮች በእስላሞች እጅ በመውደቃቸውና ዓለም አቀፍ ግንኙነትም በመቋረጡም የአክሱም መንግስት ውድቀት ተፋጠነ።።የአክሱም መንግስት መዳከምም ለዮዲት ጉዲት የጥፋት ዘመቻ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል።።
- በንግድ ሰበብ ወደ ኢትዮጵያ በገቡ የዓረብ ነጋዴዎች ምክንያት በሀገራችን የጠረፍ አካባቢዎች የእስልምና ሃይማኖት ማቆጥቆጥ ጀመረ።። ቀስ በቀስም የሸዋ፣ የኢፋት፣ የአዳል፣ የባሌ፣ የሃድ ያየፋ ጠገርና የዳዋር ታናናሽ የእስላም መንግስታት ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ።። እንደሚታወቀው በ16ኛው መ/ክ/ዘ ላይ ብዙ ጥፋት ያደረ ሰው አህመድ ግራኝም በወቅቱ የአዳል ሙስሊሞች መሪ ነበር።።
- የግብፅ በሙስሊም መሪዎች ሥር በመውደቋ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጳጳሳትን ከእስክንድርያ ለማስመጣት ብዙወርቅ፣ ብር፣ ዕንቁ፣ አልማዝ፣ የቁም እንስሳት ወዘተ... የመሳሰሉትንበመላክገጸበረክትማቅረብምየግድነበር።።
- የግብጽ ሙስሊሞች የሀሰት ደብዳቤ ወደ ሀገራችን ይዘው በመምጣትና የጵጵስና ማዕረግ እንዳላቸው በመግለጽ ህዝበ ክርስቲያኑን እስከማወናበድ ደርሰዋል።።ለምሳሌ አብዱም የሚባል ግብጻዊ እስላም የሀሰት ደብዳቤ ይዞ አባቄርሎስ ነኝ ብሎ በመምጣቱ የጵጵስና

አቀባበል እንደ ተደረገለት በቤተክርስቲያን ታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቧል፡፡ነገሩ ሀሰት እንደሆነ ሲሰማ ግን ወዲያውኑ ተይዞ እርምጃ ተወስዶበታል፡፡ከዚህም ሌላ ከአባ እንጦንስ ገዳም የተባረሩ ሚናስና ፊቅጦር የተባሉ መነኮሳት ከእስክንድርያ ፓትሪያርክ የተጻፈ አስመስለው የሐሰት ደብዳቤ ይዘው በመምጣት እንዲኖር አድርገዋል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ከክርስቲያኖች ይልቅ ለሙስሊሞች ወዳጅ የነበሩ፣ከአብያተ ክርስቲያናት ይልቅ መስኪዶችን ያሳነጹ ጳጳስም ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ውጭ በግብጽ ሱልጣኖች ፍላጎት ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ ተልእከዋል፡፡ለምሳሌ በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ሀገራችን የመጡት አቡነ ኪሮስ በኢትዮጵያ ሰባት መስጊዶችን ማሳነጻቸውና ሙስሊሞቹም በኢትዮጵያ እምነታቸውን እንዲያራምዱ ድጋፍ ይሰጧቸው ነበር፡፡

3.3.2. የዮዲት ጉዲት የጥፋት ዘመቻ

ዮዲት ጉዲት በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከምድረ ፍልስጤም ተነስተው ወደ ሀገራችን ከገቡት እስራኤላውያን ወገን እንደሆነች ይታመናል፡፡ ዮዲት በላስታ አካባቢ (ቡግና) ከሚኖሩ ፈላሾች እንደ ተወለደች ሲገመት በ9ኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ ገደማም ዘመዶቿን አስተባብራ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ የጥፋት ወረራዋን ጀምራለች፡፡ ለዮዲት ጉዲት መነሳት ዋነኛው ምክንያት በትክክል ምን እንደሆነ ባይታወቅም ከጥንት አባቶች (አይሁዳውያን) የዘለቀ ክርስቲያኖችን በጥላቻና ለክርስቲያኑ የአክሱም መንግስት ግብር ለመክፈል አለመፈለግ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ በዚህ ለ40 ዓመታት እንደቆየ በሚታመነው የጥፋት ዘመቻዋ ዮዲት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ከባድ ጉዳት አድርሳለች፡፡ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትና ቅዱሳት መካናት ተቃጥለዋል፡፡ ንዋያተ ቅዱሳት ወድመዋል፡፡ ሀውልቶች ተሰባብረዋል፡፡ ካህናትና ምእመናን ተገድለዋል፡ ፡የአክሱም መንግስት ጭራሹን ተዳክሞ ንጉሥ አንበሳ ወድም ወደ መንዝ ሸሽቷል፡፡ በዮዲት ወረራ ከፈራረሱት አብያተ ክርስቲያናት መካከልም በአብርሃና አጽብሃ ዘመን የተሰራችው የመጀመሪያዋ የአክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን ተገኝታለች፡፡በዚህ ጊዜም ካህናቱ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ዝዋይ ደሴት በመሰደዳቸው ታቦቷ ከዮዲት ጉዲት የጥፋት ዘመቻ ለመትረፍ ችላለች፡፡

3.4. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ዛጉዌ ሥርወ መንግሥት

ዛጉዌ የሚለው ስያሜ የሥርወ መንግሥቱ ተዋናዮች የነገደ አገው ተወላጆች ስለሆኑ የአገው መንግሥት ለማለት ‹‹ዘአገው›› ከሚለው ቃል እንደተወሰደ ብዙዎቹ ይስማሙበታል ለዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ነገሥታት የዘር ግንድ መሠረት የሆነው መራ ተክለሃይማኖት የአክሱም መንግሥት ካከተመ በኋላ በትረ መንግሥቱን ጨብጦ መናገሻ ከተማውን ወደ ላስታ በማዛወር በኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ለመጀመር ምክንትት ሆኗል፡፡ ከመራ ተክለሀይማኖት ጀምሮ ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ አስራ አንድ የዛጉዌ ነገስታት ኢትዮጵያን እንዳስተዳደሩ መረጃዎች ይጠቁማለ፡፡ከእነዚህም መካከል አራቱ ክህነትን ከንግስና ጋር አስተባብረው የያዙ እና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በቅድስናቸው የሚታወቁት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- ይምርሃነ ክርስቶስ
- ገብረማርያም (ሐርቤ)
- ላሊበላና
- ነአኩቶ ለአብ ናቸው፡፡

3.4.1. ካህናተ ነገሥታት

በእርግጥ ሁሉም የዛጉዌ ነገስታት ክርስቲኖች ስለነበሩ በየዲት ጉዲት የጥፋት ዘመቻ ምክንያት ተመናምኖ የነበረውን ክርስትና እንደገና እንዲንሰራራ፣ተስፋ የቆረጠውን ህዝበ ክርስቲያን እንዲጽናና፣የተቃጠሉ መጻሕፍት እንደገና እንዲጻፉና የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ ያደረጉት ጥረት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ የሚረሳ አይደለም፡፡ሆኖም ግን ከሁሉም በበለጠ እነዚህ አራቱ ነገስታት ሙሉ ሕይወታቸውን ለመንፈሳዊ ነገር አውለው አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ፣በጽድቅ ሥራቸው ሁሉ ለሕዝበ ክርስቲያን አርአያ በመሆን፣ የክርስትና ሃይማኖት እንዲከበር፣እንዲስፋፋና እንዲጠናከር በማድረግ በፍጹም ተጋድሎ ቤተክርስቲያንን ያገለገሉ ናቸው፡፡

3.4.2. የውጭ ግንኙነት

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች ክፍለ ዓለማት ጋር በነበራት ግንኙነት የረጅም ጊዜ ታሪክ አላት፡፡ የግንኙነቷ መሠረትና ዓይነተኛው ምክንያት ሃይማኖቷእ ንደነበር ይታወቃል፡፡በተለይ በዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ኢትዮጵያ ከግብጽና ከኢሩሣሌም ጋር የነበራት የጠበቀ ግንኙነት እንደ አብነት የሚጠቀስ ነው፡፡ለግብጽና ለኢትዮጵያ ግንኙነቶች መሠረታዊ ምክንያቶችም የዓባይ ወንዝ የእስክንድርያ ክርስቲያኖች እና ጳጳሳትን ወደ ኢትዮጵያ ማስመጣት ናቸው፡፡ለግብጻውያን የዓባይ ወንዝ ለጥንታዊ ሥልጣኔያቸው መሠረትና አሁንም ቢሆን የሕይወታቸው (የኑሯቸው) ዋስትና መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ከሀገራችን እንደሚነሳ የሚታወቀው የዓባይ ወንዝ በተለያየ ምክንያት ፍሰቱ እንዳይቋረጥባቸው መስጋት ግብጻውያን ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡አንድ አንዶቹ የዛጉዌ ነገሥታት በግብጽ ያለ ክርስቲያኖች ደህንነታቸው በአግባቡ ካልተጠበቀና ጳጳሳትን ወደ ሀገራችን መላክ ካልተቻለ የዐባይን ወንዝ እንገድባለን በማለት የግብጽ ሱልጣኖችን ያስፈራሯቸው እንደነበር በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ከኢየሩሣሌም ጋር የነበረው ግንኙነት መሠረቱ ደግሞ በርካታ ክርስቲያኖች ቅዱሳት መካናትን ለመጎብኘት ወደዚያው ያደርጉት የነበረው መንፈሳዊ ጉዞ ነበር፡፡ከዛጉዌ ነገሥታት መካከል ቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስና ቅዱስ ላሊበላ ኢየሩሣሌምን ሄደው እንደጎበኙም ተዘግቧል፡፡ከእነኝህ ነገሥታት በኋላ ላይ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ አብያተ ክርስቲያናትን ለማነጽ ያነሳሳቸው ዓብይ ነገር የኢየሩሣሌም ጉብኝታቸው እንደነበር ይታመናል፡፡

ቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ

የግብጽ ሙስሊም ሱልጣኖች በሀገራቸው (በእስክንድርያ) የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ስቃይ ሲያበዙባቸውና ሲያሳድዷቸው ክርስቲያኖችን ለመታደግና ሱልጣኖችን ለማስደንገጥ የዓባይን ወንዝ ለመገደብ ሙከራ ያደርግ እንደነበር በቤተክርስቲያን ታሪክ ተገልጿል፡፡ የቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስን ደግነት ክርስቲያናዊ የብቃት ደረጃውንና መንፈሳዊ አስተዳደሩን በዝና ሰምተው ይህንኑ ለማየት ከግብጽ ወደ አምስት ሺ የሚሆኑ ክርስቲያኖች ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ገድሉ ያስረዳል፡፡እነዚህም ክርስቲያኖች በጅሮአቸው የሰሙትን በዓይናቸው ስላዩትና በንጉሡ ገቢረ ተዓምራትና መንፈሳዊ ሕይወት ተመስጠው ወደ ሀገራቸው ሳይመለሱ እዚያው እንዳረፉ ይነገራል፡፡ እስከ ዛሬድረስ ዐፅመ ቅዱሳን ተብሎ ከመድረቁ በላይ ምንም ሳፈርስ በክብር አንድላይ ተሰብስቦ በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ በዋሻ ውስጥ የሚገኘው አፅም የእነርሱ እንደሆነ ይታመናል፡፡በዘመነ ይምርሃነ ክርስቶስ አቡነ ቄርሎስ የተባሉት የእስክንድርያው ፓትሪያርክ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ስለነበርም ታላቅ ደስታ ሆኖ ነበር፡፡ይምርሃነ ክርስቶስ ባረፉ ጊዜም አትናቴዎስና ያዕቆብ የሚባሉ ሁለት ግብጻውን ጳጳሳት ገንዘው እንደቀበሩት መጽሐፈ ገድሉ ይጠቅሳል፡፡

ቅዱስ ሀርቤ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከግብጽ ቤተክርስቲያን የሞግዚትነት አስተዳደር ተላቃ ራሷን እንድትችል የመጀመሪውን ጥያቄ በማቅረቡ ይዘከራል፡፡ጥያቄውንም ከኢትዮጵውን መካከል ተገቢ ናቸው የተባሉት ሰባት መነኮሳት ተመርጠው ለኤጲስ ቆጳስነት እንዲሾሙ በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩት አባ ሚካኤል በተባሉት ግብጻዊ ጳጳስ በኩል ለፓትሪያርኩ ለአባ ገብርኤል እንዲደርስ ተደረጎ ነበር፡፡ የቅዱስ ሀርቤ ጥያቄ መልስ ያገኘው በ1951 ዓ.ም እጨጌ ገብረጊዮርጊስ አቡነ ባስልዮስ ተብለው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ ሆነው ከተሾሙ ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ ነው፡፡

ቅዱስ ላሊበላ

በዘመኑ ከግብጻውን ጋር የነበረው ግንኙነት በመልካም ጎኑ የሚጠቀስና በአብዛኛው በወዳጅነት ላይ የተመሰረት ነበር፡፡ንጉሡ መልእክተኞቹን ከብዙ ገጸ በረከት ጋር አባ ሚካኤል የሚባሉ ጳጳስ ከእስክንድርያ አስመጥቶ የደመቀ አቀባበል እንደተደረገላቸው ተዘግቧል፡፡ቅዱስ ላሊበላ በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ወቅት ድል ከቀናው ሳላህዲን ከተባለ ግብጻዊ ሙልጣን ትልቅ ግምት የሚሰጣቸው ቅዱሳት መካናት ከኢየሩሳሌም በሥጦታ ተበርክቶለታል፡፡ ከእነዚህም መካናት መካከል በጎለጎታ የጌታ መቃብር አጠገብ ያለው እሌኒ ንግስት መስቀሉን ያስወጣችበት ዋሻና በቤቴልሔም ጌታ የተወለደበት በረት ይገኙበታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቅዱስ ላሊበላ ከሳላህዲን በኢየሩሳሌም ያሉ ቦታዎችን

በስጦታ ያገኘው ኢትዮጵያ በመስቀል ጦርነት ጊዜ ገለልተኛ ሆና በመቆየቷ ነው በማለት ትንታኔ የሚሰጡ በርካቶች ናቸው።።

በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት ታላቁ አባት ጻድቁ ገብረመንፈስቅዱስ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል።።በጻድቁ ገድል እንደተመለከተው ቅዱስ ላሊበላ የአቡነ ገብረመንፈስቅዱስን ላህይና ሁኔታ ተመልክቶ በጣም ተደስቶ የተለየ የክብር ቦታ ሰጣቸው።። እርሳቸውም ጥቂት ቀናት እያስተማሩ በሮሃ ቤተመንግስት ሰነበቱ።። ቅዱስ ላሊበላ በመቀጠልም አባቴ ቦታ ልስጥዎትና በዚሁ እየጸለዩ፣ እባረኩ፣ ወንጌልንም እያስተማሩ ይቀመጡ አሏቸው።።እሳቸው ግን እኔ እንዳስተምር እንደጸልይ የታዘዝኩት በደብረ ታቦር አምሳል በሆነች በዝቋላ ተራራ ስለሆነ ወደዛው እሄዳለው አንተ ግን ከተማህ የተባረከ ነው፣ አንተም የተባረክ ነህ ብለው ወደ ዝቋላ ለመሄድ ሲነሱ ዝቋላ ድረስ ሸኝቶ ሲመለስ እግረ መንገዱን የአዳዲ ማርያምን ቤተክርስቲያን እንዳነፃት ይነገራል።።

3.4.3. የዓለት ላይ አብያተ ክርስቲያናት ሥራ

የዛጉዌ ነገስታት ከሚታወቁባቸው ዓበይት ነገሮች አንዱና ዋነኛው ከተራራ ዋሻ ውስጥ በመገንባትና ከዓለት ላይ በመፈልፈል አብያተ ክርስቲናትን ማነጻቸው ነው።።እንዲህ ዓይነቱ ሥራ የተጀመረው በ6ኛው መ/ክ/ዘ በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ቢሆንም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የላቀ ደረጃ የደረሰው ግን በዛጉዌ ነገሥታት ነው።።በዚህ ዘመን ከዋሻ ውስጥና ከውቅር አለት አብያተ ክርስቲያናትን ማነው እንዲሁም ዝም ብሎ ሳይሆን ራሱን የቻለ ሃይማኖታዊ ትርጉምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድምታ ያለው ነው።።

እንደሚታወቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በቤቴልሄም ዋሻ ውስጥ ሲሆን የተቀበረው ደግሞ ዮሴፍ ለራሱ ጠርቦ ባዘጋጀው አዲስ መቃብር በጎለጎታ ነው።።ስለሆነም አብያተ ክርስቲያናት ከዋሻ ውስጥ መሠራታቸው የጌታችንን የትውልድ ቦታ (የቤቴልሔም ዋሻ) ከውቅር ዓለት መታነጻቸው ደግሞ የጌታችንን የመቃብር ቦታ (ጎለጎታን) የሚያስታውሱን ናቸው።።

የቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት

- ቤተ መድኃኔዓለም
- ቤተማርያም
- ቤተ አማኑኤል
- ቤተ መስቀል
- ቤተ ደናግል
- ቤተ መርቆሪዎስና
- ቤተ ደብረሲና
- ቤተ ጎልጎታ
- ቤተ ጊዮርጊስ
- ቤተ ገብርኤል
- ቤተ አባሊባስ

ምዕራፍ አራት

4. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በመካከለኛው የታሪክ ዘመን

ይህ ዘመን ከዛጉዌ መንግስት ማክተም ጀምሮ እስከ ዘመነ መሳፍንት ማብቂያ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል፡፡በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በርካታ ወርቃማ መንፈሳዊ ተግባራትን ያከናወነች ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ እጅግ በጣም አስከፊ የሆኑ ፈተናዎች ገጥመውታል፡፡

4.1. ወርቃማ መንፈሳዊ ክስተቶች

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክከ 13ኛው-15ኛው መ/ክ/ዘመን ያለውና በ17ኛው መ/ክ/ዘመን የነበረው የጎንደር ዘመነ መንግሥት ወርቃማ መንፈሳዊ ተግባራት የተከናወኑት ነበር ነው፡፡ከእነዚህም መካከል፡-

4.1.1. የገዳማዊ ሕይወት መስፋፋት

ገዳማዊ ሕይወት በአገራችን የተጀመረው በአምስተኛው መ/ክ/ዘመን ማብቂያ ላይ በዘጠኙ ቅዱሳን አማካኝነት ነው፡፡በተለይ በአቡነ አረጋዊ የተመሰረተው የደብረ ዳሞ ገዳም በሀገራችን ለገዳማዊ ሕይወት መስፋፋት መነሻ በመሆኑ ያበረከተው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም፡፡በዘጠኙ ቅዱሳን የተጀመረው ይኸው ገዳማዊ ሕይወት ከ13ኛው መ/ክ/ዘመን ጀምሮ ይበልጥ ተስፋፍቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ለዚህ ሁሉ መሠረት የሆነው ደግሞ አስቀድሞ በተገለጸው የደብረ ዳሞ ገዳም አበምኔት በአባ ዮሐኒ እጅ የመነኮሱትና ያገለገሉት አባ ኢየሱስ ሞዓ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ መጥተው የመሰረቱት የአንድነት ገዳም ነው፡፡የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በመካከለኛው የታሪክ ዘመን በሀገራችን የምንኩስና ሕይወት ማበብና ለገዳማት መስፋፋት ዋነኛ ማዕከል ሆኖ ያገለገለ ነው፡፡

ከሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም የተገኙ አባቶች

(የአባ ኢየሱስ ሞዓ ደቀ መዛሙርት)

የመሰረቱት	ገዳም
➢ አቡነ ተክለሃይማኖት	ደብረ ሊባኖስ
➢ አቡነ በጸሎተሚካኤል	
➢ አቡነ ጎሩተአምላክ	ደጋ እስጢፋኖስ (ሐይቅ እስጢፋኖስ)
➢ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ	ጋስጫ ገዳም

በአጠቃላይ በመካከለኛው ዘመን ከተመሰረቱት ገዳማት መካከል የደብረ ሊባኖስ፣ደብረ ምጥማቅ፣ ደብረ አስቦት፣ የጣና የዝዋይ ሐይቆች ገዳማት ይገኙበታል፡፡

4.1.2. የስብከተ ወንጌልና የትምህርተ ሃይማኖት መጠናከር

በሀገራችን የመካከለኛው ዘመን ታሪክ የገዳማት መስፋፋትና የቅዱሳን አበው በብዛት መኖር ለትምህርተ ሃይማኖት መጠናከርና ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡

የሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳም መሥራች አባ ኢየሱስ ሞዓ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሰባሰብና የትምህርት አደረጃጀትን በማጠናከር በርካታ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል፡፡ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ለሐዋርያዊ ተልዕኮ በተሰማሩበት ቦታ ገዳማትን ከመገደም ባሻገር የትምህርት ማዕከላትን አቋቁመዋል፡፡ሐዋርያዊ ተልዕኮ የፈጸሙ የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ፍሬዎች መካከል፡- አባ ኂሩተአምላክ፣ አቡነ አሮን፣ አባ በጸሎተሚካኤል፣ አባ ሠረቀብርሃን እና አቡነ ተክለሃይማኖት በዋናነት ይጠቀሳል፡፡

በመካከለኛው ዘመን የተነሱ ቅዱሳን ጣዖታትን በማፈራረስ፣ አረማውንን አሳምነው የክርስትና እምነት በመላው ኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ትልቅ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ለምሳሌ አቡነ ተክለሃይማኖት በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም በወላይታና ሐዲያ አካባቢዎች ያደረጉት ሐዋርያዊ አገልግሎት በግምባር ቀደምነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በዚሁ ዘመን የነበሩ ቅዱሳን ከትምህርተ ሃይማኖት ውጭ የሚሄዱትን ነገሥታት ሳይቀር በመገሠጻቸውም ይታወቃሉ፡፡ ለምሳሌ ዐፄ ዓምደጽዮን የአባቱን ሚስት (የእንጀራ እናቱን) ዕቁባት አድርጎ በመያዙ አቡነ ፊልጶስ የተባሉት ሦስተኛው የደብረ ሊባኖስ ዕጨጌ ፊልጶስ ከግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ ተቀብለው እንደ መምህራቸው እንደ አቡነ ተክለሃይማኖት ለትምህርተ ሃይማኖት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ዕጨጌ ፊልጶስ አሥራ አንድ ደቀመዛሙርትን መርጠው የንቡረ እድነት ማዕረግ በመስጠት ከእነርሱ ጋር በመሆን በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የክርስትና ትምህርት አስፋፍተዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በአክሱም አካባቢ የሚገኘው የደብረ በንኮል ገዳም መሥራች የሆኑት የአቡነ መድኃኒነ እግዚአ ደቀ መዛሙርት ሰባቱ ከዋክብትና አምስቱ ቅዱሳን በመባል የሚታወቁት ሲሆኑ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ትምህርተ ክርስትናን አስፋፍተዋል፡፡በተለይ ሰባቱ ከዋክብት የተባሉት አብዛኛው የጣና ሐይቅ ገዳማትን የመሰረቱ ናቸው፡፡

ዕጨጌ ፊሊጶስን ጨምሮ አሥራ አንዱ ንቡራነ ዕድ ሰባቱ ከዋክብትና አምስቱ ቅዱሳን በሀገራችን ላበረከቱት ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎትና የስብከተ ወንጌል መጠናከር በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ ቅዱሳን ብላ ትጠራቸዋለች፡፡

ከትምህርተ ሃይማኖት መስፋፋትና ከስብከተ ወንጌል መጠናከር ጋር በተያያዘ ከነገሥታት መካከል ዐፄ ዘርዐያዕቆብ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልዩ ቦታ አላቸው፡፡ ያበረከቱት አስተዋፅኦ፡-

- አምልኮተ ጣዖት ከምድረ ኢትዮጵያ እንዲጠፋ ለማድረግ ያደረጉት ተጋድሎ

- የቤተክርስቲያን በዓላት በሚገባ እንዲከበሩና አጽዋማትም በሥርዓት እንዲጸሙ ድንጋጌዎችን በማስተላለፍ
- ሕዝበ ክርስቲያኑን በሰንበት ቀን ከቅዳሴ በኋላ ትምህርተ ወንጌልን በሊቃውንት እንዲማር
- ካህናት ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌለበት ቦታ ሄደው እንዲያስተምሩ
- ምእመናን የነፍስ አባት እንዲኖራቸው እና የነፍስ አባቶችም ልጆቻቸውን ተግተው እንዲያስተምሩና እንዲመክሩ ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

ሰንጠረዥ 4.1

ተ.ቁ	ዕጨጌ ፊሊጶስና አሥራ አንዱ ንቡራነ ዕድ	ሰባቱ ክዋክብት (የአባ መድኅነኒ እግዚእ ደቀ መዛሙርት)	አምስቱ ቅዱሳን
1	ዕጨጌ ፊሊጶስ ዘደብረ ሊባኖስ	አባ ዮሐንስ	አባ ዘካርያስ
2	አኖሬዎስ ዘውረቢ (ታላቁ አኖሬዎስ)	አባ ታዴዎስ	አባ አሮን
3	ገብረክርስቶስ ዘደንቢው	አባ ያሳይ	አባ ገብረክርስቶስ
4	አኖሬዎስ ዘሞረት	አባ ያፍቅረነእግዚእ	አባ ዳንኤል
5	መርቆሬዎስ ዘመርሐቤቴ	አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ	አባ መርቆሬዋስ
6	ማትያስ ዘፈጠጋር	አባ ሳሙኤል ዘቆየዳ	
7	ቀውስጦስ ዘመሐግል	አባ ሳሙኤል ዘጣሬጦ	
8	ታዴዎስ ጽላልሽ		
9	ሳሙኤል ዘደብረወገግ		
10	ዮሴፍ ዘእናርያ		
11	ኢዮስያስ ዘውጂ (ዘክልኤቱ)		

4.1.3. የግዕዝ ስነጽሑፍ ዕድገት

በሀገራችን የጥንት ክርስቲያን የታሪክ ዘመን ቅዱሳት መጻሕፍትን ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ በመመለስ አባ ፍሬምናጦስና ዘጠኙ ቅዱሳን በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ከእነሱ በመቀጠልም ቅዱስ ያሬድ አምስቱን የዜማ መጻሕፍት በመድረስ ለመንፈሳዊ የግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ወደ መካከለኛው ዘመን ታሪክ ስንመጣ ደግሞ በርካታ መንፈሳዊ መጻሕፍት ወደ ግዕዝ ቋንቋ የተተረጎመበትና አያሌ ገድሎችና ድርሳናት የተጻፉበት በመሆኑ ዘመኑ ወርቃማው የግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ዘመን በመባል ይታወቃል፡፡

ወደ ግዕዝ ቋንቋ ከተተረጎሙት መካከል (በመካከለኛው ዘመን)

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ገድለ ሐዋርያት
- ተአምረ ማርያም
- ስንክሳር
- ውዳሴ ማርያም
- ድዲስቅልያ
- መጽሐፈአስቴር
- ደቂቅነቢያት
- ዜና አይሁድ
- ፍካሬ ኢየሱስ
- ግብረ ሕማማት
- መጽሐፈ ቅዳሴ
- መጽሐፈ ኪዳን
- ገድለ ጊዮርጊስ
- መጽሐፈኢሳይያስ
- ፍትሐነገሥት

በመካከለኛው ዘመን በሀገራችን ከተጻፉት ገድሎች መካከል፡-

- ገድለ ገብረ መንፈስቅዱስ
- አባ አረጋዊ
- አባ ፊሊጶስ
- አባ በጸሎተሚካኤል
- ላሊበላ
- ነአኩቶ ለአብ
- መስቀል ክብራ ይገኙበታል፡፡
- አቡነ ተክለሃይማኖት
- አባ ጴንጠሌዎን
- አባ አኖሬዎስ
- ይምርሐነ ክርስቶስ

በመካከለኛው ዘመን የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ጋር በተያያዘ በርካታ መጻሕፍትን በመድረሳቸው የሚታወቁቱ ከነገሥታት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከመነኮሳቱ ደግሞ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ናቸው፡፡

- ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ሰባት የሚሆኑ መጻሕፍትን ደርሰዋል፡፡ እነዚህም፡- መጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ምዕላድ፣ ጦማረ ትስብእት፣ ክህደተ ሰይጣን፣ መጽሐፈ ባሕርይ፣ጠዐቅቦ ምስጢርና እንግዚአብሔር ነግሰ የሚባሉት ናቸው፡፡
- አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ከአርባ በላይ መጻሕፍትን እንደጻፉ የሚነገር ሲሆን በደንብ ከሚታውቁት መካከልም፡- ክብረ ቅዱሳን፣ ተአምኖ ቅዱሳን፣ መጽሐፈ አርጋኖን፣ መጽሐፈ ሰዓታት፣ ውዳሴ መስቀል፣ መጽሐፈ ምስጢር. ሕማማተ ማርያም የሚባሉት ይገኙበታል፡፡ ከዚሁ ሳንወጣ የአባ ጽጌ ድንግል ማሕሌት ጽጌና በዕጨጌ ዕንባቆም የተጻፈው መጽሐፈ ቂደር የዚሁ ዘመን ታሪክ የሥነጽሑፍ አካላት ናቸው፡፡

4.1.4. የውጭ ግንኙነት

በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ጎልተው ከሚነገሩት የውጭ ግንኙነቶች መካከል፡-

ሀ) የግማደ መስቀሉ ወደ ሀገራችን መምጣት

እሌኒ ንግሥት አስቆፍራ ካስወጣቸው ጌታ ከተሰቀለበት መስቀል የቀኝ እጁ ያረፈበት የመስቀሉ ክፋይ (ግማደ መስቀሉ) ወደ ሀገራችን ከመምጣቱ ጋር የተያያዙ ሁለት ታሪኮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የነገሥታቱ የውጭ ግንኙነት ውጤት እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡

የመጀመሪያው የጌታችንን ግማደ መስቀል በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት (በ14ኛው መ/ክ/ዘመን) ከኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ መንግሥት ከሌሎች ንዋያተ ቅዱሳት ጋር በሥጦታ መልክ እንደተበረከተ የሚተረከው ነው፡፡ይኸውም ቀድሞ የነበረውን መልካም ወዳጅነትና ግንኙነት መሠረት በማድረግ ዐፄ ዳዊት ብዙ ገጸበረከትን አስጭነው ወደ ኢየሩሳሌም ፓትሪያርክ አባ ዮሐንስ መልእተኞችን በመላክ ግማደ መስቀሉን ሊያስመጡ ችለዋል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ንግስት እሌኒ አስቆፍራ ያስወጣችው የጌታ መስቀል ለአራት ተከፋፍሎ በዕጣ ለሮም፣ ለቁስጥንጥንያ፣ለእስክንድርያ ለአንያኪያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ተሰጠ ከሚለው ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው፡፡በወቅቱ የግብጽ ክርስቲያኖች ላይ ያደርሱት በነበረው ተጽዕኖና መከራ ምክንያት በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል አለመግባባት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሡ (የኢትዮጵያ) ዐፄ ዳዊት በግብጽ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁኔታቸው ካልተስተካከለ የአባይን ወንዝ እገድባለሁ ሲሉ በማስፈራራታቸውና በግብጻውያን ዘንድ ስጋት ስለተፈጠረ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ነገሩን በማርገብ የጌታ ቀኝ ያረፈበትን ግማደ መስቀል ለኢትዮጵያ መንግሥት በስጦታ መልክ እንዳበረከተችው ይተረካል፡፡ያም

ሆነ ይህ ግን የከበረው የጌታችን ግማደ መስቀል በዐጼ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ወደ ሀገራችን መግባቱ እርግጥ ነው፡፡ ከመስቀሉ ጋርም በወንጌላዊው ዩሐንስ የተሳለው ስርዓተ ርእሱ (ጌታ የእሾህ አክሊል ደፍቶ የሚያሳየው ስዕል)፣ ቅዱስ ሉቃስ የሳላት ምስል ፍቅር ወልዳ (እመቤታችን ልጇን ታቅፋ የሚያሳየው ስዕል) እና ሌሎችንም ንዋያተ ቅዱሳት አብረው በስጦታ መልክ ተበርክተዋል፡፡

ዐጼ ዳዊት መስቀሉን ከመንግድ ላይ ተቀብለው ሲመጡ ከተቀመጡበት በቅሎ ላይ በድንገት ወድቀው ሕይወታቸው በማለፉ ጉዳዩን ልጃቸው ዘርዓያዕቆብ ከፍጻሜው ሊያደርሰው እንደቻለ ይነገራል፡፡ዐፄ ዘርዓያዕቆብ መስቀሌን በመስቀልኛ ቦታ አስቀምጥ በማለት በሕልም ስለተነገራቸው መስቀልኛ ቦታ (ተራራ) በመፈለግ ብዙ አሰሳ ካደረጉ በኋላ አሁን ከሚገኙበት የግሸን ተራራ (ወሎ አምባሰል የሚገኝ) በክብር አስቀምጠውታል፡፡በዚህ መስቀልኛ የግሸን ተራራ ላይም የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን በመስቀል ቅርፅ በማሰራት ግማደ መስቀሉን በመስቀል ቅርጽ በወርቅ፣ በብር፣ በመዳብ ወዘተ ተለብዶ በተሠራ ሳጥን ውስጥ ሆኖ በክብር ከመንበሩ ሥር ተቀብሮ ይገኛል፡፡መስቀሉ ከተቀበረበት የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን በተጨማሪ ድንግል ማርያም፣የቅዱስ ሚካኤልና የቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት በዚሁ በመስቀልኛ ተራራ ላይ ይገኛል፡፡

መስቀሉ ወደ ሀገራችን የገባው መስከረም 10 ቀን ሲሆን የተቀጸል ጽጌ በዓልም የዐፄ መስቀል በዓል ተብሎ ከዚያው ጋር ተያይዞ መከበር ጀመረ፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ እሌኒ ንግሥት መስቀሉን ከተቀበረበት ቦታ (ጎለጎታ) ለማውጣት ቁፋሮ የጀመረችው መስከረም 17 ሲሆን መስቀሉ የወጣው ግን መጋቢት 10 ቀን እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የመስቀል በዓል ከዋዜማው ጀምሮ በየዓመቱ መስከረም 17 ቀን በሃገራችን በብሔራዊ ደረጃ እንዲከበር ተደርጓል፡፡ይህም የተጀመረው በዐጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነመንግሥት ነው፡፡በዐፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመን ለመስቀል የተሰጠው ክብር እጅግ ከፍያ ለስለነበር ምዕመናን በግምባራቸው፣ በእጃቸው፣ በአንገታቸው፣ በልብሶቻቸውና በጦር መሳሪያዎቻቸው የመስቀል ምልክት ማድረግና ማንጠልጠል እየተወደደና እየተለመደ መምጣት ጀመረ፡፡መንገደኛ ክርስቲያኖች በሩቅ ሆነው ቤተክርስቲያንን መሳለም እንዲችሉም በቤተክርስቲያን አቅጣጫ መንገድ ላይ የመስቀል ምልክት ማቆም የተጀመረው በዚሁ በዐፄ ዘርዐያዕቆብ ዘመን እንደነበር ይነገራል፡፡

ለ) የፍሎረንሱ የሃይማኖት ጉባኤ

የፍሎረንሱ የሃይማኖት ጉባኤ በኢጣሊያ ሀገር በፍሎረንስ ከተማ በዐፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመነመንግሥት የተደረገ ነው፡፡በጉባኤው የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የተወከለችው በኢየሩሣሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አበምኔት በነበሩት በአባ ኒቆዲሞስ በተላኩ መነኮሳት ነበር፡፡የጉባኤው መጠራት ዋና ዓላማ በወቅቱ በመስፋፋትና ኢየሩሣሌምን ጨምሮ የምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮችን በመቆጣጠር ላይ የነበረውን የቱርክ እስላም መንግሥታት በጋራ ለመታገል እንዲቻል ሁኔታዎችን በመምከር ለማመቻቸት ነበር፡፡ሆኖም ግን ስብሰባው መሠረታዊ ዓላማውን በመሳት የሮማው ፖፕ የበላይነት እንዲቀበሉ የሚል መንፈስ ስለነበረው ጉዳዩ

በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ስብሰባው ያለውጤት ሊበተን ችሏል።

ሐ) የደብረ ምጥማቅ ቤተክርስቲያን የተሠራችበት ምክንያት

በሀገራችን በተጉለት የምትገኘው የደብረ ምጥማቅ ቤተክርስቲያን ከመሰረቷት ዋነኛው ምክንያት በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል በወቅቱ የነበረው የሻከረ ግንኙነት እንደሆነ በታሪክ ተገልጿል በዚያን ጊዜ የነበረው የግብጹ ሡልጣን በግብጽ የምትገኘውን የደብረ ምጥማቅ ቤተክርስቲያን በግፍ በማፍረሱ በሁለቱም ሀገሮች የሚገኙ ክርስቲያኖችን እጅግ በጣም ያሳዘነ ጉዳይ ነበር።በዚህም ጊዜ የግብጽ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ ዐሥራ አንደኛ ለዐፄ ዘርዓያዕቆብ ቤተክርስቲያኗ በግፍ ስለመፍረሷ በደብዳቤስ ለገለጹለት በጉዳዩ እጅግ አዝኖ ከኢትዮጵያ ሕዝበክርስቲያን ጋር ለተወሰነ ጊዜ የምሕላ ጸሎት መያዙ ታውቋል።ወዲያውም ግብጽ በፈረሰቸው ቤተክርስቲያን ስም የተመሰየመችው የደብረ ምጥማቅ ቤተክርስቲያን በሀገራችን በተጉለት (ጻድቃኔ አካባቢ) ልትታነጽ ችላለች ታቦቷም በወቅቱ የነበሩት ጳጳሳት አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ተባርካ ገብታለች።

4.1.5. የኢትጵያ ቤተክርስቲያን በጎንደር ዘመነ መንግሥት (፲፮፻፵፰-፲፯፻፹፪)

በኢትዮጵያ ታሪክ የጎንደር ከተማ ከተመሰረተችበት ጀምሮ እስከ ዘመነ መሳፍንት መምጣት ድረስ ያለው የጎነደር ዘመነ መንግሥት በመባል ይታወቃል።የጎንደር ከተማ መሥራችና የመጀመሪያው የጎንደር ዘመነ መንግሥት ንጉሥ ዐፄ ፋሲለደስ ናቸው።የዐፄ ፋሲል አባት ዐፄ ሱስንዮስ ‹‹ኢየሱሳውያን›› ሚሲዮናውን (Jesuits) በተባሉ የሮም ካቶሊክ መልእክተኞች ውትወታ ምክንያት ሃይማኖታቸውን ቀይረው ይህንኑ የካቶሊክ እምነት ኢትዮጵያውያን እንዲቀበሉ ዐዋጅ በመንገራቸው በሀገሪቱ ውስጥ የእርስ በእርስ ጦርነትና ብዙ ደም መፋሰስ ተከስቶ ነበር።በዚህ የተነሳ ዐፄሱስንዮስ ሥልጣናቸውን ለቀው ለልጃቸው ዐፄ ፋሲል እንዲያስረክቡ የግድ ሁኗል።ዐፄ ፋሲል ወደ ሥልጣን እንደመጡ በመጀመሪያ ዐዋጃቸው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ይመለስ፣ የካቶሊክ እምነት ይፍለስ›› በማለት የደፈረሰውን ሁኔታ መልሰው በአገራችን መረጋጋት እንዲመጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድረገዋል በቅዱስ መጻሕፍት ትርጓሜ ሥር ያሉትን የመጻሕፍተ ብሉያትን፣ሐዲሳትን ሊቃውንትና መነኮሳትን አጠናቀው የሚያውቁ ሊቃውንት ዐራት አይና እየተባሉ መጠራት የጀመሩትም በጎንደር ዘመነ መንግሥት ነው።

በጎንደር ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትና ትውፊት መሠረት የሚሣል የመንፈሳዊ ሥዕሎችም ጥበብ የላቀ ደረጃ ደርሶ ነበር። እነዚህ ሥዕሎች የአብያተ ክርስቲያናቱ ግድግዳ፣ በሸራ፣ በብራና፣ በገበታ፣ በወረቀት እና በመስቀሎች ላይ በቀለም ወይም በጭረት ባለሁለት ጎን (two dimensional) ሆነው ይሣሉ የነበሩ ናቸው። ስዕሎቹም በተለይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን፣ የቅዱሳን መላእክትን፣ ጻድቃንና

ሰማእታትን እና በቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ላይ ያሉ ገጸባሕርያትን የሚወክሉ ናቸው፡፡ በጎንደር ዘመነመንግሥት በተሣሉ እጅግ ማራኪ ሥዕሎች የተዋቡ አብያተ ክርስቲያናት በርካታ ናቸው፡፡ከእነዚህም መካከል በዐፄ አዲያምሰገድ ኢያሱ የተሠራው የደብረ ብርሃ ዘን ሥላሴ ቤተክርስቲያን፣ የዐፄ ፋሲለደስ እኅት ወ/ሮ መለኮታዊት ያሳሉት የጎንደራ ደብረ ሲናማርያም ገዳም ሥዕሎችና እቴጌ ምንትዋብ ያሳሉት በጣና የናርጋ ሥላሴ ገዳም ተጠቃሾች ናቸው፡፡በተለይ የጣራው ክፍል በብዛትና ባማሩ የመላዕክት ሥዕሎች ያጌጠው የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተክረስቲያን በቱርሲት መስህብነቱ የታወቀነው፡፡በጥቅሉ የጎንደር ዘመነ መንግሥት ለጥንታዊ የቤተክርስቲያን ትምህርትና ለቅዱሳት ሥዕላት ወርቃማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ የሚችል ነው፡፡

4.2. ዓበይት የቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች

በመካከለኛው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዘመን ታሪክ ቤተክርስቲያን ከውስጥም ከውጭም በመጡ ፈተናዎች በርካታ የመከራ ጊዜያትን አሳልፋለች፡፡በዚያን ዘመን ከነበሩት የቤተክርስቲን ፈተናዎች አንዳንዶቹ ጠባሳዎች እስከ አለንበት ዘመን ከገጠሟት ፈተናዎች መካከልም የደቂቀ እስጢፋ የተቃውሞ ትምህርት፣ የአሕመድ ግራኝ ጦርነት የሐሳዊ መሲሕ መነሳት፣ የካቶሊክ ሚሶናውያን ትንኮሳና የዘመነ መሳፍንቱ ክፍፍል በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

4.2.1. የደቂቀ እስጢፋ የተቃውሞ ትምህርት

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሚነገረው መሰረት ደቂቀ እስጢፋ (የእስጢፋኖስ ልጆች) በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተለየ ትምህርት ያስተምሩ ነበር፡፡ይኸውም ለቅድስት ድንግል ማርያምና ለቅዱስ መስቀል ስግደት ክብር አይገባም የሚል ሲሆን ጉዳዩም ተባብሶ በዘመኑ ከነበሩት ንጉስ ዘርዓያዕቆብ ጋር ከፍተኛ አለመግባባት ውስጥ ገብተው እንደነበር ይነገራል፡፡

4.2.2. የቤተ ተክለሃይማኖትና የቤተ ኤውስጣቴዎስ አለመግባባት

አቡነ ተክለሃይማኖትና አቡነኤውስጣቴዎስ በመካከለኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተነሡት ታላላቅ ቅዱሳን አበው መካከል በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

አቡነ ተክለሃይማኖት የደብረ ሊባኖስ ገዳም መሥራችና በደቡብ የአገራችን ክፍል ሌሎች ገዳማትንና ትምህርተ ክርስትናን ያስፋፉ ታላቅ ሐዋርያ ናቸው፡፡አቡነ ኤውስጣቴዎስ ደግሞ በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይ በኤርትራ አካባቢ ከዚያም አልፈው

በአርመንያ (በውጭ አገር) ትምህርተ ክርስትናን ያስፋፉ ታላቅ የወንጌል ሰው ናቸው፡፡ ከፋሌ ባሕር በመባል የሚታወቁት አቡነ ኤውስጣቴዎስ ትምህርተ ክርስትናን ከማስፋፋታቸው ባሻገር ብዙ ገዳማትን ያቀኑና በርካታ ደቀመዛሙርትን ያፈሩ ቅዱስ አባት ናቸው፡፡የእነዚህን ሁለት ታላላቅ ቅዱሳን አበው የተከተሉት ገዳማትና የመንፈሳዊ ትምህርት ማዕከላትም ቤተ ተክለሃይማኖትና በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ቤተ ኤውስጣቴዎስ ደግሞ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ጉልህ እንቅስቃሴና ጠንካራ መሠረት ነበራቸው፡፡

በእነዚህ ሁለት ቅዱሳን አበው የሚጠሩት መንፈሳዊያን ማዕከላት (ቤተ ኤውስጣቴዎስና ቤተ ተክለሃይማኖት) በ፲፩ኛው መቶክ/ዘመን በነበረው አለመግባባት የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ትልቅ የመከፋፈል አደጋ ተጋርጦባት ነበር፡፡ ያለመግባባታቸው ምክንያትም የቀዳሚት ሰንበት መከበር ጉዳይ ነው፡፡የአባኤውስጣቴዎስ ተከታዮች (ቤተ ኤውስጣቴዎስ) ቀዳሚት ሰንበትን ከዕለተ እሑድ ጋር እኩል መከበር ይገባታል ሲሉ በግብጻዊ ጳጳስ ተጽዕኖ ሥር የነበሩት የአቡነ ተክለሃይማኖት ተከታዮች (ቤተ ተክለሃይማኖት) ደግሞ ቅዳሜን ማክበር የአይሁድ ባህል ስለሆነ ክርስቲያኖች ማክበር ያለብን እሑድን ብቻ ነው ይሉ ነበር፡፡በዚህ ምክንያት የነበረውን ውዝግብ እየተባባሰ በመሄዱ በወቅቱ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እጅግ ፈታኝ ክስተት ነበር፡፡ጉዳዩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ እ.ኤ.አ በ፩፹፬፱፱ ዓ.ም በዐፄ ዘርዐያዕቆብ ትእዛዝ በደብረ ምጥማቅ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት ጉባኤ ተደረገ፡፡ በጉባኤውም በርካታ የገዳማት አበምኔቶች፣ አድባራት አለቆች እንዲሁም ጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል በተገኙበት በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ በመጨረሻም ሁለት ሰንበታት (ቅዳሜና እሁድ) በእኩልነት ደረጃ በመላ ሀገሪቱ እንዲከበሩ ስለተወሰነ ለበርካታ ዓመታት የነበረው ውዝግብ መፍትሔ ሊያገኝ ችሏል፡፡የደብረ ምጥማቁ የሃይማኖት ጉባኤም ቤተክርስቲያን ብቻ ሳትሆን አገራችንም አንድነቷን ጠብቃ እንድትዘልቅ ያደረገው አስተዋጽኦ ታላቅ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡

4.2.3. የአሕመድ ግራኝ ጦርነት

በአጤ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት (፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን) የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እጅግ አሠቃቂ መከራ ደርሶበታል፡፡ይኸውም የአህመድ ግራኝ ጦርነት ነው፡፡አሕመድ ግራኝ ሙሉ ስሙ አህመድ ኢብን ጋህዚ ሲሆን እርሱም በወቅቱ ሐረርና አካባቢውን ማዕከል ያደረጉ የአዳል እስላሞች መሪ ነበር፡፡በኢትዮጵያ የታሪክ ትምህርት ለአህመድ ግራኝ ጦርነት ዋና ምክንያቱ በወቅቱ የምጣኔ ሃብት መሠረት የነበረችውን የዘይላ ወደብ የንግድ መስመር ለመቆጣጠር ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር የነበረው ፉክክር እንደነበር ያስረዳል፡፡በክርስቲያኑ መንግሥትና በአዳል ሙስሊሞች የተደረገው ይህ ጦርነት እ.ኤ.አ በ፩፹፭፻፳ ዓ.ም ተጀምሮ ከ፲፭ አመታት ላላነሰ ጊዜ ቆይቷል፡፡በአሕመድ ግራኝ ይመሩ የነበሩት አዳሎች የኦቶማን ቱርክን እርዳታ በማግኘታቸው እ.ኤ.አ በ፩፹፭፻፳፱ ዓ.ም በአጤ ልብነ ድንግል የሚመራውን የክርስቲያን ሠራዊት ሽንብራ ኩሬ

(ሞጆ አካባቢ) ከተባለ ቦታ ላይ ድል በማድረግ ግስጋሴያቸውን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጥለዋል፡፡በጦርነቱ ላይ ድል የተመታው ዐፄ ልብነድንግል ወደ ትግራይ በመሸሽ በስተመጨረሻም ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም አቅንቶ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ እ.ኤ.አ በ፩፶፫፱ ድረስ እዚያው ተቀምጧል፡፡እ.ኤ.አ በ፩፶፫፱ ዓ.ም ፖስኮ ደጋማ በተባለ መሪ አራት መቶ የሚደርሱ የፖርቹጋል ወታደሮች ወደ አገራችን ገብተው በወቅቱ በዐፄ ልብነድንግል ልጅ ዐፄ ገላውዴዎ ስለሚመራው የክርስቲያኑ ጦር ወታደራዊ ድጋፍ በማድረጋቸው ከሁለት ዓመት በኋላ (በ፩፶፫፱፱፭ዓ.ም) ለዓመታት የነበረው ጦርነት ሊያከትም ችሏል፡፡ በመጨረሻም ወይና ደጋ (ማና አካባቢ) ከተባለ ቦታ ጦርነት ተደርጎ አዳሎቹ ሊሸነፉና አለቃቸው አሕመድ ግራኝም ሊገደል በመቻሉ ለዘመናት የዘለቀው ጦርነት በክርስቲያኖቹ ድል ተደመደመ፡፡

ከዚሁ ታሪክ ሳንወጣ የፖርቹጋል ወታደራዊ እርዳታ መነሻው ቀደም ብሎ የአዳሎቹ እንቅስቃሴ ባስፈራት እቴጌ እሌኒ (የአጤ ልብነድንግል እናት) ለፖርቱጋል መንግሥት የቀረበው ጥያቄ ነበር፡፡ፖርቹጋል በመካከለኛው ዘመን ከኢትዮጵያ ጋር የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማድረግ የመጀመሪያዋ አውሮፓዊት አገር ናት፡፡የዚህ ዲፕሎማሲ ዊግንኙነት አጀማመር መሠረትም ቁሱ ንጉሥ ዩሐንስ ብለው በመስቀል ጦርነት ሽንፈት የገጠማቸው ምዕራባውያን ካቶሊኮች የፈጠሩት ሐሳባዊ ንጉሥ ነው፡፡እነዚህ ምዕራባውያን በተለይ ፖርቹጋሎች በደረሰባቸው ተደጋጋሚ ሽንፈት ምክንያት የዚህን በምናባቸው የፈጠሩትን ጠንካራ ሀብታም የክርስቲያን ንጉሥ እገዛ ለማግኘትና ከእርሱ ጋር ሆነው ሙስሊሞችን ከመሐል ላይ ጨፍልቆ ለማጥፋት የዚህን ንጉሥ አድራሻ ማፈላለግ ጀምረዋል፡፡ በስተመጨረሻ ንጉሡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው ብለው በመገመታቸው በኋላ ላይ በሁለቱ አገሮች ለተደረገው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሠረት ጥሎ እንዳለፈ ታሪክ ያስረዳል፡፡ ንግሥት እሌኒ ያቀረበችው ጥያቄ ለጊዜው ፍራንሲስኮ አልባሬዝ በተባለ ካቶሊካዊ ቄስ የሚመራ ቡድን እ.ኤ.አ በ፩፶፫፱፳ ላይ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ይህ ቡድን ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ለስድስት ዓመታት በስለላና አገሪቱን በማጥናት የቆየ ሲሆን በመጨረሻም ጦርነቱ ሊጀመር አንድ ዓመት ሲቀረው (እ.ኤ.አ በ፩፶፫፱፭፮ ዓ.ም) ባዶ ተስፋ በመስጠት አገሪቱን ለቆ ወጥቷል፡፡በጦርነቱ ብዙ ጥፋትና ውድመት ከደረሰ ከዐሥራ አምስት ዓመታት በኋላም የፖርቹጋል መንግሥት አስቀድሞ እንደተገለጸው በፖስኮደጋማ የተመራውን ወታደራዊ ኃይል ወደ አገራችን ሊልክ ችሏል፡፡

የአህመድ ግራኝ ጦርነት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ያደረሰው ጥፋት በቀላል የሚገመት አይደለም፡፡ በዚህ የጥፋት ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እጅግ ብዙ ነገር አጥታለች፡፡ በኢትዮጵያ የጠረፍና ቆላማ አካባቢዎች ተወስኖ የነበረው የእስልምና እምነት ወደ ተለያዩየ አገራችን ክፍሎች ሊስፋፋና በርካታ ተከታዮችን ሊያገኝ ችሏል፡፡ በትግራይ፣ በጎንደር፣ በወሎ፣ በሸዋና በባሌ አካባቢ የነበሩ ክርስቲያኖችም በግድ እስልምናን እንዲቀበሉ ተደርገዋል፡፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ያሉ በርካታ ገዳማትና አድባራት ከንዋየ ቅዱሳቱ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍቱ፣ከመነኮሳቱና ከካህናቱ ጋር አብረው ተቃጥለዋል፡፡በግራኝ የወረራና የጥፋት ዘመናት ከወደሙት ገዳማትና አድባራት መካከልም ደብረ ሊባኖስና አክሱምጽዮን ይገኙበታል፡፡ ከጦርነቱ በፊት የማይታወቁ ኢ-ክርስቲያናዊ ምግባራትም በአገራችን እየተለመዱ መጡ፡፡ለምሳሌ ያለካህን ፈቃድና

ያለሥርዓተ ተክሊል ማግባት፣ እቁባት መያዝ፣ በሆነባልሆነው መፋታት፣ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጆች መውለድና የመሳሰሉት የአሕመድ ግራኝ ጦርነት አሉታዊ ውጤቶች ናቸው፡፡ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም ቸል እየተባለ የመጣውና በአገራችን አረማዊ ድርጊቶች እየተወረሱ የመጡትም ከአሕመድ ግራኝ ጦርነት በኋላ ነው፡፡ባልተለመደ መልኩ ምዕመን ከንሰሐ ከቁርባን እና ከሥርዐተ ተክሊል በመራቅ የአሕዛብን ኑሮ መኖር ጀመሩ፡፡ በዚሁ የጦርነትና የመከራ ዘመን ምክንያት ብዙ የክርስትና መካናት የስም ተፋልሶ ደርሶባቸዋል፡፡ለምሳሌ አቡነ ተክለሃይማኖት ደቀ መዝሙር በአባ አኖሬዎስስም ይታወቅ የነበረው በባሌ የሚገኝ ቦታ ዛሬ ‹‹ኑራ ሑሴን››በመባል ይጠራል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከአሕመድ ግራኝ አስከፊ የጥፋት ዘመቻ ታቦታትን፣ ንዋያተ ቅዱሳንና ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማትረፍ አባቶቻችን ያደረጉት ተጋድሎ የሚረሳ አይደለም፡፡አባቶቻችን እነዚህን የከበሩ የቤተክርስቲያን ሃብቶች ይዘው በመሰደድ አሕመድ ግራኝ ከማይደርስባቸው ቦታዎች ለመደበቅ በመቻላቸው ቤተክርስቲያን ከውድመት እና ከቃጠሎ የተረፉ የተወሰኑ መተኪያ የሌላቸውን ቅርሶች ልታቆይችላለች፡፡ለምሳሌ ታቦተ ጽዮን ከግራኝ ቃጠሎ ተርፋ ለዚህ ትውልድ ልትደርስ የቻለችው በወቅቱ የነበሩት አበው ታቦቷን ይዘው ወደ ዝዋይ ሀይቅ በመሸሻቸው ነው፡፡ከጦርነቱ በኋላ የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ ዕምባቆም መጽሐፈ ቄዴር በማዘጋጀት በግዳጅ ወደ እስልምና የተቀየሩት (የገቡት) ምዕመናን ይኸው መጽሐፈ ጸሎት እየተደገመላቸው እና ጸበል እየተረጨ ብዙዎቹን ወደ ቀደመው እምነታቸው እንዲመለሱ አድርገዋቸዋል፡፡

4.2.4. የካቶሊክ ሚሲዮናዊያን ትንኮሳ

የአሕመድ ግራኝ ጦርነት ካከተመ በኋላ የፖርቹጋል ካቶሊክ ሚሲዮናውያን (Jesuits) የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያንን ዕረፍት ነስተዋል፡፡አስቀድሞ የፖርቹጋል መንግሥት ለኢትዮጵያ የሠጠውን ወታደራዊ ርዳታ እንደውለታ በመቁጠር ከዐፄ ገላውዲዎስ ጀምሮ የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት የካቶሊክን እምነት ካልተቀበላች ሁእያሉ መነዝነዝ ጀመሩ፡፡ በዚህም የተነሣ አጤ ገላውዲዎስ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እምነትን የሚገልጽ (Confession of Gelawdios) ጽሑፍ አዘጋጅተው ለማስተላለፍ እንደቻሉ በታሪክ ተመዝግቧል፡፡የካቶሊክን እምነት ወደ አገራችን ለማስገባትም የፖርቱጋል መንግሥት በተከታታይ በርካታ ሚሲዮናዊያንን ወደ ኢትዮጵያ ልኳል፡፡ከሚሲዮናውያኑ መካከል በተለይቤርሙዴዝ፣ አንድሬ ኦቪያዶ፣ጴጥሮስ ፓኤዝ እና አልፎንሶ ሜንዴዝ በሀገራችን ለነበረው ትርምስ እና አለመረጋጋት የጎላ አስተዋጽኦ የነበራቸው እና በደንብ የሚታወቁት ናቸው፡፡

ሚሲዮናውያኑ ከሃይማኖት ጅንጀናቸው ባሻገር የኢትዮጵን መሬት ቆርሰው ለፖርቹጋል መንግሥት ለመስጠት ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ሚሲዮናውያን አስቀድሞ ስለሀገሪቱ ባህል እና ቋንቋ ለማስተማር በሚል መንፈስ ‹‹የኢትዮጵኛ ኮሌጅ›› በማለት በቫቲካን ትምህርት ቤት እስከ ማቋቋም ደርሰዋል፡፡እነዚህ ሚሲዮናውያን በየቦታው በሆነ ባለሆነው የሃይማኖት ክርክር እንዲነሳ በማድረግ፣በነገስታቱ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ በመክፈት፣ከሙስሊሞቹ ጋር ሳይቀር በመመሳጠር ነገስታት

ለመግደል በማሴር፣የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ካህናት በመንቀፍ እና በማቃለል እንዲሁም በቤተክርስቲያን የተለመዱ ባህላዊ እሴቶቻችን በማንቋሸሽ በአገራችን ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡

ሚሲዮናውያኑ ለብዙ አመታት ኢትዮጵያውንን ወደ ካቶሊክነት ለመቀየር ብዙ ጥረት ቢያደርጉም የተሳካላቸው ግን በሱስንዮስ ዘመን መንግስት ነበር፡፡ከዚህ በፊት ከአንዳንድ ሁኔታዎች አንጻር ዐፄ ዘድንግል ካቶሊክ ሆነዋል ተብለው ውስጥ ለውስጥ ቢታሙም በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን ግን ሁሉም ነገር በግልጽ እና በይፋ ታወጀ፡፡በተለይ ጴጥሮስ ፓኤዝ የተባለው ሚሲዮናው ፊሊጣዊ አካሄዳዱ ንጉሱ ዐፄ ሱስንዮስን ከነቤተሰቡ የካቶሊኩን እምነት እንዲቀበል በማድረግ ተሳክቶለታል፡፡ፓኤዝ ለመመሳሰል ሲል የግዕዝ ቋንቋን እና ስርአተ ቅዳሴን ተምሮ ይሰብክና ይቀድስ እንደነበረ ተመዝግቧል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ዐፄ ሱስንዮስን በደካማ ጎኑ ገብቶ የሮማን ካቶሊክ እምነት ብትቀበል የፖርቹጋል መንግስት የጦር መሣሪያ ይረዳሃል፤ ስለሆነም ጠላቶችህ (መሳፍንቱን) በሰላም እንዲገዙልህ ያደርጋል በማለት ያታልለው እንደነበር ታውቋል፡፡

ፓኤዝ ከሞተ በኋላ በእርሱ እግር የተተካው አልፎንዙ ሜንዴዝ ጭራሹኑ ጥበብ የጎደለው እና ዘደኛ ላልነበረ ዐጼ ስስንዮስን በመገፋፋት ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እምነት እና ስርአት ተቃራኒ የሆነ አዋጅ እንዲውጁ እና ትርምሱ እንዲብስበት አድርጎታል፡፡በዚህ ወቅት ከታወጁ አዋጆች መካከልም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እንደገና እንጠመቁ፣ ካህናቱ እንደገና ሥልጣነ ክህነት እንዲቀበለ፣አብያተ ክርስቲያናቱ እንደአዲስ በካቶሊካውያኑ እንዲባረኩ፣በየአብያተ ክርስቲናቱ ያለው በኦርቶዶክሳውያን ስርአት የተሳለው ስዕል ቀርቶ የተቀረጸ ምስል እንዲቆም፣የሮማውያኑ የቅዳሴ ስርዓት እና የያም መቁጠሪያ በኢትዮጵያ ተግባራዊ እንዲሆን፣በረቡዕ እና አርብ ፈንታ ቅዳሜ እንዲጾም፣ ቀዳሚት ሰንበት እንዲሻር እና የመሳሰሉት የሚሉት ይገኙበታል፡ ፡ይህን አዋጅ በመቃወም በጊዜው የነበሩትን አቡነ ስምኦን የተባሉትን ጳጳስ ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ለእምነታቸው ሲሉ በጦርነት ተዋግተው ሞተዋል፡፡በዚሁ ምክንያት በላስታ አካባቢ ብቻ ወደ ስምነት ሺህ ገበሬዎች ለሃይማኖታቸው ሲሉ ህይወታቸው እንዳለፈ ተመዝግቧል፡፡በተቃውሞ የተናደዱ ሚሲዮናውያን ይብስብለው የኢትዮጵውያን ቅዱሳን አጽም ካረፈበት እያወጡ ያቃጥሉ እንደነበር እና በኦርቶዶክሳውያኑ ላይ ጭካኔ የተሞላበት ስቃይ ያደርሱባቸው እንደነበር ታውቋል፡፡በዚሁ የመከራ ዘመን ታላቅ ተጋድሎ ካደረጉት ቅዱሳን መካከል ወለተጴጥሮስ በዋናነት ትጠቀሳለች ይህች ቅድስት እናት ስዕለ ክርስቶስ የተባለ የዐፄ ስስንዮስ ወንድም እና የጦር አበጋዝ ሚስት የነበረች ቢሆንም በታወጀው የካቶሊክ ዕምነትን አልቀበልም በማለቷ ምክንያት ከቤተሰቦቿ ተለይታ ብዙ ተጋድሎ ማድረጓ እና ወደ ገዳም ገብታ ቀሪ ህይወቷን በምንኩስና እና በቅድስና እንዳሳለፈች ተመዝግቧል፡፡

4.2.5. የሐሳዊ መሲሕ መነሳት

በመካከለኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ታሪክ ከታዩት አስገራሚና አሳዛኝ ክስተቶች መካከል የሐሳዊ መሲሕ መነሳት አንዱ ነው፡፡ይህ ሰው በዐፄ ዘድንግል ዘመነ መንግስት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን በማስመሰል መቶ ሃያ የሐሰት ሰዎችን አሰባስቦ ራሱን እንደ ጌታ በመቁጠር የክሕደት ትምሕርቱን ማስተላለፍ ጀምሮ ነበር፡፡በወሎ አምሃራ ሳይንት በተባለው ቦታ የተነሳው ይህ ሰው እና ቱመርዓተ ወንጌል የምትባል ስትሆን ዐሥራ ሁለት የሐሰት ሐዋርያትን፣ሠላሳ ስድስት የሐሰት ቅዱሳን እንስትን እና ሰባ ሁለት የሐሰት አርድዕትን በመምረጥ ቅሰጣ ማድረጉ ተረጋግጧል፡፡ከሁሉም የሚደንቀው ነገር ይህ የሐሰት መሲህ ወደ ንጉሡ ተይዞ ቀርቦ ማንነቱን ሲጠየቅ የሰጠው መልስ ነው፡፡ ‹‹ከዚህ ቀደም ከድንግል ማርም ተወልጄ ወደ ዓለም የመጣሁት እኔ ክርስቶስ ነኝ፡፡ እንደምታውቁትም ለሰው ልጆች ስል ሞቼ ተነስቼ ወደ ሰማይ አርጌ ነበር፡፡ሆኖም ግን ከቤተ እስራኤል በመወለዴ ምክንያት እስራኤላውያን ያልሆኑ ሁሉ ባዕድ አደረገኝ ብለው እንዳይቀየሙኝ ከቤተ አሕዛብ ወገን ከምትሆን ከመርዓተ ወንጌል ዳግመና ተወለድኩ›› በማለት በድፍረት በመናገሩ ንጉሡ ‹‹ሰይጣን በሰው እያደረ ይጫወትብናል›› ብለው በሰይፍ እንዲቀጣ እንዳስደረጉት ተጽፏል፡፡

4.2.6. የዘመነ መሳፍንቱ ክፍፍል

ዘመነ መሳፍንት ሀገራችን በታሪክ ካሳለፈቻቸው የጨለማ ዘመናት አንዱ ነው፡፡ይህ ዘመን በመሳፍንቱ ተከፋፍላ በሀገራችን ብሔራዊና የአንድነት ስሜት የተዳከመበት ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ለይስሙላ የሚነግሡ ነገሥታት ቢሆንም ሀገሪቷን በመከፋፈል የሚያስተዳድሯት ግን መሳፍንቱ ነበር፡፡በመሳፍንቱ መካከል የነበረው የእርስ በርስ ጦርነት ሀገራችንን ለበርካታ ዘመናት የሁከትና የትርምስ ምድር አድርጓታል፡፡

- የዘመነ መሳፍንቱ ክፍፍል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን በብዙ መንገድ ጎድቷታል፡፡
- በርካታ ሚስዮናውያን ወደ ሀገራችን በመግባት በሀገራችን የሃይማኖት ልዩነት እንዲሰፋና የክህደት ትምህርታቸውን እንዲያሰራጩ ዕድሉን አግኝተዋል፡፡ከአሕመድ ግራኝ ጦርነት በኋላ እስልምና በኢትዮጵያ በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በጣም የተስፋፋውም በዘመነ መሳፍንት ነው፡፡
- በዚሁ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በርካታ ንዋያተ ቅዱሳትንም አጥታለች፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በደቡብና ምዕራብ የሀገራችን ክፍል የነበሩ በርካታ ክርስቲያኖችም ለዘመናት የሚያስተምርና ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን የሚፈጽም ካህን ባለማግኘታቸው ጠፍተው ከርመው ከብዙ ኣመታት በኋላ የክርስትና እምነታቸውን ረስተው ወደ እስልምና እና ወደ ዓረማዊነት ሊቀየሩ ችለዋል፡፡
- በዘመነ መሳፍንቱ ክፍፍል በተፈጠረ ክፍተት ምክንያትም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም ከነበሯት በርካታ ቦታዎች ብዙዎቹን በሌሎች ተቀምታለች፡፡በዚህ ዘመን ኢትዮጵውያን ክርስቲያኖች በየዓመቱ ለትንሳኤ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ያደርጉት የነበረውን ጉዞ በማቋረጣቸው እዛ የነበሩት መነኮሳትም በችግርና በረኃብ በማለቃቸውና በመሳሰሉት ምክንያቶች የኢትዮጵያ ይዞታቸው ጠፍ ሁነው ከርመው ባለቤት በመጥፋቱ በሌሎች በተለይም በግሪኮች እና በአርመኖች እንደተወሰዱባት ታውቋል፡፡

የዘመነ መሳፍንቱ ትርምስ እንዲባባስ ያደረገው ሌላው ነገር ቅባትና ጸጋ የሚባሉ ተመሳሳይ የሆኑ የእምነት ዓይነቶች በመፈጠራቸው ነው፡፡ቅባትና ጸጋ ቀደም ብሎ በዐፄ

ፋሲል በተባረሩ የካቶሊክን የሁለት ባሕርይ እምነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያንጸባርቁ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡በእነዚህ ሁለት ተመሳሳይ እምነቶች ምክንያት ከተዋሕዶ ሊቃውንት ጋር በርካታ ክርክሮች እንደተደረጉና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ችግር መፍትሔ ያገኘውና ጋብ ያለው በዐፄ ዩሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ይታወቃል፡፡

ምዕራፍ አምስት

5. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዘመናዊ ታሪክ

በሀገራችን የዘመናዊ ታሪክ የሚባለው ከዐፄቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት (1847-1860 ዓም) ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜያችን ድረስ ያለውን የሚያካትት ነው።

5.1. ነገሥታቱና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

5.1.1. ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (1847-1860)

ዐፄ ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት ማብቂያ ላይ ካሣ ኃይሉ በመባል የቀድሞ ስማቸው የሚታወቁ የቋራ አካባቢ (ጎንደር) መስፍን ነበሩ።እኝህ ሰው በዘመነ መሳፍንት ማለቂያ ላይ የነበሩትን ዋና ዋና መሳፍንት በጦርነት ድል ካደረጉ በኋላ በየካቲት ወር 1847 ዓ.ም ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብለው በደርስጌ ማርያም ቤተክርስቲያን (ጎንደር) በወቅቱ በነበሩት ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ሰላማ ተቀብተው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነዋል።ዐፄ ቴዎድሮ ስለ አገር አንድነት፣ለዘመናዊ ሥልጣኔና ዳር ድንበርን ከጠላት ለመከላከል በነበረው ቁርጠኛ ውሳኔ ብዙዎችን ያስደነቁና ያለ ዘመኑ የተፈጠረ ኢትዮጵያዊ አርበኛ ለመባል የቻሉ ናቸው።

ዐፄ ቴዎድሮስ ከልጅነታቸው ጀምሮ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው።እኚህ ንጉሥ በልጅነት ጊዜያቸው ወደ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ገብተው ትምህርተ ቤተክርስቲያንን እንደቀሰሙ የሚታወቅ ሲሆን ሥልጣን ላይ ሲወጡም ‹‹ቴዎድሮስ›› የሚለውን የንግሥና ስም የወሰዱት በዚህ ገዳም አካባቢ እንደ ‹‹ትንቢት›› (Myth) ሲወራ የነበረውን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ይነገራል። ትንቢቱም ‹‹ የዘመነ መሳፍንቱ የሰቆቃ ጊዜ ሲያበቃ አገርን አንድ የሚያደርግ፣ ሰላምን፣ ብልጽግናን ፍትሕን የሚያመጣ ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ይነግሳል›› የሚል እንደነበር ተዘግቧል።በዚሁ ገዳም በነበሩበት የልጅነት ጊዜያቸው ወቅት ዐፄ ቴዎድሮስ የቱርክ እስላሞች በተደጋጋሚ ያደርሱት የነበረውን ወረራና ጥፋት መገንዘብ እንደቻሉና ከነገሡ በኋላ ቱርኮችን ከኢሩሳሌም ሳይቀር ለማስወጣት የነበራቸው ሰፊ ዕቅድም ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ባደረባቸው ጥላቻ ምክንያት ነው።

ዐፄ ቴዎድሮስ የነበራቸውን ክርስቲያናዊ ማንነትና ለመንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸውን ቅርበት ለመመልከት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማጤን ተገቢ ነው።

- ከመጀመሪያዋ ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ጋር በሥርዓተ ቤተክርስቲያንና በቅዱስ ቁርባን ጋብቻቸውን መፈጸማቸው።

- የባሪያ ንግድን፣ ዕቁባት መያዝን፣ ከአንድ በላይ ሚስት/ባል ማግባትን፣ ውንብድናን፣ ዝርፊንና ጥንቆላን የመሳሰሉትን ኢ-ክርስቲያናዊ ተግባራት ለማጥፋት ቆርጠው መነሳታቸው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ በዘመናቸው የነበሩት ግብጻዊ ጳጳስ (አቡነ ሰላማ) ‹‹አገርን አንድ ለማድረግ አንድ ሃይማኖት ብቻ ሲኖር ነው›› ለሚለው ምክራቸው ትልቅ ትኩረት በመስጠት ለዚሁ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ብዙ ደክመዋል፡፡ለምሳሌ በወቅቱ በሰሜን ኢትዮጵያ የካቶሊክ ሚሲዮን የነበረውን አባ ያዕቆብ የተባለ ኢጣሊያዊ ከአገር እንዲባረር ተደርጎ ነበር፡፡

በዐጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት በጥቅምት ወር 1852 አባ ቄርሎስ አራተኛ የተባሉት ግብጻዊ ፓትርያርክ ወደ አገራችን መጥተዋል፡፡ፓትሪያርኩ የመጡበት ምክንያትም፡-

- በእስክንድርያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን አገራችንን ይጎብኙልን የሚል ግፊት ስለነበራቸው
- ዐፄ ቴዎድሮስን ከቱርኮች ጋር ለማስታረቅና ካይሮ የሚገኘውን የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ለማሳደስ የገንዘብ እርዳታ ለማሰባሰብ ሊሆን እንደሚችል ተገልጿል፡፡

ፓትሪያርኩ በመምጣታቸው ሞቅ ያለ አቀባበል የተደረገላቸው ቢሆንም ከቱርክ መንግስት ጋር ታረቁ ማለታቸው ዐፄ ቴዎድሮስን ስላበሳጫቸው ለእስር ዳርጓቸዋል፡፡ በጉዳዩም የተደናገጡት ሊቃውንቱና መኳንንቱ ለንጉሡ ፓትርያርክ ማሰር ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ አግባብ ያልሆነ ሥራ እንደሆነ ስለመከሯቸው ፓትሪያርኩ ከእስር ተለቀዋል፡፡ያምሆኖ ግን ፓትሪያርኩ ከእስር ከተፈቱ በኋላ ለቤተክርስቲያኑ ማሠሪያ የሚሆን ብዙ ወርቅ፣ ብርናየ ዝሆን ጥርስ ተሰጥቷቸው ወደ አገራቸው በሰላም ተመልሰዋል፡

ዐፄ ቴዎድሮስ በዘመነ መንግሥታቸው የመጀመሪያ ዓመታት ላይ የነበረው የላቀ የቤተክርስቲያን ፍቅር፣ የሃይማኖት ቅናትና፣ መንፈሳዊ ወኔ ተቀልብሶ በኋላ ላይ በአዝናኝ ሁኔታ ከቤተክርስቲያን ጋር በነበራቸው ግጭት ተደምድሟል፡፡ዐፄ ቴዎድሮስ የቤተክርስቲያንን መሬት ቀንሰው መውሰዳቸውና ሦስት ዲያቆናት ብቻ አስቀርተው ሌሎቹ ካህናት አራሾች ሆነው ለመንግሥት ግብር እንዲገብሩ ትዕዛዝ ማስተላለፋቸው ከቤተክርስቲያን ጋር ለነበራቸው ግጭት ዋነኛው መንስኤ ነው፡፡ንጉሡ ይህን ያደረጉትም አገርን አንድ በማድረግ (Varification)፣ ዘመናዊ ስልጣኔ ለማስፋፋት (Modernization) እና የአገርን ዳር ድንበር ከጠላት ለመጠበቅ (Defense territorial Integrity) የሚሉ ሦስት መሰረታዊ ዕቅዶቻቸውን ለማስፈጸም የገንዘብ እጥረት ስላጋጠማቸው መሆኑ ይታመናል፡፡ በዚሁ የንጉሡ ትእዛዝ ምክንያት ካህናቱ በማመጻቸውና ተቃውሞ በማሰማታቸው ዐፄ ቴዎድሮስ በጣም ብስጩ እንዲሆኑና በጭካኔ የተሞላ እርምጃ እንዲወስዱ አድርጓቸዋል፡፡ ይባስ ብለውም በዚሁ የካህናቱ ሁኔታና የጳጳሱ የአቡነ ሰላማ ውግዘት ተበሳጭተው ጳጳሱን ወደ እስር ቤት ማስገባታቸው ተዘግቧል፡፡በዚህ ከቤተክርስቲያን ጋር በነበረው ግጭት ምክንያት ዐፄ ቴዎድሮስ ሕዝባዊ ድጋፍ በመነፈጋቸው ብቻቸውን ሁነው ለሌሎች ተደራራቢ የውስጥና የውጭ ችግሮች ተጋልጠዋል፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ከቤተክርስቲያን ጋር ከመጋጨታቸው በተጨማሪ ከውጭ አውሮፓ መንግሥታት ጋር ለማድረግ ያሰቡት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አለመሳካት ውድቀታቸውን አፋጥኖታል፡፡ንጉሡ አስቀድሞ የተገለጹትን ሦስት መሰረታዊ ዕቅዶቻቸውን እውን ለማድረግ የአውሮፓውንን ገንዘብና ዘመናዊ ጦርመሳሪያ ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ደብዳቤ መጻፍ መጀመራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ከእነዚህም መካከል ዐፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዟ ንግስት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ ለአብነት ይጠቀሳል፡፡ዐፄ ቴዎድሮስ በደብዳቤዎቻቸው ላይ በአውሮፓ ካለ የክርስቲያን መንግሥታት ጋር በጋራ ሁነው የቱርክ እስላሞችን ለመደምሰስ ማሰባቸውን ይገልፁ ነበር፡፡ሆኖም ግን ለጥያቄዎቻቸው ተገቢውን መልስ ባለማግኘታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ፈረንጆች ሰብስበው መቅደላ ላይ አስረዋል፡፡ እነዚህ እስረኞች በማሰራቸው ውዝግቡ የበለጠ ተካረረ፡፡በመጨረሻም በጄነራል ሮበርትና ፒየር የተመሩት 32000 የእንግሊዝ ወታደሮች በ1859 ዓ.ም ወደ አገራችን በመግባት ወደ መቅደላ አምርተዋል፡፡ዐፄ ቴዎድሮስም ከውስን ወታደሮቻቸው ጋር ሆነው ጥቂት መከላከል ካደረጉ በኋላ ለእንግሊዝ ወታደሮች እጃቸውን ሳይሰጡ ራሳቸውን በራሳቸው መግደላቸው ይታወቃል፡፡ከዚህ ሁሉ በኋላ የእንግሊዝ ወታደሮች እጅግ ብዙ የአገርና የቤተክርስቲያን ቅርሶች ዘርፈው ወደ መጡበት ተመልሰዋል፡፡

5.1.2. ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (፩ሺ፰፻፷፫)

ከዐፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ የላስታው ባላባት ዋግሹም ጎበዜ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ኢትዮጵያን ለሦስት አመታት ካስተዳደሩ በኋላ በዝብዝ ካሳ ተብለው በትግራይ ገዢ በጦርነት ድል ተመትተው መንግስታቸው አክትሟል፡፡በዝብዝ ካሳም በ፩ሺ፰፻፷፫ ዓ.ም አቡነ ቴዎፍሎስ በተባሉት ግብጻዊ ጳጳስ ዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ተብለው ነገሱ፡፡የአጤ ዩሐንስ ዘመነ መንግስት አውሮፓውያን አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት ለመቀራመት የተሰለፉበት ወቅት ስለነበር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ተደጋጋሚ የውጭ ወረራና ጥቃት ደርሶባታል፡፡ ግብጾች፣ኢጣሊያኖችና ደርቡሾች በቅደም ተከተል በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በአገራችን ላይ ጥቃት ለመሰንዘር የሚሞክሩ ናቸው፡፡የግብጽና ኢጣሊያን ወረራ በኢትዮጵያውያን ድባቅ ሲመታ ደርቡሾች ግን ጎንደርና ጎጃምን ወረው ብዙ አብያተ ክርስቲናትን ካቃጠሉ በኋላ በመጨረሻ መተማ ላይ ለንጉሡ መሞት ምክንያት መሆናቸው ይታወቃል፡፡

ዐፄ ዮሐንስ ለዘብተኛ የፖለቲካ አቋም ያራምዱ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን በሃይማኖታዊ ጉዳይ ግን እጅግ ጠንካራና ቆራጥ ነበሩ፡፡ሚሲዮናውያን ኢትዮጵያ ውስጥየ ለመዱትን የመከፋፈልና የቅሰጣ ስራ እንዳያከናውኑ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጉባቸው እንደነበር ተጽፏል፡፡ለምሳሌ አባ ማትያስ የተባለው አስቸጋሪ የካቶሊክ ሚሲዮን ከአገር እንዲባረር የተደረገው በዐፄ ዩሐንስ ነው፡፡ዐፄ ዮሐንስ ለብዙ ዘመናት ለቤተክርስቲያን ህመም ሆኖ የነበረውን የቅባትና ጸጋ ባዕድ ትምህርትም እንዲያከትም አድርገውታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ንጉሡ በወሎ ቦሩ ሜዳ የሃይማኖት ጉባኤ በመጋቢት ወር፩ሺ፰፻፸ ዓ.ም እንዲጠራ አድርገው ብዙ ክርክር ከተደረገ በኋላ እነኚህ የቅባትና ጸጋ እምነቶች እንዲከትሙና በርካታ ሙስሊሞች ወደ ክርስትና እንዲመለሱ አድርገዋል፡፡በጉባኤው

ማጠቃለያ ላይም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ሆኖ ታውጇል። በዚሁ የቦሩ ሜዳ ጉባኤ መሐመድ አሊና አባዋጠው የተባሉ ሁለት ዋና ዋና የወሎ ባላባቶች ክርስትና ሃይማኖት ተቀብለው እንደቅደም ተከተላቸው ሚካኤልና ሃይለማርያም የሚል ክርስትና ስም ወጥቶላቸዋል።መምህር አካለወልድ የተባሉ ታዋቂ የቤተክርስቲያን ሊቅም እነዚህን ለማስተማር ተመድበዋል።አንድአንዶች እንደሚሉት በወሎ በተካሔደው የቦሩ ሜዳ ጉባኤ በጭካኔ የተደረገ ሳይሆን በዲፕሎማሲያዊ አቀራረብ በፍቅርበ ዘዴ በፈሊጥ የተከናወነ እንደነበር መረዳት አያዳግትም።ለምሳሌ ዐፄ ዮሐንስ የወሎውን ገዥ መሐመድ አሊን ሚካኤል ተብሎ በክርስትና ስም ከተጠመቀ በኋላ ራሳቸው ክርስትና አባት ሆነው የራስነት ማዕረግ ሰጥተውታል።ኃይለማርያም ተብሎ ለተጠመቀው ለአባዋጠው ደግሞ ምኒልክን ክርስትና አባት አድርገው የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተውታል።ይህንንም ያደረጉት ሌሎቹ ሙስሊሞች የመሪዎቻቸውን ምሳሌ ተከትለው ክርስትናን እንዲቀበሉ ለማበረታታት ጭምር ነው።

ዐፄ ዮሐንስ እንደ ዛጉዌ ንጉሥ ቅዱስ ሐርቤ (አጤ ገብረማርያም) ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን እንዲሾሙ ለግብጽ ቤተክርስቲያን ያቀረቡት ጥያቄ በታሪክ ከሚታወሱት ነገሮች አንድ ነው።ይህ ጥያቄያቸው መልስ ለማግኘት ባለመቻሉ ከአርመን ፓትርያርክ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ተጻጽፋው እንደነበር ተዘግቧል።ሆኖም ግን ያልተለመደ ነገር በመሆኑ ተመልሰው ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ጥያቄ አቅርበው አራት ጳጳሳትን አስመጥተዋል። ይህን ያህል ቁጥር ያላቸው ግብጻውያን ጳጳሳት ወደ ሀገራችን ሲመጡም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።ጳጳሳቱም አቡነ ዮሐንስና አቡነ ጴጥሮስን በትግራይ አስቀርተው አቡነ ሉቃስን ወደ ጎጃም አቡነ ማቴዎስን ወደ ሸዋ ልከዋቸዋል።

ዐፄ ዮሐንስ ደብረ ሊባኖስን ጨምሮ በግራኝ የፈረሱና የተቃጠሉ ገዳማትንና በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲሁም ከአገር ውጪ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አበምኔት መምህር ወልደ ሰማዕት አሳሳቢነት የዘውድ ቅርፅ ያላትን ደብረ ገነት ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያንን ከቱርክ የማረኩትን ወርቅ ልከው አሰርተዋል።በርግጥ በኢየሩሳሌም የምትገኘው ቤተክርስቲያን ሥራዋ ሳይጠናቀቅ ዐፄ ዮሐንስ ስላረፉ ከፍጻሜ ያደረሷት (1885 ዓ.ም) አጼ ምኒልክ ናቸው።

ዐፄ ዮሀንስ ለአገርና ለቤተክርስቲያን ጠቃሚ የሆኑ በርካታ ተግባራትን ካከናወኑ በኋላ በ1881 ዓ.ም በመተማ ላይ ከደርቪሾች ጋር ተዋግተው መሞታቸው ይታወቃል።

5.1.3. ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (1881-1906 ዓ.ም)

ዐፄ ምኒልክ በዐፄ ቴዎድሮስ የተጀመረውን አገርን አንድ የማድረግና ጠንካራ መንግሥት የመመስረት ህልም እውን የሆነውና ፍጻሜ ያገኘው በዐፄምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው።ለዚህም ነው አንድአንዶች ዐፄ ምኒልክን ኢትዮጵያዊ ቢስማርክ በማለት ያሞካሿቸዋል። ቢስማርክ የተከፋፈለች ጀርመንን አንድ ያደረገ በመሆኑ በታሪክ ዘወትር ይታወሳል።

በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቱ ለማድረግ ቆርጦ የተነሳበት ጊዜ ነበር። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የውጫሌ ስምምነት በ1881 መፈረሙና በ1888 የተካሄደው አድዋ ጦርነት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ።በኢጣሊያ ተወካይ አንቶኖሊና በዐፄ ምኒልክ መካከል የተደረገው የውጫሌ ስምምነት ሃያ አንቀጾች የነበሩት ሲሆን በተለይ 17ኛውን አንቀጽ አዛብተው በመተርጎም ኢትዮጵያ በኢጣሊያ የሞግዚትነት አስተዳደር ሥር ሆናለች ብለው ለዓለም መንግስታት ያሳወቁበት አጋጣሚ ነበር።ይህ የተጭበረበረ ስምምነት ሲታወቅም ዐፄ ምኒልክ ውሉን በማፍረሳቸው የአድዋ ጦርነት ሊመጣ የግድ ሆኗል።ለአድዋው ድል መገኘትም የኢትዮጵ ቤተክርስቲያን ካህናት ታቦታትን ተሸክመው በጸሎት፣ሞራል በመስጠትና በማበረታታት ያደረጉት አስተዋጽኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም።ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሃይማኖት ሰበብ ቅኝ የተያዙ በርካታ የአፍሪካ አካባቢዎች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በአድዋ ድል ያደረገችውን ተሳትፎ በመረዳትና የነጻነታቸው ተምሳሌት በማድረግ ሃይማኖታችን የኢትዮጵያ ሃይማኖት ነው በማለት እንቅስቃሴዎችን ያደርጉ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል።

- ዐፄ ምኒልክ ለአገራቸው ካበረከቱት በርካታ ተግባራት በተጨማሪ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም ብዙ ሥራ ሠርተዋል።
- ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት የመተዳደሪያ መሬት አግኝተዋል።
- ወደ ደቡብ ምዕራብና ምስራቅ አካባቢዎችም አሰሳ በሚያደርጉበት ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ከግራኝ ጦርነት ጀምሮ ጠፍተው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትን እንዲታደሱ አድርገዋል። አዲሶችንም አሠርተዋል።
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የዴርሱልጣን ገዳም ሕጋዊ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ መረጃዎች እንዲሰባሰቡ ያደረጉት ጥረት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። በ1895 ዓ.ም በደጅ አዝማች መሸሻ ወርቁ የሚመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ወደ ቱርክ ልከው በግብጽ የተያዘው የዴርሱልጣን ገዳም እንዲለቀቅ ለቱርክ መንግሥት ጥያቄ ማቅረባቸው ይታወቃል።በዚህ ምክንያት ከግብጾች ጋር በነበረው ክርክር ተዘግቶ የነበረው በር ተከፍቶ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት መግቢያ መውጫ ለማግኘት ችለዋል።ከዚህ በተጨማሪ ዐፄ ምኒልክ ለገዳማቱ መርጃ የሚሆን በኢየሩሳሌም ክዳሊዮን በተባለ ባንክ ሁለት መቶ ሺህ የማሪያትሬዛ ብር እንዳስቀመጡም ተዘግቧል።
- በዐፄ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት በሚሲዮናውያን ላይ ሚደረግ ቁጥጥር ስላልነበረ የተለያዩ ሚሲዮናውያን ወደ አገራችን በመግባት እንደፈለጉ ለመስፋፋት አጋጣሚውን አግኝተዋል።በዐፄ ዮሐንስ የተባረረው አባማትያስ ሳይቀር ተመልሶ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የለመደውን የመከፋፈል ሥራ ለመሥራት ዕድሉን አግኝቷል።በተለይ ዐፄ ምኒልክ ‹‹ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው›› የሚለው አቋማቸው ለበርካታ ፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲስፋፍና የተንኮል ሴራ እንዲሸርቡ ምክንያት ሆኗቸዋል።

5.1.4. ልጅ ኢያሱ፣ ንግሥት ዘውዲቱ፣ ራስ ተፈሪ መኮንን እና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (1906-1922)

ከዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በኋላ የንጉሥ ሚካኤል ልጅ ኢያሱ ሥልጣኑን ተረክቦ አገሪቱን ለጥቂት ዓመታት ማስተዳደሩ ይታወቃል፡፡ልጅ ኢያሱ ሃይማኖታዊ አቋሙ ግልጽ ስላልነበር በዘመኑ ብዙዎችን ግራ አጋብቷል፡፡በተለይ ከኢትዮጵያ የጠረፍና ቆላማ አካባቢ ሙስሊሞች ጋር የነበረው ከልክ ያለፈ ግንኙነት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሰዎች በጥርጣሬ ዐይን እንዲታይ አድርጎታል፡፡እንዲያውም ድሮስ የመሐመድ አሊ ልጅ አይደል የአባቱን የጥንቱን እምነት መከተሉ የሚያስደንቅ አይደለም ወዘተ... የሚል ሀሜት ውስጥ ውስጡን ነበር ይባላል፡፡የሚገርመው ነገር ልጅ ኢያሱ በአንድ አንድ አካባቢዎች አብየተ ክርስቲያናት እንዳሳነጹ ሲነገር በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ መስጊዶችን ማሰራቱ ይታወቃል፡፡የሆነ ሆኖ ግን ኢያሱ በነበረው ግራ የተጋባ የእምነት ፖሊሲው እና ወደ እስልምና ያጋድል ስለነበር ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተመቸ ዘመን አልነበረም፡፡

ልጅ ኢያሱ በ1909 ዓ.ም ከሥልጣን ከተወገደ በኋላ በኢትዮጵያ የሁለት ሰዎች አስተዳደር (Dual Rule) ተፈጥሯል፡፡የዐፄ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ እንደ ንግሥት እና የራስ መኮንን ልጅ ተፈሪ መኮንን እንደ ሞግዚትና አልጋ ወራሽ ሆነው ሥልጣኑን ተረክበዋል፡፡ በዚሁ ዘመን ከተከናወኑት ዓበይት መንፈሳዊ ተግባራት መካከል፡-

- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዘመናዊ አስተዳደርን መከተል መጀመሯ
- በ1919 ዓ.ም የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር መቋቋሙና ለመጀመሪያ ጊዜ ከራሷ ልጆች ጳጳሳትን መሾም መቻሏ በጉልህ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

፭.፩.፭. ዐፄ ኃይለሥላሴ እና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (1922-1960)

- ዐፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በርካታ መንፈሳዊ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህ መካከል፡-
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከ16 ክ/ዘመናት በኋላ ራሷን እንድትችል ንጉሡ ያደርጉት ያላሰለሰ ጥረት በ1951 ዓ.ም አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ ሁነው መሾማቸው፡፡
- በዘመናዊ መልኩ የተደራጁ እንደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅና ሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ያሉ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ተቋማት እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸው፡፡
- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አስተዳደር በሚገባ ተደራጅቶ እንደሰበካ ጉባኤና ሰ/ት/ቤት ያሉ መዋቅሮች በቃለ አዋዲ የተቋቋሙትም በዚህ ዘመን ነው፡፡
- ከኤፌሶን ጉባኤ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜበ 1957 ዓ.ም በአፍሪካ አዳራሽ (አዲስ አበባ) በንጉሠ ነገሥቱ ጋባዥነት በአምስቱ የምስራቅ ኦርቶዶክስ አኀት አብተክርስቲያናት ስብስባ ማድረጋቸው፡፡
- በርካታ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ ከፍተኛ ዕገዛ ማድረጋቸው
    - የምስካ የጎዙናን ገዳም

- የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
- የአክሱም ጽዮን ማርያም ክቧ ቤተክርስቲያን

ዐ ጽላተ ሙሴ የምትገኝበትን የተለየች ባለ አንድ ፎቅ ህንጻ ያሠሩት በ1945 ዓ.ም የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ባለቤት እቴጌ መነን ናቸው፡፡

በዚህ ዘመን ከተከሰቱት ዓበይት ፈተናዎች መካከል ደግሞ፡-

- ለ 5 ዓመት የቆየው የፋሽስት ኢጣሊያ ቆይታ
- ከልክ ያለፈው የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን እንቅስቃሴ (ዐፄ ኃይለሥላሴ ልክ እንደ ምኒልክ ‹‹አገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው›› የሚለው ይፋዊ መግለጫቸው)

5.2. ራስን የመቻል ትግል እና ስኬት

አባ ሰላማከሣቴ ብርሃን (ቅዱስ ፍሬምናጦስ) የመጀመሪያ ጳጳስ ሆኖ ከተሾመ በኋላ እስከ 1951 ዓ.ም ኢትዮጵያ የራሷን ጳጳስ እስክትሾም ድረስ 110 ግብጻውን ጳጳሳት ወደ ኢትዮጵያ ተሾመው ተልከዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለረጅም ዘመናት ከግብጽ ጳጳሳትን ለማምጣት የተገደደችበት ዓይነተኛው ምክንያት በ7ኛው መ/ክ/ዘመን በሠለስቱ ምእት (318ቱ ሊቃነ ጳጳሳት) ስም በኒቅያ ጉባኤ 42ኛው ቀኖና ላይ የተጨመረው የሐሰት ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ እርሱም ‹‹ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሹሙ›› የሚል ነው፡፡ይህ የሐሰት ዐረፍተ ነገር ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ በ14ኛው መ/ክ/ዘመን በተተረጎመው ፍትሐ ነገሥትም ላይ በመጨመሩ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት በሥርዓት መጽሐፋቸው ሳይቀር ታስረው ለዐሥራ ስድስት ክፍለ ዘመናት በግብጽ ቤተክርስቲያን ሥር የሞግዚትነት አስተዳደር ጥገኛ ሆኖ መቀጠል የግድ ሆኖባቸዋል፡፡ በመሰረቱ የኒቅያ ጉባኤ በተደረገ ወቅት 325 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጳጳስ አልነበራትም ፍሬምናጦስም ተሸሞ የመጣው ከአምስት ዐመት በኋላ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ330 ዓ.ም ነው፡፡ ስለሆነም በኒቅያ ጉባኤ ቀኖና ላይ የተጨመረው ዐረፍተ ነገር ሐሰት መሆኑን እንመለከታለን፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ መታወቅ ያለበት ነገር የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጳጳስ እንጂ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ሃይማኖትን ከእስክንድርያ (ከግብጽ) አላስመጣችም፡፡የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አባት ፍሬምናጦስ ወደ ግብጽ የተላከው ጳጳስን እንጂ የክርስትና እምነትን ለማምጣት እንዳልሆነ ይታወቃል፡ የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ34 ዓ›ም በመጀመሪያ መቶክ/ዘመን በጃንደረባው አማካኝነት መሆኑ ቀደም ብለን ገልፀነዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ለረጅም ጊዜያት ከግብጽ ጥገኝነት ሥር ሁና ከእስክንድርያ ጳጳሳትን ስታስመጣ መኖሯ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ ከግብጽ ይመጡ የነበሩ ጳጳስ ለኢትዮጵያውያን ቋንቋ፣ ባህልና ነባራዊ ሁኔታ እንግዳ

ስለሚሆኑ ከሕዝበ ክርስቲያን ጋር ለመግባባት የሚችሉት በአስተርጓሚ በመሆኑ በስብከት፣ በጸሎት፣ ቡራኬ በመስጠትና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ከፍተኛ ክፍተትተ ፈጥሮ ነበር።።ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ጳጳሳትም አንድ ብቻ በመሆናቸው በመላ ሀገሪቱ ተዘዋውረው ድቁና እና ቅስና ለመስጠትም እጅግ አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል።።

በዚህ ሁሉ ችግር ታጅቦ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ምእመናንን መንፈሳዊ ጥማት ለማርካት ያልቻለውን ግብጻዊ ጳጳስም ለማስመጣት የነበረው ውጣ ውረድ ቀላል አልነበረም።። አንድ ጳጳስ ከግብጽ ለማስመጣት ለበርካታ ጊዜ ደጅ መጥናትና ለሡልጣኑ (ለከሊፋው) እና ለፓትሪያርኩ ከፍተኛ ስጦታና ገጸበረከት ማቅረብ የግድ ነበር።።

19ኛው መ/ክ/ዘመን ዐፄ ዮሐንስ፣ አቡነጴጥሮስ፣አቡነ ሉቃስና አቡነ ማቴዎስ የተባሉ አራት ግብፃውያን ጳጳሳት ማስመጣታቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል።።ከነዚህ ጳጳሳት መካከል ለረጅም ጊዜ (እስከ 1919 ዓ.ም ድረስ) በሕይወት ቆይተው አገልግሎት መስጠት የቻሉት አቡነ ማቴዎስ ነበሩ።።

ከአቡነ ማቴዎስ ሞት በኋላ በንግሥተ ነገስታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ራሷን ለመቻል ለምታደርገው ጥረት ቆርጣ ተነሣች።።ይህንኑ ጉዳይ ከግብ ለማድረስ በወቅቱ ለነበሩት የግብጹ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ አምስተኛ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ራሷን መቻልና በራሷ ልጆች ለመተዳደር እንድትችል በዛያሉ ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን የጵጵስና ማዕረግ እንዲሰጡ ከበድ ያለ ጥያቄ በደብዳቤ ቀረበላቸው።።ከዚህ በኋላ በእስክንድርያና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስትያናት መካከል ለሦስት ዓመታት የዘለቀ ከፍተኛ ውይይት ተደርጎ በግንቦት ወር በ1921 ዓ.ም አራት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ካይሮ ሄደው የጵጵስና ማዕረግ ተሸመዋል።።

- አቡነ ቄርሎስ (ግብፃዊ) የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ
- አቡነ ጴጥሮስ የወሎና የላስታ ጳጳስ
- አቡነ አብርሃም የጎጃምና የጎንደር ጳጳስ
- አቡነ ይስሐቅ የትግራይና የሰሜን ጳጳስ
- አቡነ ሚካኤል የምዕራብ ኢትዮጵያ ጳጳስ
- አምስተኛው እጨጌ ገብረመንፈስቅዱስ ግን በሕመም ምክንያት ካይሮ ሄደው ለመቀባት ስላልቻሉ ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ በ1922 ዓ.ም ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት ቀብተው ሳዊሮስ በሚል ስም የጵጵስና ማዕረግ ሰጧቸው።።

ከ1928-1933 ዓ.ም ድረስ የነበረው የኢጣሊያ ወረራብ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ከባድ ችግር መፍጠሩ አይዘነጋም።። በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤልን የመሳሰሉ ታላላቅ አባቶችን አጥታለች።። በዚህ የመከራ ዘመን አቡነ ቄርሎስ የተባሉት ግብፃዊ ሊቀጳጳስ ፋሺስት የኢጣሊያ መንግስት ሹመታቸውን እንዲያጸድቅላቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥለው ወደ ሮም እንደተጓዙ ይነገራል።።ሆኖም ግን ጉዳያቸው ስላልተሳካላቸው ወደ ኢትዮጵያ ሳይመለሱ በዚያው ወደ አገራቸው ወደ ግብጽ ሄደው ቀርተዋል።።የችግሩን አሳሳቢነት ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያየ አድባራትና ገዳማት ሊቃውንትና ምእምናን በታኅሳስ ወር 1930 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ አካሂደዋል።። ተሰብሳቢዎቹም ቀደም ብለው ከተሾሙት ጳጳሳት መካከል አቡነ አብርሃምን

ሊቀጳጳስ አድርጎ ከመረጡ በኋላ እርሳቸውም በዕለቱ ሌሎች አምስት ኢትዮጵያውያንን ጳጳሳትና አንድ ኤጲስ ቆጶሳትን ሹመዋል፡፡ እነርሱም

1. አቡነ ዩሐንስ - ዕጨጌና ቆጶሳትን ሹመዋል
2. አቡነ ማርቆስ - የኤርትራ ጳጳስ
3. አቡነ ሰላማ - የሐረር ጳጳስ
4. አቡነ ገብርኤል - የጎንደር ጳጳስ
5. አቡነ ማቴዎስ - የወሎ ጳጳስ
6. አቡነ ሉቃስ - የወለጋ ኤጲስ ቆጶስ ናቸው፡፡

ይህ ሹመት ኢትዮጵያውያንንና የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ያስደሰተ ዓብይ ተግባር ቢሆንም የግብጽ ቤተክርስቲያንን ግን በእጅጉ አሳዝኗል፡፡ በዚህም ሳያበቃ የግብጽ ቤተክርስቲያን ድርጊቱ ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ ነው በማለት አቡነ አብርሃምንና በእርሳቸው የተሾሙትን ሌሎች ጳጳሳት አውግዛለች፡፡

በሐምሌ ወር 1931 ዓ.ም አቡነ አብርሃም በማረፋቸው ምክንያት በመስከረም ወር 1932 ዓ.ም/ አቡነ ዮሐንስ በምትካቸው ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሸሙ፡፡በዚያው በተሸሙበት ዕለትም አቡነ ዮሐንስ ሌሎች አራት ጳጳሳትን አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሹመዋል፡፡እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አቡነ ፊልጶስ
2. አቡነ ጎርጎርዮስ
3. አቡነ ማትያስ
4. አቡነ አትናቴዎስ
5. አቡነ ቄርሎስ

ከአምስት ወራት በኋላ ደግሞ ሊቀጳጳሱ አቡነ ዮሐንስ ‹‹አቡነ ዘካርያስ›› በሚል ስም አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሹመው በኢየሩሳሌም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ገዳማት ሐላፊ አድርገው ልከዋቸዋል፡፡

ነጻነት ከተመለሰ በኋላ በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ለረጅም ጊዜ ተቋርጦ የነበረው የግብጽና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውይይት እንደገና በአዲስ መልክ ተጀምሯል፡፡ሆኖም ግን አስቀድሞ ያለ እስክንድርያ ቤተክርስቲያን ፈቃድ የተሾሙት

ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የተጣለው ውግዘት ቢነሳም የጵጵስና ማዕረጋቸው ግን አብሮ ተነሥቷል፡፡በመከራ ዘመን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያንና ምእመናኖቿን ጥለው የሸሹት ግብጻዊ ሊቀጳጳስ አቡነ ቄርሎ ስም የሁኔታውን መረጋጋት አይተው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጥተዋል፡፡

የፋሺስት ኢጣሊያን መንግሥት ከአገራችን ለቆ ከወጣ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንና የኢትዮጵያ መንግስትራስን ለመቻል በሚያደርገ ውጥረት የግብጽ ቤተክርስቲያን ፈቃድ እንዲገኝ ለብዙ ጊዜያት በደብዳቤ በስልክና በመልእክተኛ ሳይቀር ግንኙነቶችና ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድና ድካም በኋላ በ1940 ዓ.ም የግብጽ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አምስት ኢትዮጵውያን መነኮሳትን ጵጵስና እንዲሾሙ ፈቃደኝነቱን ገለፀ፡፡በዚህ መሰረት ለእጩነት የቀረቡት የኢትዮጵያውያን መነኮሳት ካይሮ ሄደው በአቡነ ዮሳብ ፪ኛ (የግብጽ ፓትሪያርክ) የጵጵስና ማዕረግ ተቀብለዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. አቡነ ባስልዮስ (እጨጌ ገብረጊዮርጊስ)
2. አቡነ ሚካኤል (መ/ር ግርማ)
3. አቡነ ቴዎፍሎስ (ሊቀ ስልጣናት መልእክቱ)
4. አቡነ ጢሞቴዎስ (መ/ር ጌታሁን)
5. አቡነ ያዕቆብ (መ/ር ዘፈረ)

ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በጥቅምት ወር 1943 ዓ.ም በማረፋቸው ምክንያት በዚያኑ ዓመት በጥር 1943 ዓ.ም አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵዊ ሊቀ ጳጳስ በመሆን በግብጽ ካይሮ በአቡነ ዮሳብ ፪ኛ በመሰየማቸው ለረጅም ጊዜ የነበረው የሞግዚትነት አስተዳደር ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ አከተመ፡፡በተመሳሳይ ዓመት አቡነ ባስልዮስ ሊቀጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሌሎችም አምስት ኢትዮጵያን መነኮሳት የጵጵስና ማዕረግ ሰጥተዋል፡፡ እነርሱም፡-

- አቡነ ገብርኤል - የወሎ ጳጳስ
- አቡነ ታዴዎስ - የአሊባብ ጳጳስ
- አቡነ ፊልጳስ - በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ
- አቡነ ማርቆስ - የኤርትራ ጳጳስ እና
- አቡነ ጎርጎርዮስ - የከፋ ጳጳስ ናቸው፡፡

አቡነባ ስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ሆነው ከተሾሙ በኋላም በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ቀድሞ የነበረው ግንኙነትና ውይይት ተጠናክሮ ቀጥሎ በመጋቢት ወር 1951 ዓ.ም አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ

በመሆን በ116ኛው የግብጽ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ ተሹመው ለዘመናት የነበረውን ራስን የመቻል ትግል በታላቅ ውጤት ተጠናቋል።አቡነ ባስልዮስ በካይሮ ፓትርያርክ ሆነው በተሾሙበት በዚያች ታሪካዊ ዕለትም የግብጽ ፕሬዝዳንት ጋማል አብደልና ሲርና የኢትዮጵያ ንጉሥ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መገኘታቸው ይታወቃል።ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በኋላ የተሾሙ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርኮች ሢመት የተፈጸመው በአዲስ አበባ ሲሆን እነርሱም በቅደም ተከተላቸው መሠረት አቡነ ቴዎፍሎስ (193-1967 ዓ.ም) አቡነ ተክለሃይማኖት (1968-1980 ዓ.ም) አቡነ መርቆርዮስ (1980-1983 ዓ.ም) አቡነ ጳውሎስ (ከ1984 -2005ዓ.ም) አቡነ ማቲያስ (ከ2005 ዓ.ም)ጀምሮ ናቸው።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ ነጻነትን ሙሉ በሙሉ ካገኘች በኋላ በርካታ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን አበርክታለች። ከእነዚህ መካከል ሀገ ቤተክርስቲያንን መደንገግ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን መተርጎምና ማሳተም፣ጠቅላይ ቤተክህነትን ከላይ እስከ ታች ማዋቀር በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር መዘርጋትና ማጠናከር፣ ሰ/ት/ቤትና ሰበካ ጉባኤን ማደራጀት፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትን ማቋቋም ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ተቋማትን መክፈት፣ የወንጌል አገልግሎትን ማስፋፋት እና የውጭ ግንኙነትን ማጠናከር የሚሉት ይገኙበታል።

ምንጮች

1 ሰማንያወአሐዱ መፅሐፍ ቅዱስ

2 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ታሪክ አባ ጎርጎሬዎስ

3 የቤተክርስትያን ታሪክ ቁጥር 2 ማህበረ ቅዱሳን

4 (History Of The Etthiopian Ortodox Church Part 1 And 2 Professor Lule Melaku)

5 የኢትዮጵያ ታሪክ ከአባ ጋስፓሪኒ-ማ

6 ታሪክ ነግስት መ/ም ደሴ ቀለብ

7 የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ መረጃዎች ዳንኤልክብረት

8 ስንክሳር